
የ2015 ዓመት ምዘና

# አውራምባ ጠቋሚ

## የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን መስተዳድሮች የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምዘና



CARD
የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY
MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF THE GAME!

Freedom House

## ስለ ካርድ

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ በአዋጅ ቁጥር 1113/2011፣ በኢትዮጵያ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን መዝገብ ቁጥር 4307 ሐምሌ 17፣ 2011 የተመዘገበ፣ ቦርድ መር፣ የአገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ነው።

ካርድ በሰብዓዊ መብቶች እሴት ላይ የቆመ ዴሞክራሲያዊ ባሕል ያበበባት ኢትዮጵያን የማየት ራዕይ ሰንቆ፥ የኢትዮጵያ ዜጎች እና የዜጎች ማኅበራት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር በመሟገት ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲያሰፍኑ የሚያስችላቸውን የአቅም ግንባታ ማድረግ ተልዕኮ በማንገብ እየሠራ የሚገኝ ድርጅት ነው።

---

This publication was funded by a sub-grant given to CARD by the Freedom House [in part] by a grant from the United States Department of State. The opinions, findings and conclusions stated herein are those of the CARD's and do not necessarily reflect those of the United States Department of State.

**© December 2023, Center for the Advancement of Rights and Democracy (CARD).**

## For More Info

Email: info@cardeth.org
Website: www.cardeth.org
Phone: +251 116 671 657

**Book Design: Armen Interactive - +251 938 352 532**

የ2015 ዓመት ምዘና

# አውራምባ ጠቋሚ

## የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን መስተዳድሮች የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምዘና


CARD
የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY
MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF THE GAME!

Freedom House

# ማውጫ


**መቅድም** .......... I

**ማጠቃለያ** .......... III

**መግቢያ** .......... 1

**የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ** .......... 4

**የፖለቲካ ብዝኃነት** .......... 8

**የፖለቲካ ብዝኃነት ምዘኔ** .......... 9

**የፖለቲካ ብዝኃነት በድኅረ ምርጫ 2013 ዐውድ** .......... 9

**የፖለቲካ ብዝኃነት በስድስቱ ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች** .......... 11

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር .......... 11

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መስተዳድር .......... 12

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር .......... 13

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር .......... 14

የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር .......... 15

የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር .......... 16

**የ2015 ዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምዘና** .......... 17

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር** .......... 18

የመንግሥት ውጤታማነት .......... 18

ቁጥጥር እና ሚዛን .......... 20

የዜግነት ነፃነቶች .......... 22

ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች .......... 24

የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ .......... 26

አጠቃላይ ውጤት .......... 28

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መስተዳድር** .......... 30

የመንግሥት ውጤታማነት .......... 30

ቁጥጥር እና ሚዛን .......... 33

የዜግነት ነፃነቶች ........ 35
ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ........ 38
የኀዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ ........ 40
አጠቃላይ ውጤት ........ 42
**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ........ 44**
የመንግሥት ውጤታማነት ........ 44
ቁጥጥር እና ሚዛን ........ 46
የዜግነት ነፃነቶች ........ 48
ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ........ 51
የኀዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ ........ 52
አጠቃላይ ውጤት ........ 54
**የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ........ 56**
የመንግሥት ውጤታማነት ........ 56
ቁጥጥር እና ሚዛን ........ 58
የዜግነት ነፃነቶች ........ 60
ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ........ 62
የኀዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ ........ 64
አጠቃላይ ውጤት ........ 65
**የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ........ 67**
የመንግሥት ውጤታማነት ........ 67
ቁጥጥር እና ሚዛን ........ 69
የዜግነት ነፃነቶች ........ 71
ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ........ 73
የኀዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ ........ 74
አጠቃላይ ውጤት ........ 75
**የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር ........ 77**
የመንግሥት ውጤታማነት ........ 77
ቁጥጥር እና ሚዛን ........ 79
የዜግነት ነፃነቶች ........ 80
ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ........ 82
የኀዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ ........ 84
አጠቃላይ ውጤት ........ 85

---

**መደምደሚያ ........ 87**

# መቅድም

ኢትዮጵያውያን የዴሞክራሲያዊ ስርዓተ ማኅበር ግንባታ እንዲጀመር መጠየቅ ከጀመሩ ግማሽ ምዕተ ዓመት ገደማ ሆኗቸዋል። ከግማሽ ምዕተ ዓመት በኋላ ኢትዮጵያ በሕግ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ብትከተልም ቅሉ፥ በተግባር ግን ገና አፍላ እርምጃ ላይ ትገኛለች። ዴሞክራሲያዊነት የብዙኃን ይሁንታ ያለው፣ የኅዳጣን መብቶች የሚከበሩበት፣ በየጊዜው እንደብዙኃኑ ፈቃድ እና ፍላጎት እየተሻሻለ የሚሔድ መንገድ ነው። በመሆኑም የኢትዮጵያን የዴሞክራሲያዊነት ሒደት መከታተል፣ መሰነድ እና ማወጅ እየተሻሻለ መሔዱን ለማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ ነው።

የተለያዩ ዓለም ዐቀፍ ተቋማት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ከሌሎች ሉዓላዊ አገሮች ጋር በማወዳደር በየዓመቱ ምዘናዎቻቸውን ያትማሉ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵዮጵያ ፌዴራላዊ ስርዓት ውስጥ የራሳቸው ሕገ መንግሥት፣ ምክር ቤት፣ ካቢኔ፣ የፀጥታ አካል፣ ፍርድ ቤት እና ሌሎችም ተቋማት ያላቸው የክልል መስተዳድሮች በየዓመቱ ምን ዓይነት ዴሞክራሲያዊነትን የመገንባት ሥራ እየሠሩ እንደሆነ የሚመዘኑበት ልምድም ዕድልም እምብዛም የለም።

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) 'አውራምባ ጠቋሚ' (Awaramba Index) በማለት የሰየመውን የክልል እና የፌዴራል ከተማ መስተዳድሮችን ዓመታዊ የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምዘና ማዘጋጀት የጀመረው ይህንን ክፍተት ለመሙላት በማሰብ ነው።

'አውራምባ ጠቋሚ' በየዓመቱ በሚደረግ ምዘና፣ የክልል እና የፌዴራል ከተማ መስተዳደሮች በስድስት የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች እና በሥራቸው በተዘረዘሩ አምስት፣ አምስት (በድምሩ 30) መገለጫዎች አማካይነት የዴሞክራሲያዊነት ሒደትን ይመዝናል። በምዘናውም ውጤት መሠረት መስተዳድሮቹ ደረጃ የሚሰጣቸው ሲሆን፥ ይህም በየዓመቱ በሚያገኙት ነጥብ መስተዳድሮቹ ራሳቸውን ከራሳቸው ያለፈ እርምጃ አንፃር፣ እንዲሁም ከሌሎች ክልሎች አንፃር የማወዳደር ዕድል ያገኛሉ። የጠቋሚው ድምርም ከአንድ እስከ ዘጠኝ ተሰናኝቶ መስተዳድሮቹ "አሉታዊ"፣ "ግትር" እንዲሁም "ተራማጅ" በተሰኙ ሦስት ምድቦች የዴሞክራሲያዊነት ሒደታቸው ጥቅል ምዘና ይቀመጣል። ካርድ ይህ ልምድ መስተዳድሮቹ ዘንድ የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ላይ አዎንታዊ ሚና እንዲጫወቱ ጋባዥ ነው ብሎ ያምናል።

'አውራምባ ጠቋሚ' ሥያሜውን የተዋሰው ከአውራምባ ማኅበረሰብ ነው። የአውራምባ ማኅበረሰብ በደቡብ ጎንደር ዞን፣ ፎገራ ወረዳ የሚገኝ ከ400 በላይ ነዋሪዎች ያፈራ ማኅበረሰብ ነው። አውራምባ ዙምራ ኑሩ በተባሉ ግለሰብ አስተባባሪነት በ19 ሰዎች በ1970ዎቹ መጀመሪያ ገደማ የተቆረቆረ መንደርና ማኅበረሰብ ነው። በካርድ በኩል

ጠቋሚውን በአውራምባ ለመሠየም ውሳኔ ላይ የተደረሰው፣ የማኅበረሰቡ ፖለቲካዊ፣ ባሕላዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተዳደርን መልሶ የመቅረፅ ተሞክሮ፣ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ ባሕል በዴሞክራሲያዊ ስርዓተ ማኅበር መልሶ እንዲዋቀር ለሚደረገው ንቅናቄ ትምህርት ይሰጣል በሚል ስለታመነበት ነው።

'የአውራምባ ጠቋሚ' አዘገጃጀትን የሚመራ ሥነ ዘዴያዊ መመሪያ ተዘጋጅቷል። ሥነ ዘዴያዊ መመሪያው ከተዘጋጀ በኋላ የሙከራ ምዘና በአራት ክልሎች ላይ በ2014 ዓመት የተደረገ ሲሆን፥ በሙከራ ምዘናው ወቅት የተገኙ ግብዓቶች ላይ ተመሥርቶ ይፋዊ የ2015 ዓመት ምዘና ተደርጓል። የዘንድሮው (ማለትም የ2015 ዓመት) የነበረው የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምዘና የተከናወነው ለስድስት ክልሎች ብቻ ነው። ካርድ ምዘናውን በስድስት ክልሎች ብቻ ለመወሰን የተገደደው በአንድ በኩል በሀብት ውሱንነት ሳቢያ ሲሆን፣ በሌላ በኩል የፀጥታ ሁኔታ እና የክልሎች በሕዝበ ውሳኔ መፍረስ እና መፈጠር በዓመቱ ለምዘና የማይመቹ ክልላዊ መስተዳድሮች እንዲኖሩ ስላደረገ ነው። በሚቀጥሉት ዓመታት ምዘናዎች ሁሉንም ክልሎች ለማካተት ሙከራ ይደረጋል። በዚህም ሒደት፣ የመስተዳድሮቹ የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምዘና የሚመራበት ሥነ ዘዴ በዓየመቱ በሚገኙ ሙያዊ እና ተግባራዊ ግብዓቶች እየዳበረ እንዲሔድ ይደረጋል።

ይህ የመጀመሪያው 'አውራምባ ጠቋሚ' ነው። ጠቋሚው የመጀመሪያውን ይፋዊ ክትትል፣ ስነዳ እና እወጃ እውን ለማድረግ በርካታ ባለሙያዎች እና የካርድ ባልደረባዎች ከሁለት ዓመታት በላይ ሠርተዋል። በዚህም የሥነ ዘዴ መመሪያውን ያዘጋጁት አማኑኤል ተስፋዬ እና ዶ/ር ዮናስ አሸኔ፣ የ2014 ዓመት የሙከራ ምዘናውን በመሥራት የሥነ ዜዴዎች መፈተሻ እና ማሻሻያ ግብዓት የሰጡት ዶ/ር ኢዛና አምደወርቅ፣ የሙከራ ምዘናው በሁለት ክልሎች ብቻ ሊከናወን ታቅዶ ሳለ በአራት ክልሎች እንዲከናወን የፋይናንስ እገዛ ያደረገው ሲቪል ራይትስ ዲፌንደርስ፣ የ2015 ዓመቱን ምዘና ዓይነተኛ እና አሐዛዊ ትንታኔዎችን የሠሩት ብሩክ አብዱ እና ማሕሌት ፋንታሁን፣ እንዲሁም በምዘናው ላይ የተሳተፉ የጭብጥ እና ክልል-ተኮር ባለሙያዎች በሙሉ ለአውራምባ ጠቋሚ እውን መሆን ላበረኩት አስተዋፅዖ ምስጋና ይገባቸዋል።

በተጨማሪም 'የአውራምባ ጠቋሚ' ከተፀነሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ መጀመሪያው እወጃ ይፋ መሆን ድረስ የፋይናንስ እና የቴክኒክ ድጋፍ የሰጠው ፍሪደም ሀውስ የተለየ ምስጋና ይገባዋል።

በመጨረሻም፣ ክልላዊ እና የፌዴራል ከተማ መስተዳድሮች፣ ሕዝባዊ የዴሞክራሲ ተቋማት፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ መገናኛ ብዙኃን እና ሌሎችም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊነት እንዲሰፍን የሚሠሩ ተቋማት 'የአውራምባ ጠቋሚን' ምዘና ላይ የተስተዋሉትን ለዴሞክራሲያዊነት ማነቆ የሆኑ ሁነቶችን በመለየት የሙገታ ሥራችንን እንዲቀላቀሉ ካርድ የተለመደ ግብዣውን ያቀርባል።

**በፍቃዱ ኃይሉ፣**
**የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) ዋና ዳይሬክተር፡፡**

# ማጠቃለያ

'አውራምባ ጠቋሚ' የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) አባል ክልላዊ መስተዳድሮችን ዴሞክራሲያዊነት የማስፈን ሒደትን የክትትል፣ ስነዳ እና እወጃ (monitoring, documentation, and reporting) የሚያከናውንበት ዓመታዊ ፕሮጀክት ነው። የ2015 'አውራምባ ጠቋሚ፤ የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምዘና' ስድስት ክልሎች እያንዳንዳቸው በአምስት የዴሞክራሲ ባሕሪዎች ሥር ባሉ 25 መገለጫዎች የተመዘኑበት ነው። እነዚህ ክልሎች የተመረጡት ከጊዜ፣ ከተደራሽነትና ከሌሎች ነባራዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች አንፃር ሲሆን፥ የተመረጡት ክልሎች አገራዊ ብዝኃነትን እንዲያንፀባርቁ ጥረት ተደርጓል።

ክልሎቹንና የመለኪያ መሥፈርት የሆኑ ጭብጦችን በአግባቡ ከሚረዱ 54 ባለሙያዎች መረጃዎቹ የተሰበሰቡ ሲሆን፥ እነዚህ መረጃዎች ዓይነታዊና አሐዛዊ ናቸው። እነዚህ መረጃዎች አስቀድሞ በተዘጋጀ የጥናት ሥነ ዘዴ መሠረት የተተነተኑ ሲሆን፥ አሐዛዊ መረጃዎቹ የሚያሳዩት ነጥብ በምን ዓይነት ዐውድና መረጃ መሠረት ነው የሚለውን የሚጠቁሙ ዓይነታዊ ሐተታዎችም በእያንዳንዱ ማሳያ ሥር ተቀምጠዋል። ከዚህ በተጨማሪም የክልሎቹን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ሁለተኛ የመረጃ (secondary sources) ምንጮችም ጥቅም ላይ ውለዋል። እነዚህም ሕጎች፥ ጥናቶችና የመገናኛ ብዙኃን ዘገባዎች ናቸው። የተሰበሰበው አሐዛዊ መረጃም በተቀናጀ ድምር ከአንድ እስከ ዘጠኝ ባለ የተሰናኘ ልኬት ተቀይሮ ክልሎቹ ባገኙት ውጤት መሠረት 'ተራማጅ' (አረንጓዴ ወይም ይሁንታ የሚገባቸው)፣ 'ግትር' (ቢጫ ወይም በጥንቃቄ መታየት ያለባቸው) እንዲሁም 'አሉታዊ' (ቀይ ወይም ፍፁም ተቀባይነት የሌላቸው) በተሰኙ ምድቦች ተለይተዋል።

በዚህም መሠረት የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት አንዱ ክልላዊ መስተዳድር በአንዱ የዴሞክራሲ ባሕርይ የተሻለ አፈፃፀም ቢያሳይም፥ በሌሎቹ ደግሞ ደካማ ሆኖ እናገኘዋለን። በተጨማሪም ለእያንዳንዱ የዴሞክራሲ ባሕርያት ማሳያዎች በሆኑ መገለጫዎች መካከልም የነጥብ ልዩነቶች ታይተዋል።

በተሰበሰበው መጠይቅ መሠረት ሲዳማ 4.95 ከዘጠኝ በማግኘት ከፍተኛ የተሰናኘ ድምር ውጤት ሲያስመዘግብ፥ ኦሮሚያና አዲስ አበባ 4.59 በማስመዝገብ ሁለተኛ ሆነዋል። በመቀጠልም አማራ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ጋምቤላ ክልሎች በተከታታይ 4.30፣ 4.03 እና 3.80 የሆኑ በዝቅተኛነት የተሰናኙ ነጥቦችን አስመዝግበዋል። ይሁን እንጂ ስድስቱም ክልላዊ መስተዳድሮች በአውራምባ ጠቋሚ ድምዳሜ ከ3 እስከ 6 ነጥብ ያለው ምድብ ውስጥ በማረፍ 'ግትር' ተሰኝተዋል፤ ይህም የዴሞክራሲያዊነት ጥረታቸው ባለበት የቆመ ነው የሚል ትርጉም ይሰጣል።

ከዚህ በተጨማሪም፥ የምርጫና የፖለቲካ ብዝኃነትን ለመለካት በምዘናው ስነ ዘዴ የተቀመጠው መለኪያ በክልሎችና በተማ መስተዳድሮች የምርጫ ሒደት ያለመኖሩን ከግምት በማስገባት አሐዛዊ መረጃዎች በዚህ ምዘና ጥቅም ላይ ያልሆኑ ሲሆን፥ ይህ መመዘኛ በአሐዝ ገብቶና ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች ተመዝነውበት ቢሆን ኖሮ፥ ነጥብ የሚጥሉ ስለሚኖሩ በክልሎችና በከተማ መስተዳድሮች መካከል ልዩነት ሊፈጠር ይችል ነበር። ይህንንም በሐተታ ከቀረበው የክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የፖለቲካ ብዝኃነት መረጃ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መረዳት ይቻላል።

ከስድስቱም ክልሎች 'ተራማጅ' የተሰኘ አለመኖሩ ለዴሞክራሲያዊነት አዎንታዊና ተግባራዊ ጥረቶች አለመኖራቸውን የሚያመላክት ሲሆን፥ 'አሉታዊ' የተሰኙ ያለመኖራቸውም ምክንያት በዋነኝነት በስድስቱም ክልላዊ መስተዳድሮች መሠረታዊ የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች መገለጫዎች የሆኑ የሕግ ማዕቀፍና ፖሊሲዎች በመኖራቸው ነው።

'በአውራምባ ጠቋሚ' የዴሞክራሲያዊነትን ሒደት መመዘኛ ሥነ ዘዴ ከተለዩት የዴሞክራሲ ባሕሪዎች አንፃር "የኀዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ" ምዘናው በተካሔደባቸው ስድስቱ ክልሎች ውስጥ በአምስቱ የተሻለ ሆኖ የታየበት ሲሆን፥ "የመንግሥት ውጤታማነት" ባሕሪ ደግሞ በአምስት ክልሎች ዝቅተኛ ደረጃ የተመዘገበበት ነው። ለዴሞክራሲያዊነት ባሕርይዎቹ ከተቀመጡ መገለጫዎች ውስጥ ከሁሉም ክልል ዝቅተኛ የሆነ ደረጃ ያገኘው መገለጫ በመንግሥት ውጤታማ ባሕሪ ሥር ያለው "የፀረ-ሙስና ውጤታማነት" መገለጫ ሲሆን፥ ከፍተኛውን ያገኘው ደግሞ በዜግነት ነጻነቶች ባሕሪ ሥር ያለው "የሃይማኖት ነፃነት" የተሰኘው መገለጫ ነው።

| ደረጃ | መስተዳድር | የመንግሥት ውጤታማነት | ቁጥጥር እና ሚዛን | ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | የዜግነት ነጻነቶች | የኀዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | የተሰናኘ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሲዳማ | 2.49 | 2.58 | 2.78 | 3.33 | 3.69 | 4.95 |
| 2 | ኦሮሚያ | 1.96 | 3.04 | 2.96 | 2.78 | 3.24 | 4.59 |
| 3 | አዲስ አበባ | 2.36 | 3.16 | 2.64 | 3.09 | 2.73 | 4.59 |
| 4 | አማራ | 2.07 | 2.64 | 2.44 | 2.40 | 3.69 | 4.30 |
| 5 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 2.24 | 2.07 | 2.71 | 2.49 | 3.07 | 4.03 |
| 6 | ጋምቤላ | 2.00 | 2.16 | 2.27 | 2..73 | 2.96 | 3.84 |
| **አማካይ ድምር** | | **2.19** | **2.61** | **2.63** | **2.80** | **3.23** | |

አጠቃላይ የተሰናኘው ውጤት መግለጫ፤ በዚህም ሲዳማ ከፍተኛ የምዘና ነጥብ፣ ጋምቤላ ዝቅተኛ የምዘና ነጥብ ቢያገኙም፣ ሁሉም የተመዘኑ ክልላዊ እና ከተማ መስተዳደሮች "ቢጫ" ወይም "ግትር" ምድብ ውስጥ በማረፋቸው አንዳቸው አዎንታዊ የዴሞክራሲያዊነት ሒደት እመርታ በ2015 አላስመዘገቡም።


1

# መግቢያ

‘አውራምባ ጠቋሚ’ የኢፌዴሪ ክልላዊ እና የፌዴራል ከተማ መስተዳድሮችን የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ለመመዘን የተጠቀመበት ሥነ ዘዴያዊ መመሪያ የተለያዩ ዓለም ዐቀፍ እና ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው መመዘኛዎች ልምድ በመቅሰም እና ከአገራዊ ዐውድ ጋር በማቀናጀት የተዘጋጀ ነው።

‘የአውራምባ ጠቋሚ’ የሥነ ዘዴ መመሪያም የዴሞክራሲን አረዳድ ከተለያዩ ምንጮች በማጣቀስ እና ከኢትዮጵያ ዐውድ ጋር በማጣጣም፣ የመመዘኛ ባሕሪዎችን እና መገለጫዎችን አስቀምጧል። ለዚህም መነሻ ይሆን ዘንድ ዴሞክራሲዊነት የሒደትና የተጨባጭ አላባዊያን ጥምር ነው የሚለውን ብየና እንደ መነሻ ተቀብሎታል። ይህ ብየናም የተመረጠበት ምክንያት፥ የዴሞክራሲ አረዳድ ከአካሔድ አላባዎች (procedural elements) ባለፈ ተጨባጭ አላባዎችን (substantive elements) የሚገልጽ መሆን እንዳለበት ታሳቢ በማድረግ ነው። ‘የአውራምባ ጠቋሚ’ የክልላዊ እና የፌዴራል ከተማ መስተዳድሮችን ዓመታዊ የዴሞክራሲያዊነት ሒደት የሚመዝንባቸው ባሕሪዎች ለሁለቱም ‘አካሔዳዊ’ እና ‘ተጨባጭ’ አላባዎች እኩል ትኩረት እንዲሰጥ ተደርጓል።

መግለጫ 1. የአውራምባ ጠቋሚ የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች፤ የመመዘኛው ፅንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ




ይህንን ፅንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ በመጠቀም ‘አውራምባ ጠቋሚ’ በሥነ ዘዴው መመሪያ በስድስቱ ባሕሪዎች ሥር ዝርዝር መገለጫዎችን “በሰንጠረዥ 1” እንደተመለከተው ለይቷል።

| | አላባዎች | ባሕሪዎች | መገለጫዎች |
|---|---|---|---|
| ዲሞክራሲያዊነት | አካሔዳዊ | ምርጫና የፖለቲካ ብዝኃነት | ሁሉን አካታች እና እኩል ድምፅ የመጠት መብት |
| | | | የምርጫዎች ተዓማኒነት |
| | | | የገንዘብ እና የቅስቀሳ ዘመቻ ዕድሎች |
| | | | ፉክክር የሚታይባቸው ምርጫዎች |
| | | | የአካባቢ የምርጫ ሕጎች ፍትሐዊነት |
| | | የመንግሥት ውጤታማነት | የሕግ አውጪው ውጤታማነት |
| | | | የሥራ አስፈፃሚው ውጤታማነት |
| | | | የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ውጤታማነት |
| | | | የፀረ-ሙስና ውጤታማነት |
| | | | ያልተማከለ አስተዳደር |
| | | ቁጥጥር እና ሚዛን | የሕግ አውጪው ሥልጣን |
| | | | የፍርድ ቤት ነፃነት |
| | | | የፍርድ ቤት ገለልተኝነት |
| | | | ነፃ ሚዲያ |
| | | | ተሟጋች ቡድኖች |
| | ተጨባጭ | የዜግነት ነፃነቶች | ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት |
| | | | የመደራጀት ነፃነት |
| | | | የሃይማኖት ነፃነት |
| | | | የመንቀሳቀስ ነፃነት |
| | | | የግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ |
| | | ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | መሠረታዊ ፍላጎቶች |
| | | | የትምህርት መብት |
| | | | የስርዓተ ፆታ እኩልነት |
| | | | የግል ንብረት ጥበቃ |
| | | | የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ |
| | | የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | የኅዳጣን ብሔረሰቦች ነጻነት |
| | | | የኅዳጣን መብቶች |
| | | | የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ |
| | | | ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር |
| | | | የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት |

**ሰንጠረዥ 1:** የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምዘና የሦስት ደረጃ ክፍፍል

በእነዚህ ባሕሪዎች እና መገለጫዎች ላይ ተመሥርቶም የመመዘኛው ቀዳሚ የመረጃ መሰብሰቢያ የሆነው መጠይቅ ተዘጋጅቷል። ስለመጠይቁና ስለ ሌሎች የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችና ዘዴዎች ቀጥሎ ተብራርቷል። በመጠይቁና በአተኳሪ የቡድን ውይይቱ እንዲሁም በጠረጴዛ ላይ የመረጃ ማሰባሰብ ሥራዎች የተገኙ መረጃዎች በእያንዳንዱ ጠቋሚ ሥር በአጭሩ ቀርበዋል።

# 2

# የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ



በጥናቱ የሥነ ዘዴ መመሪያ በግልጽ እንደተመላከተው፣ ይህንን መመዘኛ ለመሥራት ቀዳሚው መጠይቅ ሲሆን፥ ለእያንዳንዱ ክልል ይህንን መጠይቅ የሚሞሉ ከ19-22 ሰዎች ይኖራሉ። ይህም፥ ለእያንዳንዱ ክልል ክልሉን በውል የሚረዱ ከሰባት (7) እስከ 10 ክልል-ተኮር ባለሙያዎች የሚመረጡና መጠይቁን እንዲሞሉ ይደረጋሉ ማለት ነው። በተጨማሪም፥ ለስድስቱ መገለጫዎች እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት የጭብጥ ባለሙያዎች (Thematic Experts) ይመረጡና ሁሉንም ክልሎች ዕውቀት ባላቸው የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ መገለጫዎች ላይ ብቻ ምላሽ ይሰጣሉ። የጭብጥ ባለሙያዎች ተከፋፍለው የሚሞሉት መጠይቅ በድምሩ ለአንድ ክልል ሁለት ብቻ ሲሆን፥ ክልል-ተኮር ባለሙያዎች ደግሞ የሚመዝኑትን ክልል በሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪዎች መገለጫዎች ይመዝናሉ። በክልል-ተኮር ባለሙያዎች የሚሞላው መጠይቅ ከሰባት (7) እስከ 10 ሊደርስ ይችላል። በ2015 አውራምባ ጠቋሚ፣ ለእያንዳንዱ ክልል የተመረጡ ክልል-ተኮር ባለሙያዎች ሰባት ሲሆኑ፥ በድምሩ በ12 የጭብጥ ባለሙያዎች የተሞሉት ሁለት መጠይቆች ሲደመሩባቸው ለእያንዳንዱ ክልል ዘጠኝ መጠይቆች ተሞልተዋል።

> **በዚህ መመዘኛ በጠቅላላው 54 የጭብጥ እና ክልል-ተኮር ባለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን፥ በድምሩ 54 መጠይቆች ተሞልተዋል::**
>
> **እያንዳንዱ የዴሞክራሲ ባሕሪ አምስት መገለጫዎች አሉት:: እነዚህ መገለጫዎች እያንዳንዳቸው የሚለኩት ከ5 ነጥብ ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ 1 ነው:: ለእያንዳንዱ መስተዳደር የተሞሉት መጠይቆች ቁጥር 9 ሲሆን እያንዳንዱ መገለጫ በድምሩ ሊያገኝ የሚችለው ከፍተኛ ውጤት 45 (=5*9) ፥ ዝቅተኛው ውጤት ደግሞ 9 (=1*9) ነው:: እያንዳንዱ ባሕሪ ደግሞ ሊያገኝ የሚችለው ከፍተኛ ነጥብ 225 (=5*45) እንዲሁም ዝቅተኛ ነጥብ 45 (=5*9) ነው::**

ከመጠይቁ አሐዛዊ መረጃዎች በተጨማሪ፥ መጠይቁን የሞሉት ባለሙያዎች ለእያንዳንዱ ጠቋሚ ከአንድ እስከ አምስት (ከ1-5) ደረጃ ከመስጠታቸው አስቀድሞ በክልሉ ያንን ርዕሰ ጉዳይ የተመለከቱ ክስተቶችንና የሕግ ማዕቀፎችን የሚዳስስ ውይይት በእያንዳንዱ መገለጫ ርዕሰ ጉዳይ ተደርጓል። ይህም ውይይት ለእያንዳንዱ ክልል አንድ ቀን በመውሰድ ከመስከረም 7-12 ቀን 2016 በአዲስ አበባ የተደረገ ሲሆን፥ የዴሞክራሲያዊ ሒደቱ ምዘና ዓይነታዊ የመረጃ ምንጭም በመሆን አገልግሏል። በተጨማሪም፥ በሐተታው ለሚቀርቡ ሐሳቦች ማጣቀሻና የሐቅ ማረጋገጫ (verification) ሆኖ እንዲያገለግል መጠነኛ የሁለተኛ ምንጭ ዳሰሳ ተደርጓል። የቡድን ውይይቶች የተደረጉባቸው ቀናት መዘርዝር በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመላክቷል።

| ክልል/ከተማ መስተዳደር | ቀን |
|---|---|
| **አዲስ አበባ** (የቡድን ውይይት 1) | መስከረም 7 |
| **ኦሮሚያ** (የቡድን ውይይት 2) | መከስረም 8 |
| **አማራ** (የቡድን ውይይት 3) | መስከረም 9 |
| **ሲዳማ** (የቡድን ውይይት 4) | መስከረም 10 |
| **ቤኒሻንጉል ጉሙዝ** (የቡድን ውይይት 5) | መስከረም 11 |
| **ጋምቤላ** (የቡድን ውይይት 6) | መስከረም 12 |

**ሰንጠረዥ 2:** ለዓይነተዊ መረጃዎች ግብዓት የሆኑ የቡድን ውይይቶች የተካሔዱባቸው ቀናት

የባለሙያዎች መረጣ የተከናወነው አስቀድሞ በተቀመጠ መስፈርት አማካይነት በይፋ በተደረገ ጥሪ ሲሆን፥ የፍላጎትና የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ (ከተመረጡት ክልሎችና ከርዕሰ ጉዳዮቹ ጋር ያላቸውን ትስስር) መረጃ ለማሰባሰብ ተሞክሯል። በዚሁ መሠረት፣ ለሥራው ብቁ ናቸው ተብለው የታመኑ ባለሙያዎች በመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) ባለሙያዎች አማካይነት ተመልምለዋል።

በዚህም መሠረት ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር፣ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሲዳማ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ እና ጋምቤላ ክልላዊ መስተዳድሮች እያንዳንዳቸው ሰባት የክልል ባለሙያዎች እንዲሁም ለሁሉም ክልሎች 12 የጭብጥ ባለሙያዎች እንዲሳተፉና መረጃ እንዲሰጡ ተደርጎ በውጤቱ መሠረት የሚከተለው ሐተታ ተሰንዷል።

ይሁንና፥ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴው ከመመዘኛው ስነ ዘዴ የሚመነጭ ውሱንነት ተስተውሎበታል። ይህም ምርጫ በአገር አገር አቀፍ ደረጃ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም ለክልልና ከተማ መስተዳድሮች በየአምስት ዓመታት የሚከናወን ሲሆን፥ በየዓመቱ ለሚደረግ መለኪያ የምርጫ ሒደት የመመዘኛ መስፈርት መሆኑ ክፍተትን ፈጥሯል። የአካባቢ ምርጫዎችና ሕዝበ ውሳኔዎችም እኩል በሁሉም የፌዴሬሽኑ አባል ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የሚደረግ ባለመሆኑ፥ መመዘኛው ወጥ እንዳይሆን አድርጎታል። ይህም የምዘናው ውሱንነት ነው።

| | | የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ባ1<br>ምርጫና የፖለቲካ ብዝኃነት | ባ2<br>የመንግሥት ውጤታማነት | ባ3<br>ቁጥጥር እና ሚዛን | ባ4<br>የዜግነት ነፃነቶች | ባ5<br>ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | ባ6<br>የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ |
| የባሕሪዎቹ መገለጫዎች | መ1 | ባ1መ1፡<br>ሁሉን አካታች እና እኩል ድምፅ የመጠት መብት | ባ2መ1፡<br>የሕግ አውጪው ውጤታማነት | ባ3መ1፡<br>የሕግ አውጪው ሥልጣን | ባ4መ1፡<br>ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት | ባ5መ1፡<br>መሠረታዊ ፍላጎቶች | ባ6መ1፡<br>የኅዳጣን ብሔረሰቦች ነጻነት |
| | መ2 | ባ1መ2፡<br>የምርጫዎች ተዓማኒነት | ባ2መ2፡<br>የሥራ አስፈፃሚው ውጤታማነት | ባ3መ2፡<br>የፍርድ ቤት ነፃነት | ባ4መ2፡<br>የመደራጀት ነፃነት | ባ5መ2፡<br>የትምህርት መብት | ባ6መ2፡<br>የኅዳጣን መብቶች |
| | መ3 | ባ1መ3፡<br>የገንዘብ እና የቅስቀሳ ዘመቻ ዕድሎች | ባ2መ3፡<br>የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ውጤታማነት | ባ3መ3፡<br>የፍርድ ቤት ገለልተኝነት | ባ4መ3፡<br>የሃይማኖት ነፃነት | ባ5መ3፡<br>የስርዓተ ፆታ እኩልነት | ባ6መ3፡<br>የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ |
| | መ4 | ባ1መ4፡<br>ፉክክር የሚታይባቸው ምርጫዎች | ባ2መ4፡<br>የፀረ-ሙስና ውጤታማነት | ባ3መ4፡<br>ነፃ ሚዲያ | ባ4መ4፡<br>የመንቀሳቀስ ነፃነት | ባ5መ4፡<br>የግል ንብረት ጥበቃ | ባ6መ4፡<br>ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር |
| | መ5 | ባ1መ5፡<br>የአካባቢ የምርጫ ሕጎች ፍትሐዊነት | ባ2መ5፡<br>ያልተማከለ አስተዳደር | ባ3መ5፡<br>ተሚጋች ቡድኖች | ባ4መ5፡<br>የግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ | ባ5መ5፡<br>የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ | ባ6መ5፡<br>የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት |

**ሰንጠረዥ 3:** መጠይቁ ያካተታቸው የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች እና የባሕሪዎቹ መገለጫዎች (ባ =ባሕርይ፣ መ = መገለጫ)

# 3

# የፖለቲካ ብዝኃነት

በዚህ ክፍል የሚቀርበው ዝርዝር በምዘናው የሥነ ዘዴ መመሪያ የተቀመጡ ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመሸጋገር የሚደረግን ሒደት ለመለካት የሚያገለግሉ ባሕሪዎች እና መገለጫዎች አንዱ አካል ነበር። ነገር ግን ከአምስቱ የባሕሪው መገለጫዎች ቢያንስ ሁለቱ በቀጥታ ከምርጫ ሂደት እና አፈጻጸም ጋር የሚያያዙ በመሆናቸው እና በ2015 የምርጫ ሒደት ባለማኖሩ፣ የባሕሪውን አሐዛዊ ምዘና በማስወገድ ዓይነታዊ ትንታኔው ብቻ ተሰናድቷል።

## የፖለቲካ ብዝኃነት ምዛኔ

'የአውራምባ ጠቋሚ' የምርጫ ፍትሐዊነትን የፖለቲካ ብዝኃነት መመዘኛ ማዕከል ያደርገዋል። ለዚህም አመክንዮው ምርጫና የፖለቲካ ብዝኃነት በመራጮች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ መንግሥት መመሥረት መቻል የዴሞክራሲያዊነት ዋነኛ አላባ ነው የሚል ነው።

በዚህም መሠረት ምዘናው ምርጫንና የፖለቲካ ብዝኃነትን እንደ አንድ የዴሞክራሲያዊ ሒደት ባሕሪ በመውሰድ አምስት መገለጫዎች በመለኪያነት አገልግለዋል። እነዚህም መገለጫዎች ሁሉን አካታችና እኩል ድምፅ የመስጠት መብት መኖር አለመኖርን፣ የምርጫዎች ተዓማኒነትን፣ የምርጫ ገንዘብ ምንጭ እና የቅስቀሳ ዘመቻ ዕድሎችን ፍትሐዊነት፣ ፉክክር የሚታይባቸው ምርጫዎች መኖር አለመኖርን፣ እንዲሁም የአካባቢ ምርጫ ሕጎች ፍትሐዊነትን የሚገመግሙ ናቸው። ሆኖም፣ ከላይ እንደተመላከተው ከእነዚህ መገለጫዎች መካከል ቀጥታ ከምርጫ ሒደቶች ጋር የሚገናኙና የክልሎች የሥልጣን ወሰን አካል ያልሆኑ መገለጫዎች፣ ለዚህ ዓመት ከመመዘኛው መስፈርትነት ተቀንሰዋል። ስለዚህም፣ በዚህ ክፍል የሚቀርበው የክልሎች የፖለቲካ ብዝኃነት ምዘና ይህንን ልየታ ያገናዘበ ነው።

## የፖለቲካ ብዝኃነት በድኅረ ምርጫ 2013 ዐውድ

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ብዝኃነት በሕገ መንግሥቱና በተለያዩ የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲ ሕጎች የተረጋገጠ ሲሆን፥ ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት መገንባትና የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት፣ እንዲሁም ለፖለቲካዊ ዓላማዎች ስብሰባዎችን ማድረግ የተፈቀዱ ናቸው። ነገር ግን የኢትዮጵያ የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲ ሕጎች ምንም እንኳን የአካል ጉዳተኞች አካታችነት እንዲኖር የሚደነግጉና ለምርጫና ለፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ ድጋፍ መስፈርት ተደርጎ ቢቀመጥም፥ በአንቀፅ 18-3 (በአዋጅ 1162/2011) ሥር የተወሰኑ አካል ጉዳተኞችን (በአዕምሮ ሕመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌላቸው) ለይቶ ከምርጫ ያገላል። ይህም ከዓለም ዐቀፍ የምርጫና የአካል ጉዳተኞች መብቶች አንፃር ተፃራሪ አሠራር ሆኖ እናገኘዋለን።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መጋቢት ወር 2010 ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን ሲሰየሙ ቃል ከገቧቸው[01] ጉዳዮች አንዱ አንዱ አሳዳጅ፥ ሌላው ተሳዳጅ የሆነበትን የፖለቲካ ምኅዳር በማስቀረት ሁሉን አካታች የፖለቲካ ስርዓት መዘርጋት አንዱ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለመጀመሪያ ጊዜ በፓርላማ ያደረጉት ንግግር የፖለቲካ ብዝኃነትን ተስፋ በመሰነቁም፥ በፖለቲካ ፓርቲዎች አድናቆት[02] የተቸረው ሲሆን፥ ይህንን ቃል ተስፋ በማድረግ

01 https://www.youtube.com/watch?v=tD7FlzMFQ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
02 https://amharic.voanews.com/a/opposition-reaction-abut-new-ethiopian-pm-4-2-2018/4327763.html (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

በድርድርም ሆነ ያለ ድርድር በውጭ የሚገኙ በትጥቅ ትግል የተሰማሩም ሆነ በስደት የቆዩ ፖለቲከኞችና የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች ወደ አገራቸው ተመልሰዋል[03]። ይሁንና፥ በቁጥር በርካታ የፖለቲካ ፓርቲዎች በኢትዮጵያ ቢኖሩም፥ በተግባር ግን የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ሳይሆን አሀዳዊ የፓርቲ ስርዓት ነው ያለው ብለው የሚከራከሩም አልጠፉም[04]። ለዚህ ክርክር መነሻቸው በ2013 የተደረገው አጠቃላይ ምርጫ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ በክልል ምክር ቤቶች የገዥው ፓርቲ ፍፁም የበላይነት ያሳየ መሆኑን ነው።

በምርጫ 2013 የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰላማዊና ተዓማኒ ምርጫ ለማድረግ በማቀድ በበርካታ የአገሪቱ አካባቢዎች ምርጫ ያከናወነ ሲሆን፥ በቴክኒካል ጉዳዮችና በፀጥታ ሳቢያ በአማራ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በአፋር፣ በኦሮሚያና በቀድሞ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎች በ36 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች ተወካዮች ምርጫዎች ሳይከናወኑ ቀርተዋል።

በዘህም ሳቢያ፥ በተለይ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የክልል ምክር ቤት ለመመሥረት የሚያስችለው ድምፅ ስላልነበረም የቀድሞው የክልሉ አስተዳደር የቀጠለ ሲሆን፥ በፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊኖረው የሚገባውን ውክልናም በተሟላ መልኩ አላገኘም። በተመሳሳይ መልኩ ከጥቅምት 2013 እስከ ጥቅምት 2015 በነበረው የትጥቅ ግጭት ምክንያት በትግራይ ክልል ምርጫ ባለመደረጉ ክልሉ የክልል ምክር ቤትም ሆነ የፌዴራል ሕዝብ ተወከዮች ምክር ቤት አባላት የሉትም።

እንደ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሰኔ 14፥ 2014 ምርጫ ውጤት ሪፖርት፥ በአፋር፣ በአማራ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በጠቅላላው በ48 የምርጫ ክልሎች የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ድምፅ ያልተሰጠ ሲሆን፥ ለክልል ምክር ቤቶች ደግሞ ከ1200 በላይ የምርጫ ክልሎች ድምፅ አልተሰጠም ነበር። በኋላም መስከረም 20 በተከናወነ ምርጫ ከተቀሩት የምርጫ ክልሎች የተወሰኑትድምፅ እንዲሰጡ ተደርጓል።

በዚህ ምርጫ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በክልል ምክር ቤቶች ድምፅ አግኝተው ተወካይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት መታየታቸው በበጎ መልኩ ሊታይ የሚችል የፖለቲካ ብዝኃነት ጅማሮ ነው። በአፋር፣ በአማራ፣ በጋምቤላ፣ እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤቶች የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት መቀመጫዎችን ያሸነፉ ሲሆን፥ በአማራ ክልልና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጥቂት ተቃዋሚዎች የፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫዎችን ማሸነፍ ችለዋል።


ሆኖም ግን፥ በኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሱ እንደ ኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፥ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ)[05]፥ ብሎም በሶማሊ ክልል ምርጫ ለመሳተፍ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ)፥ ነፃነትና እኩልነት ፓርቲና የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ)[06] ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ራሳቸውን ከክልሉ ምርጫው ተራ በተራ ማግለላቸው ለምርጫው ፉክክር ላይ አሉታዊ ገፅታን ሰጥቷል።

03 https://m.facebook.com/ethiopianpressagency/photos/a.504616456356374/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ) 1158340777650602/?locale=hiIN (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
04 https://www.ethiopianreporter.com/119191/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
05 https://www.bbc.com/amharic/news-56318087 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
06 https://www.ethiopianreporter.com/75914/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

የምርጫ ሒደቱ ከተጠናቀቀና መንግሥት ከተመሠረተ ወዲህም፥ በፓርቲዎችና አባላት ላይ ሲደርስ የነበረው ወከባ የፖለቲካ ምኅዳሩ ምን ያህል አዳጋች እንደነበር ማሳያ ነው። በተደጋጋሚ የምርጫ ቦርድ ጣልቃ ገብነትን የጠየቁ የፓርቲ አባላት እስር፣ መሰወር፣ ማዋከብና እንግልቶች[07] እንደነበሩ መታዘብም ተችሏል። ሆቴሎችም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጠቅላላ ጉባዔ ለማድረግ የሚጠይቁትን የስብሰባ አዳራሽ ለማከራየት ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በፓርቲነት ለመቀጠል በሕግ የሚጠበቅባቸውን መስፈርት ለማሟላት በመቸገራቸው የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መንግሥት አዳራሽ ያላቸው ተቋማቱን ለፖለቲካ ፓርቲዎች አዳራሽ እንዲፈቅዱ እስከመጠየቅ[08] ደርሷል።

በኢትዮጵያ አዳዲስ አገር ዐቀፍና ክልላዊ ፓርቲዎች ዕውቅና እያገኙና እየተመዘገቡ ቢሆንም፥ የፖለቲካ ምኅዳሩ የፖለቲካ ብዝኃነትን የሚፈታተን እንደሆነ ተስተውሏል።

# የፖለቲካ ብዝኃነት በስድስቱ ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች



## የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር

የሲዳማ ክልል አዲስ ክልል እንደመሆኑ መጠን የክልል መዋቅሮችን ዘርግቶ የተደላደለ የፖለቲካ ምኅዳር በመፍጠር ረገድ በርካታ ክፍተቶች ይታዩበታል። የሲዳማ የክልልነት ጥያቄ የወለዳቸውም ሆኑ ቀደም ብለው በክልሉ የነበሩ በመደበኛና መደበኛ ባልሆኑ መንገዶች የተደራጁ የተፅዕኖ ፈጣሪ ተቋማት አሁን ላይ ተዳክመዋል። በክልሉ ልዩነቶችን ማስተናገድ ላይ ሰፊ ክፍተቶች በመኖራቸው፥ የሐሳብ ልዩነት ያላቸው ቡድኖች ይገለላሉ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በንቃት እንዳይሳተፉ ይደረጋሉ።[09]

በመገናኛ ብዙኃን ረገድ በክልሉ በስፋት የሚንቀሳቀሱት የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ሲሆኑ፥ የተለያዩ ፖለቲካዊ ሐሳቦችን የሚያንፀባርቁ ሳይሆኑ የመንግሥትን ሐሳብ የሚያስተጋቡና የሕዝብን ጥያቄዎችና ቅሬታዎች እምብዛም የማያስተላልፉ ናቸው። በክልሉ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመገናኛ ብዙኃን ፍላጎታቸው የምርጫ ጊዜያት ላይ ብቻ የሚጎላ ሲሆን፥ ከምርጫ ወቅት ውጪ ባሉ ጊዜያት ሐሳቦቻቸውን የሚያቀርቡበትን መድረክ የመጠየቅ ልምድም የላቸውም[10]። የክልሉ አዲስነትም በክልሉ መገናኛ ብዙኃን ብዝኃነት ያላቸው አይደሉም። የፖለቲካ ፓርቲዎችና የተለየ ሐሳብ አላቸው ተብለው የሚታሰቡ ስብስቦችን የሚወክሉ ግለሰቦች የመገናኛ ብዙኃን ዕድል የሚያገኙት በመንግሥት የሚሠሩ ሥራዎችን (እንደ አረንጓዴ አሻራ) እንዲያደምቁ እንዲሆኑ እንጂ፥ አገራዊና ክልላዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አቋማቸውን እንዲያንፀባርቁ አይደለም።


ጠንካራ አቋም ያላቸውና በክልሉ በነበሩ ፖለቲካዊ ሁነቶች ውስጥ ጉልህ ሚና የተጫወቱ እንደ ሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን) ያሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች በክልሉ መንግሥትና ገዥ ፓርቲ ተደልለው ወደ ገዥው ፓርቲ እንዲታቀፉ[11] መደረጋቸው ለዚህ የፖለቲካ ብዝኃነት ውሱንነት አስተዋፅዖ አድርጓል። ይህ ፓርቲው ከዚህ

07 https://www.bbc.com/amharic/articles/c6pqjr75qzno (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
08 https://t.me/NationalElectionBoardNEBE/874?single (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
09 የቡድን ውይይት 4
10 የቡድን ውይይት 4
11 https://ethio12.com/2021/03/25/2987-10/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

አስቀድሞ ብልጽግና ፓርቲ የሲዳማ ሕዝብ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር የሚፈቅድ ፖሊሲ የለውም[12] ብሎ ከወቀሰው ድርጅት ጋር የተደረገ ቅንጅት በክልሉ በተፈጠረው የፖለቲካ ብዝኃነት ውሱን መሆን አንዱ ማሳያ ነው።

በክልሉ የሚንቀሳቀሱ እንደ ሲዳማ ፌዴራሊስት ፓርቲ (ሲፌፓ) የመሳሰሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በክልሉ ከፍተኛ የሙስናና የአስተዳደር ብልሹነቶች እንዳሉ ሲያሳውቁ[13] የነበረ ሲሆን፥ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎች በወረዳዎች ጽሕፈት ቤቶችን እንዳይከፍቱም ገደቦች አሉባቸው[14]።

## የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መስተዳድር



የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በአገሪቱ ምርጫ ካልተደረገባቸው ሁለት ክልሎች አንዱ ነው። ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጋር ምርጫ ያልተደረገበት ሌላው ክልል የትግራይ ክልል ነው። በክልሉ በአብዛኛው የክልል ምክር ቤት መቀመጫዎች ሆነው፥ በ17 የምርጫ ክልሎችና በ600 የምርጫ ጣቢያዎች[15] ይደረጉ የነበሩ ምርጫዎች በፀጥታና በቴክኒክ ጉዳዮች ተስተጓጉለው እስካሁን ክልሉ በክልል ምክር ቤትና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መወከል የነበረበት ተመራጮችን አላገኘም። ስለዚህም፥ ክልሉ ባልተመረጠ መንግሥት እየተዳደረ ነው።

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዘጠኝ (9) ተወካዮች መወከል ሲገባው፥ በሦስት (3) ተመራጮች ብቻ ነው የተወከለው። በክልል ምክር ቤት ደግሞ ከ99 የክልል መቀመጫዎችተመርጠው ሊወከሉ የቻሉት 28 ብቻ ናቸው።

በክልሉ እኩል የመምረጥና የመመረጥ መብት በሕግ የተጠበቀ ቢሆንም፥ በክልሉ ሕገ መንግሥት የክልሉ ባለቤቶች ተብለው የተቀመጡ ብሔሮች መኖራቸው በክልሉ እኩል ፖለቲካዊ መብቶች ተረጋግጠዋል ለማለት አይቻልም የሚሉ ክርክሮች አሉ[16]። በዚህ ድንጋጌ መሠረት ከመምረጥና ከመመረጥ የተገለሉ አካላት ግን የሉም የሚሉም አልታጡም[17]። ከዚህ ባለፈም፥ በክልሉ ለምርጫ መወዳደር የሚችሉት አምስቱ ብሔሮች ብቻ በመሆናቸው ሌሎች በክልሉ የሚኖሩ ብሔሮች ከግዛት ውጭ የሆነ ራስን የማስተዳደር መብት (non-territorial autonomy) የላቸውምና የፖለቲካ ምኅዳሩ ብዝኃነት የጎደለው ነው የሚል ክርክርም አለ። በሌላ በኩል ደግሞ፥ እነዚህ የክልሉ ብሔሮች በሕግ አስገዳጅነት የሚወከሉበት አሠራር ባይኖር ኖሮ ኅዳጣንን ለመጠበቅ ያስቸግር እንደነበረም የሚከራከሩ አሉ። ሆኖም ግን፥ ይህ ሁኔታ የኅዳጣን አምባገነናዊነትን ሊፈጥር እንደሚችል ሥጋቶች አሉ[18]።

12 https://shorturl.at/dnrx3 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
13 https://addisstandard.com/news-opposition-sidama-federalist-party-decry-alarming-maladministration-corruption-rights-abuse-in-region/፤ https://www.youtube.com/watch?v=EhtAbieTjUI (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
14 የቡድን ውይይት 4
15 https://nebe.org.et/sites/default/files/%E1%8B%A8%E1%8D%80%E1%8C%A5%E1%89%B3%20%E1%88%83%E1%8B%AD%E1%88%8D%20%E1%88%81%E1%8A%94%E1%89%B3.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
16 የቡድን ውይይት 4
17 የቡድን ውይይት 4
18 የቡድን ውይይት 4

በክልሉ ያለው የምክር ቤቶች ውክልና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን፥ በታችኛው መዋቅር ምክር ቤቶች የተሻለ የብሔሮች ውክልና አለ።[19]

ሆኖም ግን፥ ብዝኃነት ያለው የፖለቲካ ምኅዳር ለመፍጠር አስቻይ ሁኔታዎች ከገዥው ፓርቲ ጋር የተቃረነ ሐሳቦች ሲኖሩ ወደ ፊት እንዳይመጡ የመገናኛ ብዙኃን ውሱንነት እና የመምረጥና የመመረጥ ገደቦች ይኖሩባቸዋል[20]። ይህም በክልሉ የሚንቀሳቀሱ እና ከአጎራባች ክልል በመግባት ግጭት ውስጥ የሚሳተፉ ታጣቂዎች በመኖራቸው ለረዥም የቆየ ፀጥታ ችግር፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እና ማስፈፀሚያ ኮማንድ ፖስቶች በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ሕዝቡ ገብተው ውይይት እንዳያደርጉ፣ ጽሕፈት ቤቶችን እንዳያቋቁሙ፣ እንዲሁም አባላትን እንዳያፈሩ ገደቦች ጥለውባቸዋል። ይህንን ለማድረግ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ለእሥርና እንግልት ሲዳረጉ ታይቷል[21]። የቢኒሻንጉል ሕዝቦች ነጻነት ንቅናቄ እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የተባሉ ታጣቂ ቡድኖች በተለያዩ ግዚኤያት ከመንግሥት ጋር በመታረቅ ሰላም ለማውረድ የተደረጉ ጥረቶች ቢኖሩም በእርቆቹ አፈጻጸም ግድፈቶች እና ከሌሎች ክልሎች የገቡ ታጣቂዎች በመኖራቸው የክልሉ ጸጥታ ደፍርሶ በመቆየት የፖለቲካ ምኅዳሩ ከመስፋት ይልቅ የመጠበብ ከፍተኛ አዝማሚያ ታይቶችበታል።

## የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር



እንደ ሌሎቹ ክልሎች ሁሉ የአማራ ክልል ሕገ መንግሥትም በክልሉ ለሚገኙ ዜጎች የመደራጀትና በፖለቲካ የመሳተፍ መብትን ይጠብቃል። በመላ አገሪቱ በማዕከላዊነት ተፈፃሚ የሚሆነው የፌዴራል ሕገ መንግሥት እንዲሁም የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ በአማራ ክልልም ተፈፃሚነት ስላላቸው በሕግ ረገድ በክልሉ የፖለቲካ ብዝኃነት ዕውቅናን አግኝቷል።

በ2015 በአማራ ክልል በተከታታይ በነበሩ የፀጥታ ችግሮች ሳቢያ የፖለቲካ ብዝኃነት የተፈተነበር ዓመት እንደነበር ብዙ ማሳያዎች ያሉ ሲሆን፥ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ ልብ የሚንቀሳቀሱበትና አባላትን የሚያፈሩበት ዐውድም አልነበረም። ከዚህ አንፃር በክልሉ ያለው የፖለቲካ ምኅዳር ጠባብ ሲሆን፥ መገናኛ ብዚኃንን ጨምሮ የፖለቲካ ድርጅቶችና አባላቶቻቸው ሐሳባቸውን የሚገልፁበት መድረክ የለም። ከ2015 አስቀድሞ በነበሩ ጊዜያት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሐሳባቸውን የሚገልጹባቸው ዕድሎች ነበሯቸው፤ የትኛውም የፖለቲካ አስተሳሰብ ያላቸው ቡድኖች በነፃነት ይንቀሳቀሳሉ። በ2015 ግን ይህ ዕድል ተገድቧል።[22] ለዚህ ማሳያውም በክልሉ በ2015 የተቃዋሚ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ እምብዛም መሆኑ ሲሆን፥ የትጥቅ ትግልን ምርጫቸው ያደረጉ ቡድኖች እየተበራከቱ መጥተዋል። ከዚህ ባለፈም፣ የፖለቲካ አመራሮች ስብሰባ በሚያደርጉባቸው ሥፍራዎች በታጣቂዎች ለጥቃት ሲጋለጡም ተስተውሏል።[23]

19 https://grnpp.org/wp-content/uploads/2020/07/Tsegaye-conference-presentation-Amharic.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

20 የቡድን ውይይት 5

21 https://www.dw.com/am/%E1%8B%A8%E1%89%A4%E1%88%95%E1%8A%90%E1%8A%95-%E1%8D%93%E1%88%AD%E1%89%B2-%E1%8A%A8%E1%8D%8D%E1%89%B0%E1%8A%9B-%E1%8A%A0%E1%88%98%E1%88%AB%E1%88%AD-%E1%8A%A5%E1%88%B5%E1%88%AD/a-66738096 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)


22 የቡድን ውይይት 5

23 https://ethiopiainsider.com/2023/11085/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከገዥው ፓርቲ ጋር እንዲሠሩ የቀረበላቸውን ጥሪ ተቀብለው የክልልና የፌዴራል መንግሥት ኃላፊነቶችን መውሰዳቸው በፓርቲዎቹ መካከል ክፍተቶችን በመፍጠሩ፥ ጠንካራ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ እንዳይኖር አስተዋፅዖ አድርጓል። ይህም በክልሉ የተለያዩ ሐሳቦች እንዳይንፀባረቁ ማድረጉንና ገዥው ፓርቲ ብቻ የሐሳብ መድረኩን እንዲቆጣጠር ረድቶታል።[24]

በአማራ ክልል የሚገኙ አልያም ክልሉ ላይ ትኩረት አድርገው የሚሠሩ የመገናኛ ብዙኃን ድርጅቶች የሐሳብ ብዝኃነትን የማያስተናግዱ፥ ለተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች እኩል ዕድል የማይሰጡና ዋልታ ረገጥነት የሚታይባቸውም ናቸው[25]።

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር



የአዲስ አበባን የፖለቲካ ብዝኃነት የሚገዛው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ውስጥ የተጠበቁ የመደራጀት ነጻነቶች ሲሆኑ፣ ዝርዝር አዋጆችም ተፈፃሚ ይሆናሉ። በኢትዮጵያ በአገር ዐቀፍ ፓርቲነት ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች[26] አዲስ አበባን ማዕከል አድርገው የሚሠሩ ሲሆን፥ ይህም በአዲስ አበባ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥር በርካታ እንዲሆን አድርጎታል። ይሁንና፥ የፖለቲካ ፓርቲዎች በከተማይቱ የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች በስፋት የተገደቡ ከመሆናቸው አኳያ ይህ የፓርቲዎች ቁጥር ትርጉም ያለው የዴሞክራሲያዊነት አስተዋጽዖ እንዳይኖረው ሆኗል። የፖለቲካ ፓርቲዎችም ለወከባ ይዳረጋሉ[27]።

የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሕዝባዊ የገንዘብ ማሰባሰብ ላይ በርካታ እንቅፋቶች ይገጥሟቸዋል - ለፓርቲዎች ገንዘብ የሚሰጡም ጫና ይደርስብናል ብለው ይሰጋሉ። በተቃራኒው ገዥው ፓርቲ የመንግሥትን ሀብት በገንዘብም በንብረትም እንዳሻው ይጠቀማል።[28]

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 30 ማንኛውም ግለሰብ በሰላማዊ መንገድ መሣሪያ ሳይታጠቅ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ እንደሚችል የተደነገገ ሲሆን፥ በ1983 የወጣው አዋጅ ቁጥር 3/1983 እንዲሁም የማንኛውንም ግለሰብ ሰላማዊ ሰልፍና የፖለቲካ ስብሰባዎችን የማዘጋጀትና የመሳተፍ መብቶች እንዳሉት የሚደነግግ ቢሆንም፥ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ግን በተግባር አዳጋች እንደሆነ፥ ከዓለም ዐቀፍ ሥምምነቶች ጋር የማይጣጣሙ አሠራሮችና ድንጋጌዎችም እንዳሉ ጥናቶች ያሳያሉ[29]።


በእነዚህም ምክንያቶችና በተለያዩ ፖለቲካዊ ፍላጎቶች ሳቢያ፥ በ2015 በአዲስ አበባ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ በተግባር አይቻልም ነበር[30]። በተጨማሪም የፖለቲካ ፓርቲዎች የመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀምም የተገደበ ሲሆን፥ "ፍትሐዊ

24 የቡድን ውይይት 5
25 የቡድን ውይይት 5
26 https://nebe.org.et/sites/default/files/List%20of%20Registered%20Political%20Parties%20Amharic%20%26%20English%20Final.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
27 የቡድን ውይይት 1
28 የቡድን ውይይት 1
29 http://etd.aau.edu.et/bitstream/handle/123456789/16746/Yenatfanta%20Eskindir.pdf?sequence=1&isAllowed=y (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
30 የቡድን ውይይት 1

"የሚዲያ ተደራሽነት የላቸውም።" ከዚህ ባለፈም፥ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አባላት ወደ ሚዲያ ሲቀርቡ እንዲናገሩ የሚደረጉት "የመንግሥትን መልካም ገፅታ የሚያጎሉ ጉዳዮችን እንጂ ለራሳቸው ሐሳብ ለማቅረብ አይደለም።"[31]

ከዚህ በተጨማሪም፥ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ በከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤት የምትመረጥ አለመሆኗ በምርጫ ሒደቱ ላይ የተለያዩ ሐሳቦች እንዳይፋጩ በማድረግ የፖለቲካ ብዝኃነት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል።[32]

## የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር



የምርጫ ሕጎችና የምርጫ ሥራዎች በሙሉ ማዕከላዊ ሲሆኑ፥ በኦሮሚያ የምርጫና የፖለቲካ ብዝኃነትን የሚገዛው ስርዓት ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ክልሎች ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ሆኖም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴና የመደራጀትና በሰላማዊ ሰልፍ ጥያቄ የመጠየቅ ሁኔታዎች ክልላዊ ዐውድ ይኖራቸዋል። ከዚህ ጋር በተገናኘም በምርጫ 2013 ገዥው የብልፅግና ፓርቲ በኦሮሚያ ክልል ከ60 በመቶ በላይ በሆኑ የምርጫ ክልሎች ብቻውን መወዳደሩ[33] በክልሉ ለታየው የፖለቲካ ብዝኃነት መቀጨጭ ሚና ተጫውቷል።

ለተከታታይ አራት ዓመታት በመጠነ ሰፊ የትጥቅ በግጭት[34] ውስጥ የከረመው የኦሮሚያ ክልል የፖለቲካ ብዝኃነትን ለማረጋገጥ ይቅርና "ከጨለማ ወደ ጨለማ እየሔደ ያለ ነው።"[35]


ከዚህ ባለፈም በ2015 በክልሉ ይፋዊ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ባይኖርም፥ በክልሉ በተለያዩ አካባቢዎች በግጭቶች ሳቢያ የኮማንድ ፖስቶች መኖራቸው የፖለቲካ ብዝኃነት ላይ አሉታዊ ጫና አሳድሯል። በዚህም ምክንያት የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመንቀሳቀስና አባላትን የመመልመል፥ የማስተማርና የማስተባበር ገደቦች እንዲኖርባቸው ሆኗል።[36]

በተጨማሪም በክልሉ የሕዝብ አዳራሾችን መጠቀም እንዲሁም ሚዲያ ላይ የተጣሉ ገደቦች አሉ። ገዥው ፓርቲም በክልሉ አባላትን የማፍራት፣ የተለያዩ ማኅበራዊ ሥራዎችን ለመሥራት የመንግሥትን ሀብት ጥቅም ላይ ሲያውልም ይስተዋላል። በአገር አቀፍ ደረጃ ለረጅም ጊዜ የቆየው የመንግሥትና የፓርቲ መቀላቀል በክልሉም በግልጽ ይታያል። የፖለትካ ምኅዳሩ ለገዥው ፓርቲ ያደላ በመሆኑ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ በስፋት አይስተዋልም።[37]

የፖለቲካ ባሕሉ ለመንግሥትና ለገዥው ፓርቲ ያደላ ከመሆኑም በተጨማሪ፥ ሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ ሰፊ ተደራሽነት ያላቸው የመገናኛ ብዙኃን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ስለሚገኙ ገዥው ፓርቲ እንደፈለገ ጥቅም ላይ ያውላቸዋል። ለፖለቲካ ስርዓቱ አንዱ ስጋትና የፖለቲካ ብዝኃነት እንቅፋት የሆነውም በክልሉ የፖለቲከኞች እሥርና እንግልት የቀጠለበት ዓመት ስለነበር በኦሮሚያ ክልል የፖለቲካ ብዝኃነት አደጋ ላይ ወድቆ ነበር።[38]

31 የቡድን ውይይት 1
32 የቡድን ውይይት 1
33 https://ambadigital.net/2021/3183/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
34 https://m.facebook.com/dw.amharic/posts/704312588400611/?locale=de_DE (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
35 የቡድን ውይይት 2
36 የቢድን ውይይት 2
37 የቡድን ውይይት 2
38 የቡድን ውይይት 2

## የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳድር



የጋምቤላ ክልል በአገሪቱ ለረዥም ጊዜ የዘለቁ ግጭቶችና ጥቃቶችን ካስተናገዱና እያስተናገዱ ካሉ ክልሎች አንዱ በመሆኑ፥ ይህ በክልሉ የፖለቲካ ምኅዳር ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል። በክልሉ ያለው የፖለቲካ ምኅዳር ሐሳብን በነፃነት ለመግለፅ የሚያስቸግር፣ በፆታ፣ እምነት እና ብሔር እየተለየ መድልዖ የሚደረግበት ነው[39]።

ለዚህ እንደ ማሳያ ከሚጠቀሱ ክስተቶች አንዱ ከክልሉ መንግሥት ጋር ሥምምነት በማድረግ በ2015 ወደ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የተመለሰው የጋምቤላ ሕዝቦች ነፃነት ግንባር (ጋሕነግ)[40] አባላቱ ከእስር የተለቀቁ ቢሆንም፥ ትጥቅ ፈትተው ወደ ሰላማዊ የፖለቲካ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መግባታቸው በገዥው ፓርቲ የበላይነት በተያዘው የፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ እንዲዋጡ ነው ያደረጋቸው[41]። የክልሉ ሕጎች የመምረጥና የመመረጥ መብትን ባይገድቡም፥ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ፣ ሐሳብን በነፃነት ለመግለጽ የሚያስችል ምኅዳር ግን በክልሉ አልነበረም። ግለሰቦች በፖለቲካ አመለካከታቸው ሳቢያ ሲታሰሩ ነበር፤ እስር በመፍራትም በርካቶች ከመናገርና ሐሳባቸውን በይፋ ከመግለፅ ይቆጠባሉ[42]። በተጨማሪም፣ የክልሉ የፀጥታ ሁኔታ አስቸጋሪ ሆኖ በዘለቀባቸው ወራት በ2015 የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታወጀበትና የሰዓት እላፊ ገደብ የተጣለበት ሲሆን፥ ይህም በመሰብሰብ መብቶችና በመሰል ለፖለቲካ ብዝኃነት ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች ላይ ገደብ ጥሏል[43]። እነዚህ ገደቦች የሰዎችን መብቶች ከመኖር መብት እስከ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ድረስ እንዳይኖር አድርገዋል። በተጨማሪም፥ በጋምቤላና በደቡብ ሱዳን ጎሳዎች መካከል ያለው የጎሳና የብሔር መመሳሰል በፖለቲካ ምኅዳሩ ላይ አሌ የማይባል ጫና የሚያሳድርም ነው። በእነዚህ መመሳሰሎች ሳቢያም፥ በክልሉ ነዋሪ ያልሆኑ የውጭ አገር ዜጎች በፖለቲካው ተሳትፎ እንዲያደርጉና በሌሎች ላይ ጫና ማሳደር እንዲችሉ ይደረጋል[44]።


ገዥው ፓርቲ የክልሉን መንግሥት ሀብት ለፖለቲካ ዓላማዎች የሚጠቀም ሲሆን፥ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበትን ሀብት ለማሰባሰብ እንዳይችሉ ገደቦችን ያኖራል። ከዚህ በተጨማሪም፥ ገዥው ፓርቲ በክልሉ መገናኛ ብዙኃን ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ያለውና የፓርቲ ሰዎች ስለሆነ በበላይነት ተሹመው የሚመሯቸው፥ ከገዥው ፓርቲ የተለየ ሐሳብ ላላቸው አካላት እኩል ዕድል አይሰጥም። የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴዎችም እጅግ የበዛ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል[45]። ሆኖም ግን፥ በክልሉ በሚኖሩ ብሔሮች አባላት መካከል በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ቅራኔዎችና ግጭቶች የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደልባቸው የሚንቀሳቀሱበት ከባቢ ካለመኖሩም በተጨማሪ፥ ክልሉ አጎራባች በሆነው ኦሮሚያ ክልል የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች ወደ ክልሉ እየገቡ ጥቃቶችን ስለሚሰነዝሩ በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራሉ። ይህም በብዝኃነት ላይ ላቅ ያለ ተፅዕኖ ያሳድራል[46]።

39 የቡድን ውይይት 6
40 https://www.youtube.com/watch?v=Pfu0_7QxzZE (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
41 የቡድን ውይይት 6
42 የቡድን ውይይት 6
43 https://ehrc.org/%e1%8c%8b%e1%88%9d%e1%89%a4%e1%88%8b-%e1%8a%ad%e1%88%8d%e1%88%8d%e1%8d%a1-%e1%8b%a8%e1%8a%ad%e1%88%8d%e1%88%89-%e1%8c%b8%e1%8c%a5%e1%89%b3-%e-1%88%81%e1%8a%94%e1%89%b3-%e1%89%a0%e1%8a%90%e1%8b%8b/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
44 የቡድን ውይይት 6
45 የቡድን ውይይት 6
46 የቡድን ውይይት 6

# 4

# የ2015 ዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምዘና

ከላይ አስቀድሞ እንደተመላከተው፥ የሚከተሉት የክልሎች ምዘና በመጠይቁ፣ የቡድን ውይይቶች እና ማጠናከሪያ መረጃዎችን በማዋደድ ተተንትኖ የቀረበ ነው።



# የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር

## የመንግሥት ውጤታማነት

### የሕግ አውጪው ውጤታማነት

የሲዳማ ክልል መስተዳድር በክልልነት የተገኘውን ደስታ ከማጉላት ባሻገር የሚጨበጥ ለውጥ በሕግና በተግባር ለማምጣት የሠራው ሥራ ውስን ነው። ከዚህ በተጨማሪም፥ እንደ አዲስ ክልልነቱ የፓርቲና የሌሎች ክልሎችና የፌዴራል መንግሥት ፍላጎቶች እና ጫናዎች ከፍ ያሉ ናቸው።[47]

በክልሉ ያሉ መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ አደረጃጀቶች በውሳኔ አሰጣጦችና ሒደቶች ላይ ጫና ያሳድራሉ። በዚህም ሁሉን አካታች ሕጎችንና ፖሊሲዎችን በማውጣት ላይ ውስንነቶች ያሉ ሲሆን፥ ሲዳማ ክልል መሆኑ እንደ መጨረሻ ግብ ተወስዷል።[48]

### የሥራ አስፈፃሚው ውጤታማነት

የሲዳማ ክልል ሥራ አስፈፃሚ በተለይ በክልሉ ባሉ ኢ-መደበኛ በሆኑ አደረጃጀቶች ከፍተኛ ጫና የሚደረግባቸው ሲሆን፥ በተለይ በክልሉ ካሉ ጎሳዎች የመንግሥት ውስጥ ውክልና ጋር በተያያዘ የሚያደርጉት ግፊት ከፍተኛ ነው[49]።

የፌዴራል መንግሥቱና የገዢው ፓርቲ መዋቅር በክልሉ የሹመትና የውሳኔ አሰጣጥ ሒደቶች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ስላለው የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ አካል ከተፅዕኖ ነፃ ሆኖ ተግባሮቹን እንዳያከናውን ያደርጉታል። በዚህም ሳቢያ የክልሉ መንግሥት የፖሊሲ ነፃነት ኖሮት በክልሉ የሚያስፈልጉ ሥራዎችን የሚያከናውንበት ዕድል አናሳ ነው።[50]

47 የቡድን ውይይት 4
48 የቡድን ውይይት 4
49 የቡድን ውይይት 4
50 የቡድን ውይይት 4

## የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ውጤታማነት

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚቀጠሩ ሠራተኞች በዝምድናና በጥቅም ትስስር የሚፈፀሙ እንደሆኑ ማሳያዎች ያሉ ሲሆን፣ በተለይም ከፍ ያሉ ግን ሹመት ያልሆኑ ኃላፊነቶች በፓርቲና በዝምድና እንጂ ብቃትን መሠረት ባደረገ ምርጫ የሚከናወኑ አይደሉም።[51]

ለአብነትም በሲዳማ ክልል ከሕግ አግባብ ውጪ የተፈፀሙ 752 ቅጥሮችን መሰረዙን የክልሉ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ አስታውቆ ነበር።[52] ሆኖም ግን፣ ከእነዚህ ሠራተኞች መካከል በሕገ ወጥ መንገድ የተከናወኑ ሳይሆኑ የተባረሩ ነበሩ።

ከዚህ ባለፈም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎቶች በገዥው ፓርቲ አባላት የተያዙ በመሆናቸው፣ በብዛት የፖለቲካ ዓላማ ማስፈፀሚያ ሲሆኑም ይስተዋላል።

እነዚህና ሌሎች ማሳያዎች እንደሚያመለክቱት፣ በክልሉ የመንግሥት አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ ብቃትን መሠረት ያደረገ፣ ከፖለቲካና ከሌሎች ጫናዎች የፀዳ አይደለም።

## የፀረ ሙስና ሥራዎች ውጤታማነት

በሲዳማ ክልል የፀረ ሙስና ሕጎችና ተቋማዊ አደረጃጀቶች የተመሠረቱ ቢሆንም፣ ሙስናና ብልሹ አሠራር ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተጠያቂነቶች መጠቃቂያና ፖለቲካዊ ዓላማ ማሳኪያ ይሆናሉ። የመንግሥት ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ንብረት ማስመዝገብ ሥራዎች እምብዛም ትኩረት የሚሰጣቸው ባለመሆናቸው፣ ሥልጣን የሀብት ማጋበቻ እንዲሆን በር ይከፍታል[53]።

ከዚህ ባለፈም፣ በተለይ በ2015 ከአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ጋር የተያያዘ ከፍተኛ ስርቆት የነበረ ሲሆን፣ ለአብነትም 38 ሚሊዮን ብር ያወጣል የተባለ 25,000 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ተሰርቆ ነበር።[54] የሌሎችም የግብርና ምርቶች ስርጭት ላይ ስወራና ባልተገባ መንገድ የመሸጥ ልምምዶች አሉ።

በክልሉ ከዚህ ስርቆት ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው የታሰቡ 148 የሥራ ኃላፊዎች በቁጥጥር ሥር ውለው በምርመራ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ በ2015 በሌሎች ጥፋቶች ከተጠረጠሩ 95 የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች 50ዎቹ ላይ ምርመራ መጀመሩ ተነግሮም ነበር።[55] በተጨማሪም በ2015 ክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ (በፍትሕ ቢሮ) ሥር የፀረ-ሙስና ኮሚቴ አቋቁሞ ነበር[56]። ይህ ኮሚቴ የተቋቋመው በፌዴራል መንግሥት ተነሳሽነት[57] ሲሆን፣ ይህ ተነሳሽነት ሳይሳካ እንደቀረ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲናገሩ ተደምጠዋል።

51 የቡድን ውይይት 4

52 https://www.fanabc.com/archives/208604 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

53 የቡድን ውይይት 4

54 https://ethiofm107.com/2023/10/19/%E1%89%A0%E1%88%B2%E1%8B%B3%E1%88%9B-%E1%8A%AD%E1%88%8D%E1%88%8D-%E1%89%A0%E1%89%B0%E1%8D%88%E1%8C%B8%E1%88%98%E1%8B%8D-%E1%8B%A8%E1%8A%A0%E1%8D%88%E1%88%AD-%E1%88%9B%E1%8B%B3%E1%89%A0%E1%88%AA/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

55 https://t.me/feacc/1712 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

56 https://www.ena.et/web/amh/w/am_201200 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

57 https://www.ena.et/web/amh/w/am_193367 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

## ያልተማከለ አስተዳደር

የሲዳማ ክልል ሲመሠረት በሕገ መንግሥቱ መሠረት በአቅጣጫ በተሰየሙ አራት ዞኖችና አንድ የዞን ደረጃ ያለው የከተማ አስተዳደር፣ እንዲሁም 30 ወረዳዎችና ስድስት በወረዳ ደረጃ ያሉ የከተማ አስተዳደሮች እንደሚኖሩት ተመላክቷል።[58] ይሁንና፥ በ2015 የክልሉ የታችኛው መዋቅር ዝርጋታ ክልሉ ከተመሠረተ ከሁለት ዓመታት በኋላ እንኳን ያልተጠናቀቀ ሲሆን፣ የክልሉ ሥራ በስፋት የሚሠራው ከክልል በሚሰጡ አቅጣጫዎች ነው። ስለዚህም የታችኛው መዋቅር አስተዳደሮች በአግባቡ የተለየ ሥልጣን የላቸውም። ከዚህ ባለፈም ለእነዚህ መዋቅሮች የሚሰጡ የአስተዳዳሪነትና ሌሎች ሹመቶች ከክልል ስለሆኑ በንዑስ የመንግሥት መዋቅሮች ሥር የሚተዳደሩ ዜጎች በፍላጎቶቻቸው የሚመርጧቸው መሪዎች የሏቸውም።[59]

> በእነዚህ ሁነቶች ላይ በመንተራስ ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ **(25)** ያገኘው የመንግሥት ውጤታማነት ባሕሪ መገለጫ ***"የሕግ አውጪው ውጤታማነት"*** ሲሆን፥ ዝቅተኛ ነጥብ **(18)** ያስመዘገበው ደግሞ ***"የፀረ-ሙስና ውጤታማነት"*** ነው። በአጠቃላይ የሲዳማ ክልል ***"የመንግሥት ውጤታማነት"*** ድምር ውጤት **112** ነው።

በዚህ ውጤት ማሳያ መሠረት በክልሉ ያለው የመንግሥት ውጤታማነት እጅግ አናሳ ሲሆን፥ ክልሉ ከተለካባቸው የዴሞክራሲ ባሕርያት እጅግ ደካማ ውጤት የተመዘገበበትም ዘርፍ ነው።

## ቁጥጥር እና ሚዛን

## የሕግ አውጪው ሥልጣን

በክልሉ የተመሠረተው የክልል ምክር ቤት በ2013 የተደረገውን አጠቃላይ ምርጫ ተከትሎ በተመረጡ የሕዝብ ተወካዮች ሲሆን፥ የሕግ አውጪ የሆነው የክልሉ ምክር ቤት ውሳኔዎቹንና የሕጎችን አፈፃፀም ከመከታተል አንፃር ድክመቶች አሉበት። ለዚህም እንደ አንድ ማሳያ የሚቀርበው በክልሉ ምክር ቤት የዞን አደረጃጀት በአዋጅ ከፀደቀ በኋላ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይተገበር ሲቀር የወሰደው ዕርምጃ/ያመጣው ተጠያቂነት አለመኖሩ ነው።[60]

ይህ የሆነው ደግሞ በክልሉ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ አውጪ አካላት መካከል ወጥነት ባለው መልኩ በተግባር የተቀላልቀለ አሠራር እና ሚና በመኖሩ፥ ሕግ አውጪው አስፈፃሚው የሚያስበውን ማስፈፀሚያ ነው።[61] በዚህም ምክንያት፥ በምክር ቤቱ የተቋቋሙ ቋሚ ኮሚቴዎች ቢኖሩም የቁጥጥርና ሚዛን ሥራ ይሠራሉ ለማለት ያዳግታል።

---

58 https://www.proworksmedia.com/69778/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

59 የቡድን ውይይት 4

60 https://wazemaradio.com/%E1%8B%A8%E1%88%B2%E1%8B%B3%E1%88%9B-%E1%8A%AD%E1%88%8D%E1%88%8D-%E1%89%A0%E1%8B%98%E1%8A%95%E1%8B%B5%E1%88%AE-%E1%8B%93%E1%88%98%E1%89%B5%E1%88%9D-%E1%8B%9E%E1%8A%95-%E1%88%9B%E1%8B%8B%E1%89%80/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

61 የቡድን ውይይት 4

## የፍርድ ቤቶች ነፃነት

የሲዳማ ክልል ሕግ ተርጓሚ አካል የሆኑት ፍርድ ቤቶች በውሳኔ አሰጣጥ ሒደት የተሻለ ነፃነት አላቸው የሚል አመለካከት በአንድ ወገን ሲኖር፥ በሌላ በኩል ደግሞ ተቋማዊ ነፃነት ላይ ከበጀትና ከዳኞች ሹመት ጋር የተያያዙ ተፅኖዎች ይኖሩባቸዋል የሚሉ አረዳዶች አሉ። ምንም እንኳን የዳኞች ሹመት በምክር ቤት የሚደረግና ሌሎች የዳኞች ግድፈቶች በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የሚታዩ ቢሆንም፥ በፍርድ ቤቱና በአስፈፃሚው አካል ላይ ያለው የፖለቲካ ጫና በዳኝነት አካላቱ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም። የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቅራቢነት ስለሚሾሙ በተዘዋዋሪ የሚኖርባቸው ጫና ይኖራል።[62]

## የፍርድ ቤት ገለልተኝነት

ፍርድ ቤቶች በተቋማዊ አደረጃጀት፣ በሕግና በውሳኔ ነፃነት ገለልተኝነታቸው ተረጋግጧል ቢባልም፥ ውሳኔዎቻቸው ግን ከፖለቲካ ተፅዕኖና ከፖሊሲ ፍላጎቶች እምብዛም የተላቀቁ እና የተለዩ አይሆኑም። የፍርድ ቤቶች ትዕዛዞች በማይከበሩባቸው ሁኔታ ፍርድ ቤቶች ትኩረት የሚሰጧቸውና መፍትሔ ለማስገኘት የሚጥሩባቸው እስሮች እንደየሁኔታዎቹ ይለያያሉ።[63]

## ነፃ ሚዲያ

በሲዳማ ክልል ከፍተኛ ተደራሽነትና መረጃ የማግኘት ዕድሉ ያላቸው በመንግሥት ቁጥጥር የሚተዳደሩ የክልሉ መገናኛ ብዙኃን ከመሆናቸው የተነሳ፥ በክልሉ የመንግሥት አካላትን የመቆጣጠር ሥራ አይሠሩም። እነዚህ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚገኙ መገናኛ ብዙኃንም ኃላፊዎች የሚሾሙላቸው በመንግሥት አስፈፃሚ አካላት በመሆኑ ተሿሚዎቹ የመረጃ በር ጠባቂ ሆነውም ያገለግላሉ። በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የግል መገናኛ ብዙኃን ሳይቀር የመንግሥትን፣ የግለሰቦችንና የፓርቲዎችን ሐሳቦች የሚያስተጋቡ ናቸው[64]። በክልሉ ያሉ የግል/የሕዝብ መገናኛ ብዙኃን (ለምሳሌ የሲዳማ ሚዲያ ኔትወርክ) በመንግሥት ቦርድ ተሹሞላቸው የሚሠሩ ናቸው።

በክልሉ የሚገኙ ሚዲያዎች በብዝኃነትም ሆነ በሙያተኝነት ብቃት ያነሰ አቋም አላቸው። ለዚህ አንዱ አስተዋፅዖ ያደረገውም ክልሉ አዲስ መሆኑ ሊሆን ይችላል።[65]

## ተሟጋች ቡድኖች

በሲዳማ ክልል መቀመጫቸውን አድርገው የሚንቀሳቀሱና በፌዴራል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የተመዘገቡ 50 ገደማ አገር በቀል ድርጅቶች ያሉ ሲሆን፥ ከእነዚህ ድርጅቶች አብዛኞቹ እምነት ተኮር ስብስቦች ሲሆኑ የልማት ሥራዎችን የሚሠሩ ናቸው። በዚህም፥ ለቁጥጥርና ሚዛን አስተዋፅዖ እያደረጉ ነው ማለት አይቻልም። ነገር ግን አሁን በክልሉ ያለው የተሟጋች ቡድኖች ምኅዳር እየተሻሻለ የሚገኝ በመሆኑ፥ የወጣቶችና ሌሎች ስብስቦች ብቅ ማለት መጀመራቸውና የልማት ሥራ ላይ የተሠማሩም የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን ማንሣት መጀመራቸው በበጎ የሚታይ ነው።[66]

---

62 የቡድን ውይይት 4
63 የቡድን ውይይት 4
64 የቡድን ውይይት 4
65 የቡድን ውይይት 4
66 የቡድን ውይይት 4

ይሁንና በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በክልሉ ሔደው ለመሥራት አስተዳደራዊም ሆነ ሌሎች ውስብስብ አሠራሮች አለመኖራቸው የተሚጋች ቡድኖች ሊስፋፉ የሚችሉበት ከባቢ እንዳለ ያሳያል።[67]

> እነዚህ ነጥቦች ከግምት ገብተው ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበ መረጃ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ **(27)** ያገኘው የቁጥጥር እና ሚዛን መገለጫ *"ተሚጋች ቡድኖች"* ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(17)** ያስመዘገበው ደግሞ *"ነፃ ሚዲያ"* ነው። በአጠቃላይ የሲዳማ ክልል መስተዳድር የቁጥጥር እና ሚዛን ድምር ውጤት **166/225** ነው።

በዚህም መሠረት ክልሉ በቁጥጥርና ሚዛን ረገድ ሁለተኛ ዝቅተኛ ውጤት ያስመዘገበበት ከመሆኑ አንፃር ክፍተቶች እንዳሉ ያሳያል።

## የዜግነት ነፃነቶች

### ሐሳብን የመግለፅ ነፃነት

በሲዳማ ክልል ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት ከኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የተቀዳ ሲሆን፥ በክልሉ ሕገ መንግሥትም የተጠበቀ መብት ነው። በክልሉ ውስጥ ይህ ነፃነት በተግባር ደረጃ የሚገጥሙት ተግዳሮቶች አሉ። በሲዳማ ክልል ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብታቸውም የተጠቀሙ ሰዎች ታስረዋል።[68]

ሐሳብን ከመግለጽ ነጻነት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ጥቃቶችንና መሰል ጫናዎች የተለየ ሐሳብ የሚያንፀባርቁ የወጣት ስብስቦችና አደረጃጀቶች እንዲቀጭጩም አድርገዋል።[69]

### የመደራጀት ነፃነት

በሲዳማ ክልል ዜጎች በመረጡት መልኩ ለሰላማዊ ዓላማ መደራጀት በሕግ የተፈቀደላቸው ሲሆን፥ በተለያዩ ማኅበራት በሕግ የተረጋገጠላቸውን መብት በመጠቀም በተለያዩ ማኅበራት ተደራጅተዋል። በክልሉ በማንኛውም ሁኔታ መደራጀትን ሰላማዊ ለሆነ ዓላማ እስከሆነ ድረስ በሕግም ሆነ በፖሊሲ የተጣለ ገደብ የለም።[70]

ሆኖም፥ በክልሉ በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሠሩ ሠራተኞች በማኅበራት ለመደራጀት የሚያነሷቸው ጥያቄዎችን ለመመለስ ክልሉ የተጫወተው ሚና አናሳ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም፥ በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ወጣቶች አሁን በተለያዩ ምክንያቶች የተበታተኑ ሲሆን፥ በተለይ በሐዋሳ ሐይቅ አካባቢ ተደራጅተው ይሠሩ የነበሩ አሳ አጥማጆች

67 የቡድን ውይይት 4

68 https://www.dw.com/am/%E1%89%A0%E1%88%B2%E1%8B%B3%E1%88%9B-%E1%8A%A5%E1%88%A5%E1%88%AD%E1%8A%93-%E1%88%9B%E1%88%B3%E1%8B%B0%E1%8B%B5-%E1%8A%A5%E1%8B%A8%E1%89%B0%E1%8D%88%E1%8C%B8%E1%88%98-%E1%8A%90%E1%8B%8D-%E1%88%B2%E1%8D%8C%E1%8D%93/audio-67054511 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

69 የቡድን ውይይት 4

70 የቡድን ውይይት 4

በአካባቢው በነበሩ ግጭቶች አሁን እንደ ቀድሞው እየሠሩ አይደለም።[71] ስለዚህ፥ የሕግ ጥበቃ ቢኖራቸውም፥ ብንደራጅ በድጋሚ መፍረሳችን አይቀርም የሚል ስጋት በስፊው ይስተዋላል።

ከዚህ ውጪ፥ ለመብቶችና ለመልካም አስተዳደር እንዲሁም ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ቡድኖች ተደራጅተው መደበኛ በሆነ ቅርፅ ሲሠሩ እምብዛም አይታዩም።

## የሃይማኖት ነፃነት

የሲዳማ ክልል ሕገ መንግሥት በክልሉ የሚኖሩ ዜጎች የመረጡትን ሃይማኖት እንዲከተሉና እምነታቸውንና ሃይማኖታቸውን እንዲያስተምሩና እንዲያመልኩ ይፈቅዳል። ከዚህም የተነሳ፥ የሲዳማ ክልል የበርካታ እምነት ተቋማት መናኸርያ ልትሆን ችላለች።[72]

## የመንቀሳቀስ ነፃነት

በሲዳማ ክልል የመንቀሳቀስ ነፃነት በሕግ የተረጋገጠ ቢሆንም፥ ከኦሮሚያ ክልል ጋር አጎራባች አካባቢዎች በነበሩ ግጭቶች[73]፥ እንዲሁም በክልሉ በነበሩ የጠለፋና የአስገድዶ መሰወር ድርጊቶች ሳቢያ የዜጎች የመንቀሳቀስ ነፃነቶች አደጋ ላይ ወድቆ ነበር።[74] በሲዳማ የጠለፋ ጋብቻ በገጠሩ አካባቢ የተንሰራፋ በመሆኑም ሴቶች እንደልባቸው እንዳይንቀሳቀሱ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል።

ከዚህ በተጨማሪም፥ ካሁን ቀደም በሲዳማ ከክልልነት ጥያቄ ጋር ተያይዞ በነበረ አመፅ ጉዳት በመድረሱና እስካሁን ያጠላው ሥጋት ባለመግፈፉ በመንቀሳቀስ ነፃነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። የፖለቲካ ልዩነታቸውን በግልጽ የሚናገሩ ሰዎችም በክልሉ እንደልባቸው እንዳይንቀሳቀሱ፣ አንዳንዴም እንዲሸሹ ይደረጋሉ።[75]

## የግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ

በሲዳማ ክልል የዜጎች የግል ደኅንነትና ምሥጢር ጥበቃ በተለይ በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚወድቁ ሲሆን፥ በክልሉ ያሉ ዜጎች የደኅንነት ሥጋቶች አሉባቸው። ከዚህ ባለፈም በግለሰብ ደረጃና ኢ-መደበኛ በሆኑ አደረጃጀቶች ሰዎች ተጠልፈው የሚሰወሩ ከመሆኑም በላይ፣ ሰዎችን ማስፈራራትም በስፋት ታይቷል።[76]

> ስለዚህም ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(42)** ያገኘው መገለጫ *"የሃይማኖት ነፃነት"* ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(23)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"የመደራጀት ነፃነት"* ነው። በአጠቃላይ የሲዳማ ክልል *"የዜግነት ነፃነቶች"* የዴሞክራሲ ባሕሪ ድምር ውጤት **150/225** ነው።

71 የቡድን ውይይት 4
72 የቡድን ውይይት 4
73 https://ethiopiainsider.com/2022/6622/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
74 https://www.bbc.com/amharic/articles/c2584e2grvzo (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)፥ የቡድን ውይይት
75 የቡድን ውይይት 4
76 የቡድን ውይይት 4

የሲዳማ ክልላዊ መስተዳድር ከዚህ ባሕሪ አንፃር በሃይማኖት ነፃነት ረገድ መልካም ገጽታ እንዳለው ማየት የሚቻል ሲሆን፥ በክልሉ ያለው የዜግነት ነፃነቶች በመደራጀት መብት ረገድ ውሱንነቶች ይታዩበታል።



## ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች

### መሠረታዊ ፍላጎቶች

የሲዳማ ክልል መዋቀር ያሳካዋል ተብለው ከተነገሩ ጉዳዮች አንዱ ክልሉ የተሻለ የሕዝቡን ቁጥር የሚመጥን በጀት ይሰጠዋል፣ በዚህም የመሠረታዊ ፍላጎቶችን ጨምሮ ሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎችን መመለስ ያስችለዋል[77] የሚል ነበር። ይሁንና፣ እንደ ውኃና ጤና ያሉ አገልግሎቶችን ማግኘት አዳጋች ነው። የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ማነስ፣ እንዲሁም የጤና ተቋማት ቁሳቁሶችና ባለሙያዎች አለመሟላት ቀዳሚ ምክንያቶች ሆነዋል። በጤና ተቋማት የሚገኙ ባለሙያዎች በብዛት ከክልሉ የሚፈልሱ ሲሆን፣ እንደምክንያት ከሚያነሷቸው በርካታ ጉዳዮች አንዱ ሙስና ነው።[78]

ከከተማ ራቅ ብሎ የሚገኘው አብዛኛው ማኅበረሰብ የውኃ አቅርቦቱ ከወራጅ ወንዝ ሲሆን፥ የሚበላሹ የጉድጓድ ውኃዎችም አይጠገኑም።[79] ይህ እንዳለ ሆኖ፥ በክልሉ ቆላማ አካባቢዎች ደግሞ የውኃ እጥረቱ ስለሚከፋ ለበለጠ ችግር ይዳረጋሉ።

በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ የመጣው የኑሮ ውድነት በተለይ የዋጋ ንረት የክልሉ ነዋሪዎች መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት እንዲቸገሩ አድርጓቸዋል።

### የትምህርት መብት

በኢትዮጵያ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት ከቅድመ አንደኛ ደረጃ እስከ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት በአስገዳጅነት በነፃ እንዲሰጥ የሚደረግ፣ እንዲሁም ከ9-12ኛ ክፍል ትምህርት አስገዳጅ ሳይሆን በነፃ እንዲሰጥ የሚበረታታ ነው።[80] ይሁንና በሲዳማ ክልል በዚህ ረገድ በተለይ የቅድመ መደበኛና የመጀመሪያ ትምህርት ተሳትፎ አነስተኛ ነው። ለአብነትም፣ በሲዳማ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የመጀመሪያ ዕድሜያቸው ደርሶ ወደ ትምህርት የማይገቡ ሕፃናት ካሉባቸው አምስት ቀዳሚ ክልሎች አንዱ ሲዳማ ነው።[81]

ይህም በክልሉ ያለውን የመጠነ ተሳትፎ መጠን አናሳነት የሚያመላክት ሲሆን፥ በሴቶች አጠቃላይ የመጠነ ተሳትፎ ከወንዶች የበለጠ ሆኖ ከተመዘገበባቸው ክልሎች ደግሞ ከቀዳሚዎቹ ነው።

---

77 https://www.ethiopianreporter.com/69917/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
78 የቡድን ውይይት 4
79 የቡድን ውይይት
80 https://moe.gov.et/storage/Books/Education%20and%20Training%20Policy-Yekatit-2015%20Final.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
81 https://moe.gov.et/storage/Books/ESAA%202014%20EC%20(2021-22%20G.C)%20Final.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

## የስርዓተ ፆታ እኩልነት

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥትም ሆነ የሲዳማ ክልል ሕገ መንግሥት የሴቶችን መብት በተመለከተ ግልጽ ድንጋጌዎች ያሏቸው ሲሆን፥ የሴቶች ጉዳይ ቢሮዎች፣ በተዋረድ ያሉ መምሪያዎችና ጽሕፈት ቤቶች ተቋቁመዋል። በክልሉ በውክልና ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ እየጨመረ የመጣ ሲሆን፥ በክልሉ ምክር ቤት የሴቶች ቁጥር ከወንዶች ጋር የተመጣጠነ (48%) ነው።[82]

በ2015 ይፋ የተደረገ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥናት እንደሚያሳየው፥ በሲዳማ ክልል፣ በተለይም በሐዋሳ ከተማ በሴቶች ላይ የሚደርስ ከፍተኛ የሆነ ጾታዊ ጥቃት አለ።[83] ከዚህ ባለፈም በክልሉ በተለያዩ ጊዜያት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጠለፋዎች ሁለንተናዊ የስርዓተ ፆታ እኩልነት ለማረጋገጥ እንቅፋት የሚሆኑ ሲሆን፥ የሴቶችን የትምህርት፣ የሥራና ሌሎች ዕድገቶችን ይገታል።[84]

ለዚህ ተግዳሮት አንደኛውን ክፍተት የፈጠረው የስርዓተ ፆታ አገራዊ ፖሊሲ አለመኖር ሲሆን፥ ኢትዮጵያ የገባቻቸው ዓለም ዐቀፋዊና አገራዊ የሕግ ግዴታዎች[85] ተበታትነው በተለያዩ ዘርፎች በመመሪያና በደንብ ለመተግበር ሲሞከሩ ተስተወልዋል[86]።

## የግል ንብረት ጥበቃ

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትም ሆነ ሌሎች ክልላዊ ሕጎች የዜጎችን በየትኛውም ስፍራ ንብረት የማፍራትና በባለቤትነት የመጠቀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋሉ። ይህ በሕግ የተደነገገ መብት ቢሆንም፥ በተለያዩ መዋቅራዊና ከግጭት ጋር በተያያዙ ችግሮች አደጋ ላይ ይወድቃሉ። ስለዚህ፥ የሕግ ጥበቃ ቢኖርም በተግባር ግን ከፍተኛ ተግዳሮቶች አሉበት።[87]

ሆኖም ግን፥ ይህ በ2015 እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን፥ በክልሉ የሚኖሩ ዜጎች ንብረቶች እንዲጠበቁና አዳዲስ ንብረት የሚያፈሩ ዜጎችም ሆኑ ሌሎች መዋዕለ ነዋይ የሚያፈሱ አካላት ወደ ክልሉ እንዲመጡ ጥረቶች ሲደረጉም ታይተዋል።[88]

## የኢኮኖሚ ደረጃ መመጣጠን

በሲዳማ ክልል ብዝኃነት ያለው የሥራ ዕድልና የኑሮ መምሪያ (livelihood) ባለመኖሩ የኢኮኖሚ አለመመጣጠኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ ነው። በክልሉ ካለው የኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞም በተለይ በመንግሥት ሠራተኞች ገቢ አለመጨመርና በአቅም ለመሥራት አዳጋች በመሆኑ የኢኮኖሚ አለመመጣጠኑ እንዲሰፋ አድርጓል።[89]

82 የቡድን ውይይት 4

83 https://ethiopia.un.org/en/235094-creating-safe-and-empowering-public-spaces-women-and-girls%C2%A0 (ጥቅምት 2016 የተገኘ)

84 የቡድን ውይይት 4

85 https://www.facebook.com/MOJEthiopia/posts/1186316018129147/ (ጥቅምት 2016 የተገኘ)

86 የቡድን ውይይት 4

87 የቡድን ውይይት 4

88 የቡድን ውይይት 4

89 የቡድን ውይይት 4

ሆኖም በቅርብ ጊዜ በተጀመሩ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎች ለውጦች የታዩ ቢሆንም፥ አነስተኛ ገቢ ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ የኢኮኖሚ ጫናው ከፍተኛ በመሆኑ የኢኮኖሚ አመመጣጠኑ እየሰፋ ቀጥሏል።

> እነዚህን ግብዓቶች ከግምት በማስገባት ከተሳታፊዎች በተሰበሰበ መረጃ ከላይ ከተጠቀሱት መገለጫዎች ከፍተኛውን ነጥብ **(31)** ያገኘው *"የትምህርት መብት"* ሲሆን፥ ዝቅተኛው ነጥብ **(20)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ"* ነው። በአጠቃላይ የሲዳማ ክልል *"ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች"* ድምር ውጤት **125/225** ነው።

ከዚህ በመነሳትም በክልሉ ያለው የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶች ጥበቃ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማምጣት ክልሉ ክፍተቶች እንዳሉበት የሚያመላክት ነው።



## የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

### የኅዳጣን ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር ነፃነት

የሲዳማ ክልል የሲዳማ ሕዝብ በክልልነት በመደራጀት ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር በተደረገ ትግል ፌዴሬሽኑ ከተፈጠረ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሠረተ 10ኛው የኢትዮጵያ ክልል ሲሆን፥ በክልሉ ተሰባስበው የሚኖሩ ኅዳጣን ብሔረሰቦች የሚገኙባቸው ቦታዎች የሉም። ይልቁንም፥ በክልሉ ተበታትነው የሚኖሩ፥ በአንዳንድ ስፍራዎችም ተቀላቅለው የሚኖሩ የሌሎች ብሔሮች ተወላጆች በብዛት ይኖራሉ። ከእነዚህም ወላይታ፣ ጉዳጉ፣ አማራ፣ ኦሮሞ ብሔሮች ተጠቃሽ ናቸው።[90]

የቅርብ ጊዜ መረጃ ባይኖርም፥ ለመጨረሻ ጊዜ በተካሔደው የ1999 የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በሲዳማ ክልል 93 በመቶ የክልሉ ነዋሪዎች የሲዳማ ብሔር ተወላጆች ሲሆኑ፥ ከቀሪው ሰባት በመቶ 4.5 በመቶ የሚሆነውን የሚይዙት የኦሮሞና የአማራ ብሔር ተወላጆች ናቸው። በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ አገልግሎት መረጃ መሠረት በክልሉ 4.7 ሚሊዮን ዜጎች ይኖራሉ።

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት በሚጠይቀው መሠረት በክልሉ የሚኖር ብሔር በክልሉ ውስጥ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ማቅረብ የሚችል ሲሆን፥ ይህንን ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችል የተሰባሰበ ኅዳጣን በክልሉ የሉም። ሆኖም ግን የተበታተኑና የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚናገሩ ግለሰቦች በተለያዩ መዋቅሮች እንዲሳተፉ ይደረጋል።[91]

90 የቡድን ውይይት 4

91 የቡድን ውይይት 4

## የኀዳጣን መብቶች

በሲዳማ ክልል የሚኖሩ የብሔርና የእምነት ኀዳጣን ባሕሎቻቸውንና እምነቶቻቸውን በመተግበርና በማስተዋወቅ ረገድ የሚጣልባቸው ገደብ የለም። ሆኖም ግን በክልሉ የሚገኙ ፖለቲካዊ ኀዳጣን ቡድኖች የመገለልና የመገፋት ጫና ይደርስባቸዋል።[92]

የክልሉ መንግሥትም በሃይማኖታዊና ባሕላዊ በዓላት ወቅት የፀጥታ ድጋፎችን የሚሰጥ ከመሆኑም ባሻገር፥ በአደባባይም ሆነ በቤት ውስጥ በሚከበሩ ክብረ በዓላት ላይም የሚደረግ ገደብ የለም።[93] ሆኖም ግን፥ ካሁን ቀደም በነበሩ ብሔር ተኮር ጥቃቶች ሳቢያ ባሕላቸውን በአደባባይ ለመግለጽ ቁጥብነት ይታይባቸዋል።[94]

## የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

በሲዳማ ክልል ተጋላጭ የሆኑ በተለይ ሴቶች የጥቃቶች ሰለባ ሲሆኑ የሚስተዋል ሲሆን፥ በክልሉ ከድንበር ጋር ተያይዘው በሚነሱ ግጭቶችም በሴቶች፣ በሕፃናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላሉ። በክልሉ በከተማም ሆነ በገጠር የሴቶች ጠለፋና ሌሎች ጾታዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶች ይስተዋላሉ።[95]

በብሔር ልዩነት ባይኖራቸውም በሥራ ዘርፎቻ ሰበብ የሚገለሉ እንደ ሐዲቾ ያሉ ኀዳጣን በክልሉ ያሉ ያሉ ሲሆን፥ አሁንም ድረስ ከተለያዩ ማኅበራዊ መስተጋብሮች ይገለላሉ። ሆኖም በዚህም ረገድ በክልሉ መንግሥትና በማኅበረሰቡ በተደረገ ጥረት በጋብቻ እስከ መተሳሰር የደረሰ ለውጥ እየተስተዋለ ነው።[96]

## የብዝኀ ቋንቋ አስተዳደር

በሲዳማ ክልል መቀመጫውን ያደረገው የደቡብ መገናኛ ብዙኃን ድርጅትም ሆነ የሲዳማ ሚዲያ ድርጅቶች ዝግጅቶቻቸውን በሲዳምኛና በሌሎች ቋንቋዎች፥ በብዛት በአማርኛ ያቀርባሉ። በክልሉ የሚገኙ መንግሥታዊ ተቋማት መልዕክቶቻቸውን እና ምልክቶቻቸውን በሲዳምኛና በፌዴራል መንግሥቱ የሥራ ቋንቋ (አማርኛ) ያደርጋሉ። በተጨማሪም፥ የንግድና የኢንቨስትመንት ፈቃዶች ሲሰጡ በተለያዩ ቋንቋዎች ይጻፋሉ። የክልሉ የሥራ ቋንቋ ሲዳምኛ ቢሆንም፥ በተለይ አማርኛ ቋንቋ ለአስተዳደርና ለሚዲያ ሥራ በስፋት ጥቅም ላይ ይውላል።[97]

ይህም፥ በክልሉ የሚሰጡ አገልግሎቶችና የመገናኛ ብዙኃን ስርጭቶች በስፋት በአማርኛና በሲዳምኛ የተወሰኑ ሲሆን፥ በተለይ በክልሉ በሚኖሩ ሕዝቦችና አጎራባች ክልሎች ያሉ ስብጥሮችን ሙሉ ለሙሉ ከግምት ያስገባ እንዳልሆነ ያሳያል።

## የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት

በሲዳማ ክልል የሚወጡ ሕጎችና አፈፃፀማቸው ላይ የተለያዩ ቡድኖች ጥያቄዎችን የሚያነሱ ሲሆን፥ የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት ግን እምብዛም ነው። ለአብነትም፥ በክልሉ እየተዘጋጀ ባለው የጥብቅና ፈቃድ ሕግ በክልሉ

92 የቡድን ውይይት 4
93 የቡድን ውይይት 4
94 የቡድን ውይይት 4
95 የቡድን ውይይት፥ https://ethiopia.un.org/en/235094-creating-safe-and-empowering-public-spaces-women-and-girls%C2%A0 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
96 የቡድን ውይይት 4
97 የቡድን ውይይት 4

የጥብቅና ፈቃድ ለማውጣት ሲዳምኛ ቋንቋን መቻል በግዴታ ማስቀመጡ አግላይ ሊሆን ይችላል በሚል ለሚነሱ ጥያቄዎች እስካሁን አጥጋቢ ምላሽ አልተሰጠም።[98]

ከዚህ ባለፈም፥ በክልሉ ለሚነሱ የመልካም አስተዳደር፥ የሙስና ጥያቄዎች፥ እንዲሁም በተደጋጋሚ ለሚነሱ የተጋላጭ ቡድኖች ጥቃቶች ምላሽ በመስጠር ረገድ ውሱንነቶች አሉት። ሆኖም፥ በ2015 በክልሉ መዲና ሐዋሳ ከንቲባ ጠባቂ ተጠልፋ የነበረችን ሴት ለማስለቀቅና አጥፊውንም በሕግ እንዲጠየቅ የተደረገው ርብርብ አበረታች እና በመልካም የሚታይ ነው።[99]


> ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት በዚህ የዴሞክራሲ ባሕሪ ውስጥ ከፍተኛውን ነጥብ **(37)** ያስመዘገበው መገለጫ *"የጎዳጣን ብሔረሰቦች ነጻነት"* ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(27)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት"* ነው። በአጠቃላይ የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መንግሥት*" የጎዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* ድምር ውጤት **166/225** ነው።

## አጠቃላይ ውጤት

በእነዚህ አምስት ባሕሪዎች (Attributes) መሠረት ተሳታፊዎቹ ከሞሉት መጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከአምስቱ የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች ውስጥ ከፍተኛውን ነጥብ (166) ያገኘው *"የጎዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* ሲሆን፤ ዝቅተኛውን (112) ያገኘው መገለጫ ደግሞ *"የመንግሥት ውጤታማነት"* ነው። ከአምስቱ ባሕሪያት ውስጥ አራቱ ከግማሽ በላይ ነጥብ ያስመዘገቡ ሲሆን አንዱ ባሕሪ (*"የመንግሥት ውጤታማነት"*) ከግማሽ በታች ነጥብ አስመዝግቧል።

የሚከተለው ቻርት የሲዳማ ክልል በሁሉም መገለጫዎች (Indicators) ያገኘውን አጠቃላይ ውጤት ያሳያል።

**የዴሞክራሲያዊነት መገለጫዎች አጠቃላይ ውጤት (የሲዳማ ክልል አስተዳደር)**




ቻርት 1: የሲዳማ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር የዴሞክራሲያዊነት ባሕርያት አጠቃላይ ውጤት

98 የቡድን ውይይት 4
99 የቡድን ውይይት

ከዚህ በታች የተቀመጠው ሠንጠረዥ ደግሞ የሲዳማ ክልል መስተዳደርን የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ለመለካት የተቀመጡ ባሕሪያት እና መገለጫዎች ያስመዘመገቡትን ውጤት እና ድምር በዝርዝር ያሳያል።

| የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ | የባሕሪዎቹ መገለጫዎች | | | | | ድምር | የተሰናኘ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መ1 | መ2 | መ3 | መ4 | መ5 | | |
| የመንግሥት ውጤታማነት | 25 | 22 | 24 | 18 | 23 | 112 | 2.49[100] |
| ቁጥጥርና ሚዛን | 25 | 23 | 24 | 17 | 27 | 116 | 2.58 |
| የዜጎች ነፃነቶች | 24 | 23 | 42 | 32 | 29 | 150 | 3.33 |
| ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያ መብቶች | 23 | 31 | 21 | 30 | 20 | 125 | 2.78 |
| የኀዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | 37 | 36 | 30 | 36 | 27 | 166 | 3.69 |
| ድምር | 134 | 135 | 141 | 133 | 126 | 669 | 4.95[101] |


**ሰንጠረዥ 4:** የሲዳማ ክልል መስተዳደር ሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪያት እና መገለጫዎች ዝርዝር ውጤት

በዚሁ መሠረት በሁሉም የዴሞክራሲ ባሕርያት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ያገኘው ድምር ውጤት **669** ወደ *ተሰናኘ ድምር* ሲቀየር **4.95** ይሆናል፤ በዚህም መስተዳድሩ ቢጫ ምድብ ("ግትር"[102]) የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ላይ ያርፋል።

100 የእያንዳንዱ የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ "የተሰናኘ ድምር" የሚሰላው ድምር ነጥቡ በ45 (ዘጠኝ መጠይቅ * 5 ነጥብ) ተካፍሎ ነው። በዚህ የተሰናኘ ድምር የሚገኘው ነጥብ ከ1 እስከ 5 ነው።

101 የተሰናኘ ድምር ጠቅላላ ውጤት የሚሰላው ((ጠቅላላ ድምር -225)*2/225)+1)። በዚህም መሠረት የሚገኘው ውጤት ከ1 እስከ 9 ነው። ይህ ውጤት የመስተዳድሩን ምድብ ለመለየት ይጠቅማል።

102 የተሰናኘው ድምር ጠቅላላ ውጤት የሚሰላው ከ1 እስከ 9 ነው። በዚህ መሠረት ከ(1-3) ነጥብ ያገኙት "አሉታዊ" ወይም ቀይ ምድብ ውስጥ ይገባሉ፤ ከ(3 በላይ እስከ 6) ነጥብ ያገኙት "ግትር" ወይም ቢጫ ምድብ ውስጥ ይገባሉ፤ እንዲሁም ከ6 በላይ እስከ 9 ነጥብ ያገኙት "ተራማጅ" ወይም አረንጓዴ ምድብ ውስጥ ይገባሉ።



# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መስተዳድር

## የመንግሥት ውጤታማነት

### የሕግ አውጪው ውጤታማነት

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕገ መንግሥት መሠረት በክልሉ ከፍተኛ የሥልጣን አካል የክልሉ ምክር ቤት ወይንም የሕግ አውጪው አካል ነው። በዚህም መሠረት የክልሉ ምክር ቤት አባላት ተገዥነት ለክልሉ ሕገ መንግሥት፣ ለሕዝብና ለሕሊናቸው እንደሆነ በክልሉ ሕገ መንግሥት ተደንግጓል[103]።

ይሁንና፥ የክልሉ ሕገ መንግሥት የክልሉ ምክር ቤት ከአስፈፃሚውም ሆነ ከሌሎች አካላት ጣልቃ ገብነት ሳይኖርበት ሊሠራ እንደሚገባው ምክር ቤቱን በተመለከቱ ድንጋጌዎች ሥር አላስቀመጠም።

ከዚህ በተጨማሪ፣ የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ አካል በገዢው ፓርቲ አማካይነት የበላይነት ያለው በመሆኑ፣ በተጨባጭ በሚታየው አሠራር መሠረት የክልሉ ምክር ቤት አባላት የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ የበታች ናቸው። በዚህም ሳቢያ፣ በተለይ የፓርቲና የመንግሥት መሥመር በግልጽ ባልተለየበት ስርዓት በፓርቲ የሚሰጡ አቅጣጫዎች (በውሳኔ ማዕከላዊነት ምክንያት) የምክር ቤቱ አባላት በምክር ቤቱ ውስጥ ለሚያደርጓቸው ውይይቶችም ሆነ ለሚያወጧቸው ሕጎችና ለሚያስተላልፏቸው ውሳኔዎች መሠረት በመሆን ያገለግላሉ። ይህም በምክር ቤቱ ገለልተኛ አሠራር ላይ ቀላል የማይባል ጫና ያሳድራል[104]። ይህ ደግሞ፣ መንግሥት የሚመሠርተው ከፍተኛ ድምፅ ያገኘ ፓርቲ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በድምፅ አሸንፎ መንግሥት የሚመሠርተው ፓርቲ በምክር ቤቱ ከፍተኛ ተወካይ ስለሚኖረው ቀጥተኛ ተፅዕኖ እንደሚኖር ማሳያ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም፥ ምንም እንኳን ምክር ቤቶች የሀብት ማሰባሰብን የተመለከቱ ሕጎችን የሚያወጡና ተፈፃሚነቱን የሚከታተሉ ቢሆኑም፥ ሀብት የሚያሰባስበውና ለተለያዩ ተቋማት በጀት የሚመድበውም የአስፈፃሚው አካል በመሆኑ፥ ምክር ቤቱ ይህንን በብቃት የሚቆጣጠርበት በቂ በጀት፣ ግልጽና አስገዳጅ አሠራር እንዲሁም በቂ የሰው ኃይል የለውም።

103 የክልሉ ሕገ መንግሥት - http://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/Benishangul-Gumuz%20consolidated%20laws%20-%20V%201.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

104 የቡድን ውይይት 5

## የሥራ አስፈፃሚው ውጤታማነት

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕገ መንግሥት ለአስፈፃሚ ኮሚቴና ለርዕሰ መስተዳድሩ ከፍተኛውን የአስፈፃሚ ሥልጣን ያጎናፅፋል። አስፈፃሚውም ለክልሉ ምክር ቤት (ሕግ አውጪ ተቋም) ተጠሪ እንደሆነ ይደነግጋል። ሆኖም ግን፥ በክልሉ ያለው የአስፈፃሚ በምርጫ በተዋቀረ ምክር ቤት የተመረጠ/የተሰየመ ባለመሆኑ፥ በክልሉ ያለው አስፈፃሚ አካል ለውጤታማነት የሚያበቃው ዝግጁነት የለውም[105]።

ከዚህ ባለፈም፥ በክልሉ ባሉ የፖለቲካ ፍላጎቶች ምክንያት ከፍተኛ ጫና ያለበት ክልል ነው። በተለይ ክልሉን ከሚያጎራብቱ የአማራና የኦሮሚያ ክልሎች ፖለቲካዊ ፍላጎቶች የሚመነጩ ጫናዎች የክልሉን አስፈፃሚ አካል በከፍተኛ ጫና ውስጥ ይከቱታል[106]። ከዚህ በተጨማሪም፥ ከክልሉ ፀጥታ መደፍረሶች፥ ማለትም ተደጋጋሚ ጥቃቶች፥ በትጥቅ የታገዙ አመጾችና ግጭቶች ጋር በተያያዘ በክልሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች፣ በፌደራል መከላከያ ሠራዊት የበላይነትና ከክልሉ የጸጥታ አካላት ጋር በቅንጅት ተፈጻሚ የሚደረጉ የሰዓት እላፊ ገደቦችና የኮማንድ ፖስት መዋቅሮች በመኖራቸው፣ የክልሉ ሥራ አስፈፃሚ በተለይ የክልሉን የፀጥታ ሥራ በተመለከተ ሚናው አነስተኛ ነው[107]።

በክልሉ ያለው ለም መሬትና ትልልቅ እርሻዎች እንዲሁም እንደ ወርቅ ያሉ ውድ ማዕድኖችን በመፈለግና እንዳንዴም ከመደበኛ ወይም ሕጋዊ አሠራር ውጪ ማዕድኖችን በማውጣት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተለያዩ ፍላጎቶች ስለሚኖሯቸውም በክልሉ መንግሥት ላይ ጫና ያሳድራሉ። እንደማሳያም በ2015 የክልሉ መንግሥት ከባለብቶችና ከጨረታ ሒደቶች ጋር የተያያዙ 70 የሙስና ጥቆማዎችን ተቀብሎ ሲያጣራ እንደነበርና፥ ወንጀል በሆኑ 52 ድርጊቶች የአስፈፃሚው አካል ሥራ የሆኑ እንደ ጨረታ ያሉ ሒደቶች መስተጓጎላቸውን የክልሉ መንግሥት አስታውቆ ነበር[108]።

## የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ውጤታማነት

በሌሎች ክልሎች እንደሆነው ሁሉ፥ የሲቪል ሰርቪስ የክፍያና የማበረታቻ ስርዓት በቂ ስላልሆነ አገልግሎታቸው ብቃትን መሠረት ያደረገ፥ ጣልቃ ገብነት የሌለውና ውጤታማ ነው ለማለት ያዳግታል[109]። የክልሉ የሲቪል ሰርቪስ በአዋጅ የተቋቋመና የመቋቋሚያ መርሖዎችና የአሠራር ደንቦች ያሉት ቢሆንም፥ አጠቃላይ የማኅበረኢኮኖሚ ሁኔታው እና የፖለቲካ ባሕሉ ሲቪስል ሰርቪሱ በቀጣይነት እንዳይሻሻል በተለይ ብቃትን መሠረት ያደረገ (merit based) አሠራር እንዳይኖር በማድረግ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ከዚህ ባለፈም፥ በብቃት እንኳን የሚያዙ ኃላፊነቶች ቢኖሩም ለጣልቃ ገብነት እንዲረዳ ሹመት እንዲታከልበት ይደረጋል - ይህ በተለይ ከምክትል ቢሮ ኃላፊዎች በታች ላሉ ኃላፊነቶች የተለመደ እየሆነ መጥቷል[110]።

105 የቡድን ውይይት 5
106 የቡድን ውይይት 5
107 የቡድን ውይይት 5
108 https://www.ena.et/web/amh/w/amh_2655092 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)፤ የቡድን ውይይት 5
109 የቡድን ውይይት 5
110 የቡድን ውይይት 5

ሆኖም ግን፥ በክልሉ ያለው ጎዳጣንን በሲቪል ሰርቪስ የመወከል የኮታ አሠራር መዋቅራዊ በሆኑ ችግሮች ውስጥ ያለፉና እያለፉ ያሉ የክልሉ ብሔሮች በሲቪል ሰርቪስ እንዲወከሉ የሚያደርግ በመሆኑ በበጎ የሚነሳ ነው። ሲቪል ሰርቪሱ ግን እንደ ቢሮክራሲ ውጤታማ ነው ለማለት ያስቸግራል፤ ለምሳሌ የክልሉን ፀጥታ ከማስጠበቅ አንፃር ውጤታማ አይደለም[111]።

## የፀረ ሙስና ውጤታማነት

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሙስና መከላከያ መሣሪያዎች ከሆኑ መንገዶች አንዱ የሆነው የፀረ-ሙስና የሕግ ማዕቀፍና ተቋማዊ መዋቅር የተዘረጋ ቢሆንም፥ ሙስናና ብልሹ አሠራር ግን በክልሉ በስፋት ይስተዋላሉ[112]። በ2015 የክልሉ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ባስጠናው ጥናት፥ ከግዥ ብቻ ከሚመደበው በጀት ከ15-30 በመቶ የሚሆነው እንደሚመዘበር አስታውቋል። ይሁንና የክልሉ መንግሥት ያወጣቸው ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ባለመተግበራቸው ሙስናን መከላከል እንዳልተቻለና፥ እነዚህን ሕጎች መተግበር ከተቻለ ሙስናን መከላከል እንደሚቻል በጥናቱ ተመላክቷል[113]። ሆኖም ግን፥ አገር ዐቀፍ በሆኑ የፀረ-ሙስና ዘመቻዎች በክልሉ ከ28 ሚሊዮን ብር በላይና 100ሺሕ ሔክታር መሬት ማትረፍ ተችሏል[114]።

እነዚህ ውጤቶች ግን የሰፊው ችግር ማሳያ ቅንጫቢዎች ናቸው እንጂ አሁንም ቢሆን በክልሉ ያሉ የፀረ-ሙስና ሕጎች ወደ መሬት ወርደው አልተተገበሩም በተለይም የበጀት አስተዳደር፥ ሀብት ያለባቸው ሥፍራዎች አስተዳደርና የሰዎች ቅጥር ላይ ሰፊ ችግሮች ይስተዋላሉ። በአስፈፃሚ አካላት ቤተሰባዊ ትስስሮችም ይስተዋላሉ።[115] የሙስና መከላከያ መንገድ አንዱ አጥፊዎችን ልሕግ ማቅረብ እና ተጠያቂ ማድረግ ሲሆን ይህም አሠራር በክልሉ ዝቅተኛ ነው።

## ያልተማከለ አስተዳደር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕገ መንግሥት በክልሉ የክልል፣ የዞን፣ የወረዳና የቀበሌ መዋቅሮች እንደሚኖሩ የሚደነግግ ሲሆን፥ የእነዚህም መዋቅሮች አደረጃጀት፣ ሥልጣንና ኃላፊነትን ይደነግጋል። እያንዳንዱ መዋቅርም ምክር ቤቶችና አስፈፃሚ አካል ያሉት ሲሆን፥ ከታች ያሉት መዋቅሮች ወደላይ ካሉት መዋቅሮች ጋር የተጠብርና የተጠሪነት ግንኙነትም በሕገ መንግሥቱ ተመሥርቶላቸዋል።[116]

---

111 የቡድን ውይይት 5

112 የቡድን ውይይት 5

113 https://www.facebook.com/bgrseacc/posts/pfbid02WZBdDvQtL4Zx5b88EAMakp8uuf6EcegKFcQN4JfgvNzHHjabfZxfdhHHhu8aSSkyl?__cft__[0]=AZW-7MSSgyef7DdJ5qamiRpufms5qDeoNMuWVAJBDIE5FIjFrRJstxBWYXO2u51qwwNYKPwljoq_jXqxmu4Y-jEZgCyoEkC29-KA2eHDk4ItAfHIR1rqFaZVEPPExWqQpPvdnjo1FM5ZUywDNwRVRD9R6CJoDgQmZsxNU7gYY7ITXKqJcUW8ZJSTR6ufNqkx2OcbY4XLx1TQUZDZ5D0L5KCo&__tn__=%2CO%2CP-R (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

114 https://www.facebook.com/bgrseacc/posts/pfbid02qTKrS6gpNXpXewvveuUTB5v2MdGP8TLJHMSKoFa2F6iKKsAykfQQZFxT4vSytqf9l?__cft__[0]=AZX-EYmli2c8yU4ZhkFqzZo1PYQl_CSpLCyIDM5m-7eHbxJzokPu0EU92BaWLJdx-fU-jwInzWCglmMagCUldXfT9C96w4CpVSKRhfDseTgYmpiEhr0fMGjfuF0jofP6FFsIhupH68XIVue4eiCd45anUCC-y1uH6may4cTf2rVnYSkOEZndKRgCQlu-63MsfgADf54jHkBQf_labSRGuRZR&__tn__=%2CO%2CP-R (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

115 የቡድን ውይይት 5

116 የክልሉ ሕገ መንግሥት - http://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/Benishangul-Gumuz%20consolidated%20laws%20-%20V%201.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

ሆኖም ግን፥ ከዞን እስከ ቀበሌ ባለው መዋቅር ያለው የሰው ኃይልና ሀብት የማሰባሰብ አቅም ውሱንነት ሳቢያ፥ የክልል ጫና ሥር ይወድቃሉ። የክልል መዋቅሮች ለታችኛው መዋቅር በጀት የሚመድቡ ስለሚሆኑም በታችኞቹ መዋቅሮች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥርና "ጥርነፋ" ያከናውናሉ።[117] ለዚህ ደግሞ ትልቁን ድርሻ የሚጫወተው የፓርቲ የውሳኔ ማዕከላዊነት ሲሆን፥ በተዋረድ ሲታይ፥ በክልል ያሉ የሥራ ኃላፊዎች ለታችኛው መዋቅር የሥራ ኃላፊዎች የበላይ ናቸውና በሕግ የተቀመጡ ያልተማከለ አስተዳደር መዋቅሮች በተግባር ማዕከላዊ እንዲሆኑ ያደርጋሉ።

ስለዚህም፥ ያልተማከለ አስተዳደራዊ ስርዓት በሕግ ተደንግጎ ቢኖርም፥ በተግባር ግን የበጀትና የሌሎች ውሳኔዎች ማዕከላዊነት ጎልቶ ይታያል።[118]

> እነዚህን እውነታዎች ከግንዛቤ በማስገባት ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከ**45** ከፍተኛ ነጥብ **(23)** ያገኘው መገለጫ ነጥብ *"የሕግ አውጪው ውጤታማነት"* ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(16)** ያስመዘገበው ደግሞ *"የፀረ - ሙስና ውጤታማነት"* ነው። በአጠቃላይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልል *የመንግሥት ውጤታማነት* ድምር ውጤት **101** ነው።

ይህ ማለት ክልሉ በመንግሥት ውጤታማነት የዴሞክራሲያዊነት ባሕርይ ያስመዘገበው ውጤት ከ225 ከፍተኛ ነጥብ 101 ብቻ ነው።

## ቁጥጥር እና ሚዛን

### የሕግ አውጪው ሥልጣን

የሕግ አውጪው በሕግ የተመሠረቱ የቁጥጥርና ሚዛን ሥራዎች የሚሠራባቸው ቋሚ ኮሚቴዎችን የማቋቋም ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን፥ በሕገ መንግሥቱ እንደተደነገገው የክልሉን የኦዲትና የቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል[119]።

በዚህም መሠረት በተለይ ክልሉ ምክር ቤት የተቋቋሙ ቋሚ ኮሚቴዎች የክልሉን አስፈፃሚ አካላት በመጥራትና በመጎብኘት ግመገማ በማድረግ በጥንካሬና ድክመቶቻቸው ላይ ግብረ መልስ የሚያቀርቡ ናቸው። ካሁን ቀደም በነበረው አሠራር የቢሮ ኃላፊዎችን ሥራዎች መገምገም ከሥልጣን ተዋረድ አንፃር አስቸጋሪ የነበረ ቢሆንም፥ በቅርቡ በተደረገ ማሻሻያ ግን የቋሚ ኮሚቴ አባላት በአፈ ጉባዔ ጽሕፈት ቤት ቢሮ ተሰጥቷቸው በካቢኔ ማዕረግ ስለሚሾሙ የቁጥጥርና ክትትል ሥራቸውን ለመሥራት የሚያስችላቸው አደረጃጀት ተፈጥሯል[120]።

117 የቡድን ውይይት 5
118 የቡድን ውይይት 5
119 የክልሉ ሕገ መንግሥት - http://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/Benishangul-Gumuz%20consolidated%20laws%20-%20V%201.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
120 የቡድን ውይይት 5

ሆኖም ግን ግብረ መልስ የሚሰጠው የአስፈፃሚ አካል አስተያየቶችን ወስዶ ይተገብራል ለማለት ያስቸግራል። አንዱ ሳንካ የፓርቲና የመንግሥት መሥመሮች መደበላለቅ ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ የበላይ የአስፈፃሚ አካላት የሥራ ግምገማ ውጤቶችን እና ግኝቶችን ወስደው ለለውጥ ሲሠሩ እምብዛም አይታይም። ስለዚህም፥ ያልተፈፀሙ ጉዳዮችን የመገምገምና ተገቢውን ተጠያቂነት የመተግበር ውሱንነቶች አሉ።[121]

## የፍርድ ቤት ነፃነት

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕገ መንግሥት የዳኝነትን አካል በሚያቋቁመው አንቀፅ ሥር "ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል"[122] ሲል ይደነግጋል።

ሆኖም ግን፥ በክልሉ ያለው የዳኝነት ሥራ እንቅፋት የሞላበት፣ እንዲሁም አንድን ወገን ለማጥቃት መጠቀሚያ የሚሆኑ ተቋማት እንደሆኑ ባለሙያዎች ይከራከራሉ። በዚህም ምክንያት ከፍተኛ ቅጣት የሚያስጥሉ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች በይግባኝ ወደ ፌዴራል ሲወሰዱ በብዛት ይሻራሉ አልያም ቅጣታቸው እጅጉን ያነሰ ይሆናል።[123] ስለዚህም፥ የክልሉ ፍርድ ቤቶች የፍትሕ ማረጋገጫ ከመሆን ይልቅ የፖለቲካ መጠቀሚያ ሆነው ሲያገለግሉ በስፋት ይስተዋላል።[124]

## የፍርድ ቤት ገለልተኝነት

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕገ መንግሥት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ገለልተኛ ሆነው እንዲቋቋሙ ይደነግጋል። ከዚህ በተጨማሪም የክልሉ የዳኝነት አካላት ምንም እንኳን ተቋማዊ አደረጃጀታቸው በሹመትና በአቀራረብ ከአስፈፃሚውና ከሕግ አውጪው አካላት ጋር የሚገናኙ ቢሆንም፥ ተቋማዊ ውሳኔዎችን የሚሰጥበት መዋቅር እንዲኖር የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይመሠርታል።[125]

## ነፃ ሚዲያ

በክልሉም ሆነ ከክልሉ ውጪ በክልሉ ሁነቶች ላይ ትኩረት አድርገው የሚሠሩ ገለለትኛ የመገናኛ ብዙኃን የሉም። እንደ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ያሉ ተቋማት በክልሉ የሚገኙ ቢሆንም ግን ለመንግሥትና ለገዢው ፓርቲ ያደሉና የሐሳብ ብዝኃነት ውክልና የሌለበት ነው።

በተጨማሪም፥ በክልሉ ያለው የፀጥታ ችግር የመገናኛ ብዙኃን መንቀሳቀስና መሥራት ቢፈልጉ እንኳን አስቻይ ሁኔታን ስለማይፈጥር ከመንግሥት ብቻ የሚያገኟቸውን መረጃዎችን ያስተጋባሉ። የክልሉ የመገናኛ ብዙኃንም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የሚገኙ ስለሆኑ የሙያዊ ብቃትና የሕዝብን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ ትችቶችን በማስተናገድ ረገድ ውሱንነቶች አሉባቸው[126]።

121 የቡድን ውይይት 5

122 የክልሉ ሕገ መንግሥት - http://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/Benishangul-Gumuz%20consolidated%20laws%20-%20V%201.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

123 የቡድን ውይይት 5

124 የቡድን ውይይት 5

125 የክልሉ ሕገ መንግሥት - http://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/Benishangul-Gumuz%20consolidated%20laws%20-%20V%201.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

126 የቡድን ውይይት 5

መገናኛ ብዙኃን ሙስናን እንደመታገል ያሉ የማኅበረሰብ ጥያቄዎችን ለመመለስ ሚናቸው ወሳኝ እንደሆነ የሚታወቅ ቢሆንም[127]፥ በዚህ ረገድ በክልሉ ያለው የመገናኛ ብዙኃን ሚና አነስተኛ።

## ተሟጋች ቡድኖች

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተለያዩ ዘርፎች የሚንቀሳቀሱ ከ22 ያላነሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚገኙ ሲሆን[128]፥ እነዚህ ድርጅቶች በስፋት የክልሉን አስተዳደር ውጤታማነት የሚፈትሹና የሚተቹ እንዲሁም ብዝኃነት ያላቸው ድርጅቶች አይደሉም። ብዙኃኑ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም የመንግሥት አስተዳደር (ገቨርናንስ) ፥ አድቮኬሲና የሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚሠሩ ሳይሆኑ፥ በተለያዩ የልማት ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ናቸው።[129]

በክልሉ በሚታዩ ኢ-ፍትሐዊ አሠራሮች ድምፃቸውን የሚያሰሙና የሚሞግቱ ድርጅቶች የሌሉ ሲሆን፥ በዚህም ሳቢያ በክልሉ የሚታዩ ችግሮች እየተባባሱ መጥተዋል።[130] ሆኖም፥ እንዲህ ያሉ ውሱን የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም፥ ለዚህ ሥራ የሚፈቅድ የሕግ ማዕቀፍ መኖሩና ከ10-15 በሚደርሱ ዘርፎች የሚሠሩ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በመኖራቸው በአወንታዊነት የሚታይ ነው።[131]

> እነዚህን ርዕሰ ጉዳዮች ከግምት በማስገባት ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከመገለጫዎቹ ከ45 ከፍተኛ ነጥብ **(24)** ያገኘው መገለጫ ***“ተሟጋች ቡድኖች”*** ሲሆን፥ ዝቅተኛ ነጥብ **(13)** ያስመዘገበው ደግሞ ***“ነፃ ሚዲያ”*** ነው። በአጠቃላይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መስተዳድር የቁጥጥር እና ሚዛን ድምር ውጤት **93/225** ነው።

# የዜግነት ነፃነቶች

## ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት እና በክልሉ ሕገ መንግሥት መሠረት ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት የተረጋገጠ[132] ቢሆንም፥ ወደ ተግባር ሲመጣ ግን ተግዳሮቶች ይታያሉ። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት ተግባራዊ ገደብ ስላለ ሰዎች በድብቅ ሥሞች በመጠቀም በማኅበራዊ ትስስር ገፆች ላይ ሐሳባቸውን ያስተጋባሉ። ይህም የሆነበት ምክንያት ራሳቸውን ገልጠው ቢናገሩ መዘዝ ስላለው ነው[133]።

---

127 https://m.facebook.com/541629952535552/posts/6206016862763471/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
128 https://acso.gov.et/wp-content/uploads/2021/04/Local.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
129 የቡድን ውይይት 5
130 የቡድን ውይይት 5
131 የቡድን ውይይት 5
132 የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት https://constitutii.files.wordpress.com/2013/02/amh-constitution.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)፤ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕገ መንግሥት ሕገ መንግሥት http://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/Benishangul-Gumuz%20consolidated%20laws%20-%20V%201.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
133 የቡድን ውይይት 5

ይህ እያደገ የመጣ ልማድ ቢሆንም ቅሉ፥ በተደጋጋሚ በሚከሰቱ ግጭቶችና አገራዊ ሁነቶች ሳቢያ የሚጣሉ የኢንተርኔት ገደቦች ሐሳብን በመግለጽ ነፃነት ላይ የማይስተባበል ተፅዕኖ አላቸው። ለአብነትም በ2015 መጨረሻ አካባቢ በአማራ ክልል በተከሰተው ግጭት ሳቢያ የኢንተርኔት አገልግሎት በመላ የአማራ ክልል ሲቋረጥ[134] በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መተከልና ዞን እና አካባቢውም ተዘግቷል።[135]

ሐሳብን በነጻነት የመናገር መብት በሕግ የተፈቀደና ዕውቅና የተሰጠው ቢሆንም፥ ሰዎች ሐሳባቸውን በድፍረት ለመናገር ድፍረቱ እንዳይኖራቸው ሆነው ነው የሚኖሩት።[136]

## የመደራጀት ነፃነት

በክልሉ ለተለያዩ ዓላማዎች መደራጀትን የሚከለክሉ የሕግ ማዕከቀፎች የሌሉና የመደራጀት፣ የመሰብሰብና የመቃወም ነፃነት በድንጋጌ የተረጋገጠ[137] ቢሆንም፥ በትግበራ ላይ ግን ሰፊ ክፍተቶች ይታያሉ። የዚህ ችግር ዋና መንስዔ በክልሉ ያሉ የፖለቲካ አለመረጋጋቶች እና ውጥረቶች እንዲሁም ረጅም ጊዜ የቆዩ የትጥቅ ግጭቶች ሲሆኑ ናቸው። በዚህና በሚደርሱባቸው ማዋከቦች ምክንያት በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጽሕፈት ቤት ለመክፈትና በሕግ የሚጠበቅባቸውን ዓመታዊ ጉባዔ ለማድረግ አልቻሉም።[138]

በክልሉ በመንግሥት ዕውቅና አግኝቶ የተካሔደ ሰላማዊ ሰልፍ በ2015 እንዳልነበረና ይህና መሰል መብቶቻቸው የተገደቡባቸው ስብስቦች በክልሉ የትጥቅ ትግልን አማራጭ እንዲያደርጉ አስገድዷቸዋል የሚሉ አስተያየቶች በስፋት ተንሸራሽረዋል[139]። በክልሉ የሚንቀሳቀሱ በርካታ ታጣቂዎች መኖራቸው የዚህ ችግር ማሳያ ከመሆኑም ባሻገር፥ የችግሩ ምንጭም በመሆን የክልሉን አለመረጋጋት አዙሪት ውስጥ ከቷዋል። ምክንያቱም፥ በርካታ ታጣቂዎች ባሉበት ስፍራ ሰላምና ደኅንነትን አረጋግጦ የመደራጀት ነፃነትን ማስከበር አዳጋች ስለሚሆን ነው።[140]

ከዚህ ባለፈም፥ በክልሉ ሕገ መንግሥት "የክልሉ ባለቤቶች" ተብለው የተለዩ ብሔሮች ስላሉና የአገሪቱ የፖለቲካ መዋቅር በብሔር መደራጀትን እንደ አስተዳደራዊ መንገድ ተቀብሎ እየሠራበት ባለበት ጊዜ ይህ ድንጋጌ የዜጎችን የመደራጀት መብት የሚያኮስስ ነው።[141]

## የሃይማኖት ነፃነት

በሃይማኖት ነፃነት ረገድ ክልሉ በሕግም በተግባርም መልካም የሚባል ተቀባይነት ያለው ሲሆን፥ የክልሉ ሕገ መንግሥት የሃይማኖት ነፃነትን የሚገድብበት ሕግም ሆነ አሠራር የለውም። በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የሃይማኖት ተቋማትም ያለ ገደብ ሃይማኖታዊ ክንውኖቻቸውን ይፈፅማሉ።[142]

134 አክሰስ ናው https://www.accessnow.org/press-release/amhara-internet-shutdown/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
135 የቡድን ውይይት 5
136 የቡድን ውይይት 5
137 የክልሉ ሕገ መንግሥት፣ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት
138 የቡድን ውይይት 5
139 የቡድን ውይይት 5
140 የቡድን ውይይት 5
141 የቡድን ውይይት 5
142 የቡድን ውይይት 5

ይሁንና፥ ሃይማኖታዊ ልዩነቶች ለግጭት ማነሳሻነት እንደሚውሉ መንግሥት ጭምር በግልጽ የተናገረው[143] ከመሆኑ ባሻገር፥ በሃይማኖታዊ ነፃነት ላይ አሉታዊ ጫና ይኖረዋል።

## የመንቀሳቀስ ነፃነት

በ2015 በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሞት የነበረው የነፃነት ዓይነት የዜጎች ከቦታ ወደ ቦታ የመዘዋወር ነፃነት ሲሆን፥ በተለይም በክልሉ ለዓመታት የዘለቀው ግጭት ለዚህ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል። ዜጎች በምድር ተሽከርካሪዎች የሚንቀሳቀሱባቸው መንገዶች በስፋት ለጥቃት ሲጋለጡ የነበረ ሲሆን[144]፥ ደኅንነቱ የተጠበቀው መንገድ የአየር ትራንስፖርት ብቻ ሆኖም ቆይቷል።[145] ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች የደኅንነት ሥጋት ስላለባቸው አስገዳጅ ከሆነ በአጀብ ነው የሚሔዱት።

ከዚህ በተጨማሪም፥ በሌላ ክልል የሚንቀሳቀሱ እንደ ኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት ያሉ ድርጅቶች ወደ ክልሉ በመዝለቅ ጥቃቶችን የሚሰነዝሩ ሲሆን፥ የዜጎችን የመንቀሳቀስም መብት በዚሁ መጠን ገድበውታል። ይህ የሆነበት አንዱ ምክንያትም በክልሉ ሲጣል የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅችና የሰዓት እላፊ ገደብ ናቸው።

## የግል ደኅንነትና ምሥጢር ጥበቃ

በክልሉ በሚታዩ ተደጋጋሚ ግጭቶችና ጥቃቶች ሳቢያ የዜጎች ደኅንነት አደጋ ላይ የወደቀ ሲሆን፥ ተደጋጋሚ የነበሩ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች እንዲሁም ኮማንድ ፖስቶች ለሕግ አስከባሪ አካላት በሚሰጧቸው የተለጠጡ ሥልጣኖች የዜጎች ደኅንነትና ምሥጢር ጥበቃ ነበር ለማለት ያዳግታል።[146]

የክልሉም ሆኑ በክልሉ ተፈፃሚነት ያላቸው የፌዴራል መንግሥት ሕጎች የዜጎችን ደኅንነትና ምሥጢር የሚጠብቁ ቢሆንም፥ በክልሉ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ግን የግል ደኅንነትና ምሥጢር መጠበቅም አስቸጋሪ አድርጎታል። በዘፈቀደ የሚታሰሩና የሚሰወሩ ሰዎችም በርካታ ናቸው።[147] የሚታሰሩ ሰዎችም በወታደራዊ ካምፖች የሚታሰሩ መሆናቸው ደግሞ ሌላኛው ተግዳሮት ነው።

> እነዚህ ከግምት ገብተው በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(37)** ያገኘው የዜግነት ነፃነቶች መገለጫ ***"የሃይማኖት ነፃነት"*** ሲሆን፣ ዝቅተኛው ነጥብ **(13)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ ***"ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት"*** ነው። በአጠቃላይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ክልል መስተዳድር ***"የዜግነት ነፃነቶች"*** ድምር ውጤት **112/225** ነው።

143 https://x.com/AbiyAhmedAli/status/1341350445651021826?s=20 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

144 https://addisstandard.com/news-eight-killed-16-injured-in-latest-attack-by-armed-group-in-benishangul-gumuz-despite-peace-agreement/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

145 የቡድን ውይይት 5

146 የቡድን ውይይት 5

147 የቡድን ውይይት 5

# ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች

## መሠረታዊ ፍላጎቶች

አሁንም ድረስ በክልሉ በሚታዩ ግጭቶችና ጥቃቶች ሳቢያ የመሠረታዊ አገልግሎቶች መስጫ ተቋማት ከጥቅም ውጪ ሆነዋል፤ ክልሉ ያሉትን መሠረተ ልማቶች አጥቷል። ቀድሞም ክልሉ በታዳጊ ክልሎች ዘርፍ የነበረ ቢሆንም መሻሻሎች እየታዩ ነበር። አሁን ግን በግጭቶቹ ምክንያት የከፋ ሆኗል።[148] ይህ በተለይ ስርዓተ ፆታዊ አንድምታ ያለው ሲሆን፥ ሴቶች ይበልጡኑ በመሠረታዊ ፍላጎቶች አለመሟላት ተጎጂ ናቸው።[149]

በክልሉ የተከሰቱ ተደጋጋሚ ግጭቶች በፈጠሯቸው መስተጓጎሎች ሳቢያም፥ ወደ ክልሉ የሚገቡ ሸቀጦችና ሌሎች መሠረታዊ ቁሳቁሶች ስለተቋረጡ በመሠረታዊ ፍላጎቶች ላይ ከባድ ጫና አሳድሯል።[150]

የጤና ተቋማት ተደራሽነት እጅግ ውሱን በመሆኑና በክክሉ የሚገኙ የጤና ተቋማት በግጭቶች የተጎዱ አልያም የግብዓት አቅርቦታቸው የተስተጓጎለ በመሆኑ በቂ የጤና አገልግሎቶች የሉም። በዞን ደረጃ ያሉ ሆስፒታሎች ውሱን ከመሆናቸው የተነሳ በግጭቶች የተጎዱ ሰዎችን በማከም ተጠምደዋል።

## የትምህርት ዘርፍ

በክልሉ ከሚገኙ 679 ትምህርት ቤቶች መካከል ከ270 በላይ በፀጥታ ችግሮች ወድመዋል[151]፥ ከ300,000 በላይ በክልሉ ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት መካከል 50,000 ያህሉ ከትምህርት ገበታ ቀርተዋል።[152]

ከዚህ በተጨማሪም፥ በትምህርት ቤቶቹ የተሟላ መሠረተ ልማት ባለመኖሩ፥ አካል ጉዳተኞች አሁንም በስፋት ከትምህር ገበታ የተገለሉ ሲሆኑ፥ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤንሻንጉል ጉሙዝ ከሁሉም የአገሪቱ ክልሎች ያነሰ አፈፃፀም አለው[153]።

በክልሉ የመንገድ መሠረተ ልማት በተለያዩ ምክንያቶች ያላደገ እንዲሁም በግጭቶች ምክንያት የወደመ በመሆኑ ከፍተኛ የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት አለ። ስለዚህም ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ለመድረስ ረዥምና አስቸጋሪ መንገዶችን መጓዝ ይጠበቅባቸዋል።

148 የቡድን ውይይት 5

149 https://sihanet.org/press-statement-ethiopian-women-speak-out-on-conflict-and-peace-in-the-country/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

150 https://epo.acleddata.com/2022/11/17/%E1%8A%A2%E1%8D%92%E1%8A%A6-%E1%88%B3%E1%88%9D%E1%8A%95%E1%89%B3%E1%8B%8A-%E1%8A%A8%E1%8C%A5%E1%89%85%E1%88%9D%E1%89%B5-26-%E1%88%85%E1%8B%B3%E1%88%AD-2-2015/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

151 https://moe.gov.et/ViewNews/168 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

152 https://www.ethiopianreporter.com/120044/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

153 https://moe.gov.et/storage/Books/ESAA%202014%20EC%20(2021-22%20G.C)%20Final.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)፤ የቡድን ውይይት 5

## የስርዓተ ፆታ እኩልነት

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የስርዓተ ፆታ እኩልነት በሕግ የተረጋገጠ ቢሆንም፥ በክልሉ የታዩ ግጭቶች ዜጎችን ለፆታ-ተኮር ጥቃቶች አጋልጠዋቸዋል።[154]

ከተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች በግጭቶች ምክንያት ተፈናቅለው በጊዜያዊ መጠለያዎች በሚገኙ ዜጎች መካከል የሚሰሙ የፆታ ተኮር ጥቃቶች አሉ።[155] ይሁንና፥ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው ለግጭት ተጋላጭነትና እኩል የትምህርትና የሥራ ዕድሎች ያልተመጣጠኑ ናቸው። በዚህም ምክንያት፥ በክልሉ እንደ ቀድሞው ሁሉ አሁንም ሴት መሆን ለተለያዩ ጥቃቶች የሚያጋልጥ ነው።[156] ከዚህ ባለፈም፥ ባሕላዊ የፆታ መስተጋብሮች በሴቶች ላይ ጫና ያሳድራሉ። በክልሉ በዝቅተኛ ክፍያ አነስተኛ የወርቅ ማዕድን ቁፋሮ ከተሰማሩ ሠራተኞች መካከል ሴቶች 70 በመቶ የሚሸፍኑ[157] ቢሆኑም፥ በቤት ውስጥም ከፍተኛ የሥራ ጫና አለባቸው። ይህም፥ ከውጭ የሚያገኙትን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት በሕይወታቸው ላይ እምብዛም ለውጥ እንዳያመጣ አድርጓል።[158] ስለዚህ መዋቅራዊ የሆኑ የስርዓተ ፆታ ችግሮች በክክሉ እንዳሉ ማመላከቻዎች አሉ።

## የግል ንብረት ጥበቃ

ልክ እንደ ሌሎቹ ክልሎችና ሌሎች መብቶች ሁሉ፥ ንብረት ለማፍራትና ግለሰቦች በተናጠልም ይሁን በግል ለሚያፈሩት ንብረት ጥበቃ የሚነፍግ የሕግ ማዕቀፍም ሆነ ፖሊሲ የለም። በክልሉ በተደጋጋሚ በተከሰቱ ግጭቶች በርካታ ንብረቶች የወደሙ ሲሆን፥ የአሶሳ ዩኒቨርሲቲ ባጠናው ጥናት በክልሉ በተከሰቱ ግጭቶች 79 ቢሊዮን ብር የሚገመት ንብረት የወደመ ሲሆን፥ ከዚህ መካከል በ44 ቢሊዮን ብር የተገመተ 16 ሚሊዮን ኩንታል ሰብል ይገኝበታል። ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት፥ በክልሉ በግጭቶች ሳቢያ 43,640 ቤቶችም ወድመዋል።[159]

ስለዚህም፥ በ2015 የክልሉ መንግሥት የዜጎችን ንብረቶች ከማስጠበቅ ረገድ ሰፊ ተግዳሮቶች ታይተውበታል።

## የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የኢኮኖሚ መመጣጠን በተለያዩ መንገዶች የሚገለጥ ቢሆንም፥ በደምሳሳው የፆታና የፖለቲካ ሥልጣን የበላይነት ለዚህ ትልቁን ሚና ይጫወታሉ። በተለይ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው የኢኮኖሚ ልዩነት እንዲሁም የዕድል አለመመጣጠን ከፍተኛ ነው።[160]

በፖለቲካ ምክንያት ያለው አለመመጣጠን የሚመነጨው ፌዴራሊዝሙ ባልዳበረ የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ ቀዳሚው የማምረቻ ግብዓት የሆነውን መሬት ባለቤትነት ከብሔር ጋር ማስተሳሰሩ ነው። የአካባቢው እጅግ ባሕላዊ የግብርና አሠራር በክልሉ ማኅበረሰቦች ዘንድ ከፍተኛ የሀብት ልዩነት የፈጠረ ሲሆን፥ ቴክኖሎጂ ያላቸው በትንሽ መሬት ብዙ ምርት ማምረት ይችላሉ።

154 https://reliefweb.int/report/ethiopia/gender-based-violence-area-responsibility-ethiopia-secondary-data-review-february-2023#:~:text=The%20conflicts%20in%20northern%20Ethiopia,HRP%2C02%2F2023 (ጥቅምት 2016 የተገኘ)
155 የቡድን ውይይት 5
156 https://cusointernational.org/stories/creating-equal-access-to-education-in-ethiopia/ (ጥቅምት 2016 የተገኘ)
157 https://cirdisumm.org/wp-content/uploads/2022/07/Opportunities-for-women-in-ASM_Final-Report.pdf (ጥቅምት 2016 የተገኘ)
158 የቡድን ውይይት 5
159 https://www.thereporterethiopia.com/26461/ (ጥቅምት 2016 የተገኘ)
160 የቡድን ውይይት 5

በዚህ ላይ በክልሉ ያለው የተራዘመ የፀጥታ ችግር ለህብት አለመመጣጠን ስር መስደድ ትልቁን ሚና ተጫውቷል። እነዚህ ግጭቶችን የሚመግቡ የሕገ ወጥ ድንበር አቋራጭ ንግዶችና ሌሎች ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎች የክልሉን የሀብት ልዩነትን አስፍተዋል።[161]

ወርቅና እብነ በረድ ያለባቸው አካባቢዎች ያለው የሀብት መጠን ከሌሎች አካባቢዎች የተሻለ ሲሆን፥ በስፋት በግብርና ላይ የተመረኮዘ የኑሮ ዘይቤ ያላቸው አካባቢዎች የሀብት ምጣኔያቸው አናሳ ነው።

> በእነዚህ መመዘኛዎች መሠረት ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ ከፍተኛውን ነጥብ **(29)** ያገኘው መገለጫ *"የግል ንብረት ጥበቃ"* ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(20)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"መሠረታዊ ፍላጎቶች"* ነው። በአጠቃላይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል *መንግሥት "ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች"* ድምር ውጤት **122/225** ነው።

ይህም ክልሉ አሁንም አማካይ ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያሳየን ሲሆን፥ በተለይ ግጭቶችና ጥቃቶች በክልሉ ላይ ያደረሱት ጫና ከፍተኛ እንደሆነ የሚያመላክት ነው። ከፍተኛ ውጤት የተባለው የግል ንብረት ጥበቃ ራሱ ከአማካይ በታች ነው ያገኘው።



## የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

### የኅዳጣን ብሔረሰቦች ነፃነት

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ተሰባስበውና ተበታትነው የሚገኙ ኅዳጣን የሚገኙ ሲሆን፥ በስፋት የብሔር ኅዳጣን ማዕከላዊውን የፖለቲካ ክርክር መድረክ ይይዛሉ። እነዚህ ኅዳጣን በክልሉ የባለቤትነት መብት በሕገ መንግሥት ስለተነፈጉ እንደ ሌላው የክልሉ ማኅበረሰቦች እኩል ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር አይችሉም የሚል ክርክር ቢኖርም፥ በሕገ መንግሥቱ የክልሉ ባለቤቶች ተብለው ከተዘረዘሩ ብሔሮች ውጪ ያሉ ማኅበረሰቦች በስፋት በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ራሳቸውን ያስተዳድራሉ።[162] በተለይ በወረዳ ደረጃ ያሉ መዋቅሮች ተሰባስበው የሚኖሩ ብሔሮች ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ።

በአንድ አካባቢ የሚኖሩ የአማራና የአዊ ብሔረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ አይደለም የሚል የክርክር የሚነሣ ቢሆንም፥ ለክልሉ መንግሥት ቀርቦ የተከለከለ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ በሌለበት ይህ መከራከሪያ ልክ አይደለም የሚሉም አሉ። ሆኖም ግን፥ በክልልና በዞን ምክር ቤቶች በቂ ውክልናን የማግኘት ጥያቄዎች አሁንም በስፋት ይነሣሉ።[163]

161 የቡድን ውይይት 5
162 የቡድን ውይይት 5
163 የቡድን ውይይት 5

## የጎዳጣን መብቶች

በዚህ ሥር ጎዳጣን በሚደረግባቸው ያልተገባ ገደብ የባሕሎቻቸውንና የእምነቶቻቸውን እሴቶች የመተግበርና የማስተዋወቅ መብቶቻቸው የተቃኘ ሲሆን፥ በክልሉ የሚኖሩ በተለይ የባህል ጎዳጣን እምነቶቻቸውንና ባህሎቻቸውን እንዳያስተዋውቁ የተጣለ የሕግም የሆነ የፖሊሲ ገደብ የለም። ከዚህ ባለፈም፥ ሕፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እንዲማሩ ተደርገዋል።

ከዚህ ባለፈ የክልሉ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን[164]፥ ሌሎች የክልሉ ብሔሮችም በራሳቸው ቋንቋ እንዲጠቀሙና አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል። ለአብነትም፥ የክልሉ መገናኛ ብዙኃን ድርጅትም እስከ ሰባት በሚደርሱ ቋንቋዎች ስርጭት አለው[165]። በዚህ ረገድ የጎዳጣን መብት መከበር በክልሉ መዋቅር እየተሻሻለ መጥቷል የሚል ማመላከቻዎች አሉ።

## የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

በክልሉ በነበሩ የተራዘሙ ግጭትቶና የፀጥታ ችግሮች ሳቢያ፥ በክልሉ የሚገኙ እንደ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያንና ሕፃናት ያሉ ወገኖች ቀዳሚ የችግሩ ገፈት ቀማሾች ነበሩ።[166] እነዚህ የተራዘሙ ግጭቶች ባሳደሯቸው ሥነ ልቡናዊ ጫናዎች ምክንያትም በነዋሪዎች ዘንድ የጥቃትና የግጭት ሥጋቶች ጥልቅ ናቸው።[167]

የክልሉ የፀጥታ ተቋማት ውስጥ የሚሠሩ የሕግ አስከባሪዎችም ለተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ ማድረግ አልቻሉም። ይልቁንም ንፁኃንን ከሕግ አግባብ ውጪ ሲገድሉም እንደተስተዋለ አምነስቲ ኢንተርናሽናል አረጋግጧል።[168] በዚህም ሳቢያ፥ እነዚህ የኅብረተሰብ ክፍሎች ለትንኮሳና ሥጋቶች የተጋለጡ ናቸው።

## ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አማርኛ ቋንቋን እንደ ክልሉ የሥራ ቋንቋ የሚጠቀም ቢሆንም፥ የክልሉ መገናኛ ብዙኃንና የዞንና ወረዳ መዋቅሮች በተለያዩ ቋንቋዎች አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። ለአብነትም የክልሉ መገናኛ ብዙኃን ድርጅት በሰባት ቋንቋዎች የይዘት ሥርጭት ያደርጋሉ።[169]

ሆኖም አንዳንድ እንደ ማኦ ያሉ የክልሉ ቋንቋዎች እምብዛም ያልበለፀጉ በመሆናቸው የክልሉ የሥራ ቋንቋ ለመሆንና እንደ ሌሎች ቋንቋዎች የትምህርት ቋንቋ ለመሆንም አልበቁም።[170]

## የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት በክልሉ ራስን በራስ የማስተዳደርና መሰል ጥያቄዎችን ለማስተናገድ

---

164 https://www.ethiopianreporter.com/42881/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

165 https://www.dw.com/am/%E1%8B%A8%E1%89%A4%E1%8A%92%E1%88%BB%E1%8A%95%E1%8C%89%E1%88%8D-%E1%8C%89%E1%88%99%E1%8B%9D-%E1%88%9A%E1%8B%B2%E1%8B%AB-%E1%88%A5%E1%88%AB-%E1%8C%80%E1%88%98%E1%88%A8/a-62662511 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

166 https://addisstandard.com/news-ethiopian-women-children-bear-brunt-of-pandemic-conflicts-drought-induced-basic-rights-violation-rights-commission/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

167 የቡድን ውይይት 5

168 https://www.amnesty.org/en/location/africa/east-africa-the-horn-and-great-lakes/ethiopia/report-ethiopia/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

169 https://twitter.com/FdreService/status/1553677383844200449 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

170 የቡድን ውይይት 5

እንዲረዳ የብሔረሰቦች ምክር ቤት እንዲመሠረት ቢታሰብም በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ምክር ቤት ወደ ተግባር ሊገባ አልቻለም። ይህ በአንድ ወገን በክልሉ ያሉ በሕገ መንግሥቱ ዕውቅና የተሰጣቸው የክልሉ 'ባለቤቶች' በምክር ቤቱ የማይወከሉ ከሆነ አግላይ ይሆናል በሚሉ ምክንያቶች ቢሆንም ወደ ተግባር ሳይገባ የቀረው፥ በክልሉ የሚነሱ ጥያቄዎች የሚመለሱበትን አንድ ተቋማዊ አሠራር እንዳይኖር አድርጓል።[171] በክልሉ ለረዥም ጊዜያት የቆየ የጎዳጣን ጥበቃ ጥያቄ ያለ ሲሆን፥ በ2015 የክልሉ መንግሥት ይህንን ጥያቄ የሚያስተናግድበት አቅምም አልነበረውም።

> ከዚህም ጋር በተያያዘ ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(31)** ያስመዘገበው መገለጫ የ*"ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር"* ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(22)** የተመዘገበበት ባሕሪ ነጥብ ደግሞ *"የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት"* ነው። በአጠቃላይ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል *"የጎዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* ድምር ውጤት **138/225** ነው።


በዚህ የዴሞክራሲያዊነት መለኪያ ባሕሪ ክልሉ ከሌሎቹ የተሻለ ነጥብ ያገኘ ሲሆን፥ በክልሉ በተለይ የብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር መኖር በዚህ ረገድ አስተዋፅዖ አድርጓል።

## አጠቃላይ ውጤት

ተሳታፊዎቹ ከሞሉት መጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ክልሉ ከአምስቱ የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች ውስጥ ከፍተኛውን ነጥብ (138) ያገኘው በ"የጎዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ" ሲሆን፤ ዝቅተኛውን (93) ያገኘው ደግሞ በ"ቁጥጥር እና ሚዛን" ባሕሪ ነው። ከአምስቱ ባሕሪያት ውስጥ ሁለቱ ("ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያ መብቶች" እና "የጎዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ") ከግማሽ በላይ ነጥብ ያስመዘገቡ ሲሆን የተቀሩት 3ቱ ባሕሪያት ከግማሽ በታች ነጥብ ያስመዘገቡ ናቸው።

የሚከተለው ቻርት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለሁሉም መገለጫዎች ያገኘውን አጠቃላይ ውጤት ያሳያል።

**የዴሞክራሲያዊነት መገለጫዎች አጠቃላይ ውጤት (የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አስተዳደር)**




**ቻርት 2:** የቤኒሻንጉል ጉሙዝ መስተዳደር የዴሞክራሲያዊነት መገለጫዎች አጠቃላይ ውጤት


171 የቡድን ውይይት 5

ከዚህ በታች የተቀመጠው ሠንጠረዥ ደግሞ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መስተዳደርን የዴሞክራሲ ሒደት ለመለካት የተቀመጡ ባሕሪያት እና መገለጫዎች ያስመዘመገቡትን ውጤት እና ድምር በዝርዝር ያሳያል።

| የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ | የባሕሪዎቹ መገለጫዎች | | | | | ድምር | የተሰናኘ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መ1 | መ2 | መ3 | መ4 | መ5 | | |
| የመንግሥት ውጤታማነት | 23 | 20 | 21 | 16 | 21 | 101 | 2.24 |
| ቁጥጥርና ሚዛን | 23 | 16 | 17 | 13 | 24 | 93 | 2.07 |
| የዜጎች ነፃነቶች | 13 | 18 | 37 | 24 | 20 | 112 | 2.49 |
| ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያ መብቶች | 20 | 25 | 25 | 29 | 23 | 122 | 2.71 |
| የጎዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | 30 | 30 | 25 | 31 | 22 | 138 | 3.07 |
| **ድምር** | **109** | **109** | **125** | **113** | **110** | **566** | **4.03** |

**ሰንጠረዥ 5:** የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መስተዳደር ሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪያት እና መገለጫዎች ዝርዝር ውጤት

በዚህም መሠረት በሁሉም የአውራምባ ጠቋሚ የዴሞክራሲ ባሕሪዎች የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መስተዳድር ያገኘው ድምር ውጤት **566** ወደ *ተሰናኘ ድምር* ሲቀየር **4.03** ይሆናል፤ በዚህም መስተዳድሩ ቢጫ ምድብ *"ግትር"* የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ላይ ያርፋል። ይህም፥ በክልሉ የዴሞክራሲያዊነት ጉድለቶች (deficits) ጥልቀት እንዳሉ እና ለማሻሻልም ሙከራዎች እንደሌሉ ማሳያ ነው።



# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር

## የመንግሥት ውጤታማነት

### የሕግ አውጪው ውጤታማነት

የአማራ ክልል ምክር ቤት አባላት ተገዥነት ለሕግ፣ ለክልሉ ሕዝብና ለኅሊናቸው ቢሆንም፥ ከፍተኛ የሆነ የፓርቲና የኢ-መደበኛ ቡድኖች ጫና የሚንፀባረቅበት የክልሉ መንግሥት አካል የሆነ ተቋም ነው። በተለይም በክልሉ ለዓመታት ከዘለቀውና በ2015 መልኩን ቀይሮ በሚታየው ግጭት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ቡድኖች እንዲሁም የፓርቲ መስመሮች ተፅዕኖ ሥር ይወድቃል።[172]

ሕጎች ሲወጡም የክልሉ ምክር ቤት ላይ ከፍተኛ ጫናዎች የሚደርሱ ሲሆን፥ ከዚህ ባለፈም ክልሉ ሳያውቃቸውና የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ የቀየሩ ግጭቶችን ያስከተሉ ውሳኔዎች ያለ ክልል ምክር ቤት ዕውቅና ውጪ የተወሰኑ ውሳኔዎች አሉ። ከዚህ ቀዳሚው ከክልሉ ልዩ ኃይል መፍረስ ጋር የተያያዙ ውሳኔዎች ናቸው። በማዕከላዊ መንግሥት የሚወሰኑ ውሳኔዎች በክልሉ ላይ ከባድ ጫና አሳድረዋል።[173]

ስለዚህ፥ የክልሉ ምክር ቤት በሕግ በተሰጠው ኃላፊነትና ሥልጣን እንዳይሠራ የሚያደርጉት የፌዴራል መንግሥት፣ የፓርቲና የኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች ጣልቃ ገብነት ጉልህ ነው። የምክር ቤት አባላት በሥም በማኅበራዊ ትስስር ገፆች ላይ እየተጠሩና የግል ስልክ ቁጥሮቻቸው እየተለጠፉ የውሳኔ ግፊት ሲደረግባቸው የነበረ ሲሆን፥ ባለሀብቶችም ትልቅ ተፅዕኖ ያደርጉባቸዋል።[174]

172 የቡድን ውይይት 3
173 የቡድን ውይይት 3
174 የቡድን ውይይት 3

## የሥራ አስፈፃሚው ውጤታማነት

የአማራ ክልል መንግሥት ነፃ ሆኖ ለመሥራት ያልታደለና የፌዴራል መንግሥትና የገዥው ፓርቲን ማዕከላዊ ውሳኔዎች ወደ ሌሎች የክልሉ ተቋማት በማስተላለፍ የጣልቃ ገብነት መሣሪያ ሆኗል። ታጣቂዎች የሥራ አስፈፃሚው የሚወስናቸውን ውሳኔዎች ማስፈፀም እንዳይችል በርካታ የክልሉን መዋቅሮችን ተቆጣጥረው ይገኛሉ። ለአብነትም የወልቃይት ጠገዴ፣ ጠለምት እና ሁሙእራ (ምዕራብ ትግራይ) እና የራያ (ደቡብ ትግራይ) ተፈናቃዮችን ወደ ቀዬአቸው ለመመለስ ክልሉ ከትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ጋር ተስማምቶ የነበረ ቢሆንም፥ የሥራ አስፈፃሚው ባለበት ጣልቃ ገብነት ምክንያት ይህንን ለማስፈፀም ሳይችል ቀርቷል። የሥራ አስፈፃሚዎች በተለያዩ የፖለቲካ ልዩነቶች ሳቢያ ለጥቃት ሲጋለጡም ታይቷል።[175]

አስፈፃሚው አካል ያለው ተቀባይነትና ተሰሚነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሽቆለቆለ በመምጣቱና በ2015 በክልሉ የሚገኙ ግጭቶች እየተባባሱ ሲሆን፥ ክልሉ በሕግ የተሰጠወን የፖሊሲና የውሳኔ ነፃነቱን ለማስጠበቅ ይቅርና ሕዝቡንና ራሱን ለመጠበቅ በፌዴራል ኃይሎች ላይ ጥገኛ ሆኗል።[176]

## የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ውጤታማነት

የአማራ ክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በግጭቶችና በጣልቃ ገብነቶች እጅግ የተዳከሙ ስለሆኑና የመንግሥት የታችኛው መዋቅር ከሞላ ጎደል ስለፈረሰ በአገልግሎቶቻቸው ውጤታማነት ላይ ከፍተኛ ጫና አሳድሯል። ለአብነትም፥ በክልሉ በ2015 መጨረሻ በተከሰተው ግጭት ሳቢያ በአስር ዞኖች እና አንድ የከተማ አስተዳደር የገንዘብ እንቅስቃሴ ታግዶ ነበር።[177]

ከዚህ ባለፈም፥ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ቅጥር በዝምድና እና የጥቅም ትስስሮች፥ አገልግሎቶችም አላግባብ በሆኑ ክፍያዎች የሚገኙ ሲሆን፥ ይህ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውጤታማ አለመሆን ክልሉን ለብጥብጥ ከዳረጉ ጉዳዮች አንዱ ነው።[178] በአንዳንድ አካባቢዎች ሰዎች ሲታገቱና ለማስለቀቅ ክፍያ ሲጠየቅባቸው ስለነበረም አገልግሎት ሰጪ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በፍርሐትና ስጋት የተሸበቡ ናቸው።

## ያልተማከለ አስተዳደር

በሕገ መንግሥቱ መሠረት የአማራ ክልል በክልል፣ በወረዳና በቀበሌ የተዋቀረ ሲሆን፣ በክልሉ የሚገኙ የዋግ ኽምራ፣ የአዊና የኦሮሞ ብሔረሰቦች የራሳቸው የዞን ምክር ቤቶች እንደሚኖራቸውም ተደንግጓል።[179] የክልሉ ሕገ መንግሥት ክልሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሌሎች መዋቅሮችንም ይዘረጋል ስለሚል በክልሉ የዞን አደረጃጀቶችም አሉት።

ሆኖም ግን፥ የተራዘሙ ግጭቶች የአማራ ክልል እነዚህ መዋቅሮች ተናበው የሚሠሩባቸውን ዕድሎች አሳጥቷል። ከዚህ ባለፈም፥ እነዚህ የክልል መዋቅሮች ቢኖሩም፥ የክልሉ ውሳኔ ከላይ ተሰጥቶ ወደ ታች ይወርዳል እንጂ

175 https://acleddata.com/2023/08/10/fact-sheet-crisis-in-ethiopias-amhara-region/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
176 የቡድን ውይይት 3
177 https://ethiopiainsider.com/2023/11863/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
178 የቡድን ውይይት 3
179 https://knowledge-uclga.org/IMG/pdf/amhara-national-regional-state-constitution_1_.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

አሳታፊና የፖሊሲ ገለልተኝነት ያለው የታችኛው መዋቅር አልተዘረጋም። የተለያዩ የታችኛው መዋቅር ሹመቶች የሚሰጡትም በፓርቲ መስመር ነውና ከፍተኛ የሆነ ጣልቃ ገብነትም አለው።

በክልሉ በሕግ የተመሠረተ የተሻለ ያልተማከለ አስተዳደር ቢኖርም፣ የሕዝብ ተሳትፎ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ እና ጥያቄዎችን የሚመልስ መዋቅር ሳይሆን በመቅረቱ በክልሉ ለተከሰተው የፀጥታ ችግር አንዱ ግብዓት ሆኗል።[180]

> በእነዚህ ዝርዝሮች መነሻነት ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ **(22)** ያገኘው መገለጫ ***"ያልተማከለ አስተዳደር"*** ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(16)** ያስመዘገበው ደግሞ ***"የሥራ አስፈፃሚው ውጤታማነት"*** ነው። በአጠቃላይ የአማራ ክልል የመንግሥት ውጤታማነት ዴሞክራሲያዊ ባሕሪ ድምር ውጤት **93** ነው።

ይህ የክልሉ መንግሥት በዴሞክራሲ ባሕርይዎች መለኪያ ያገኘው ዝቅተኛው ውጤት ሲሆን፥ ከአማካይ ውጤት እጅግ ያነሰ ነው።



## ቁጥጥር እና ሚዛን

### የሕግ አውጪው ሥልጣን

የአማራ ክልል ምክር ቤት የክልሉ የሕግ አውጪ አካል ሲሆን፥ የሥራ አስፈፃሚወን ሥራ ለመቆጣጠርና ለመገምገም የሚያግዙ ቋሚ ኮሚቴዎችም በሥሩ ተቋቁመዋል። የአሠራር ደንብም አለው። ይሁንና፥ በፖለቲካዊ መሥመር ስለሚገዛ ጥርስ ኖሮት የክልሉን መንግሥት የሚቆጣጠርበት አቅም አልገነባም።[181] ብዙውን ጊዜ በምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ሲሰበሰቡ የማይታይ ሲሆን፥ የክልሉ ሰላም ማጣት ለቁጥጥር ሥራው ራሱን የቻለ ጫና አሳድሯል።

ሆኖም ግን፥ በምክር ቤቱ የተሻለ ሐሳብን የመግለጽ ባሕልና ልምምድ ያለ ሲሆን፥ በክልሉ ምክር ቤት ስብሰባዎች ላይ የተለየ ሐሳብ ያላቸው ከመናገር አይቆጠቡም።[182] ለአብነትም የክልሉ ምክር ቤት አባል አቶ ዮሐንስ ቧያሌው የክልል ልዩ ኃይል መፍረስን በመቃወም ያደረጉት ንግግር[183] ተቀርፆ በተያዩ መገናኛ ብዙኃን ሲሰራጭ ነበር። ከዚህ ባለፈም፥ የክልሉ ምክር ቤት ስብሰባዎች በቴሌቪዥን የሚሰራጩ ሲሆን ይህ ከበርካታ ክልሎች ለየት ያለ የግልፅኝነት ልምምድ ነው።

ይህ ቢሆንም፥ በተሰጠው ሥልጣን ልክ የቁጥጥርና ሚዛን ሥራዎችን በመሥራት ረገድ ክፍተቶች አሉበት።

180 የቡድን ውይይት 3
181 የቡድን ውይይት 3
182 አተኳሪ የቡድን ውይይት 3
183 https://www.youtube.com/watch?app=desktop&v=gMUqjzT-RV8 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)። ይህ ጽሑፍ በተሰናዳበት ጊዜ (ኅዳር 2016) አቶ ዮሐንስ ቧያለው በክልሉ ከተከሰተው የትጥቅ ግጭት ጋር በተያያዘ ከመንግሥት ጋር እየተፋለሙ ካሉ የፋኖ ታጣቂዎች ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው በመጠርጠር ከሌሎች በርካታ ፖለቲከኞች እና ጋዜጠኞች ጋር ቁጥጥር ሥር ውለው በአዋሽ አርባ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ታስረው ይገኛሉ።

## የፍርድ ቤት ነፃነት

በአማራ ክልል ፍርድ ቤቶች በነፃነት ሥራቸውን ለመሥራትና የቁጥጥርና ሚዛን ሚናቸውን ለመጫወት የሚሞክሩ ቢሆንም፥ የፖለቲካው ተፅዕኖ ከፍተኛ በመሆኑ በዳኞች ላይ ማዋከብና እስር ይፈፀምባቸዋል። እነዚህ ጥቃቶችም ዳኞች በብዛት ከሥራቸው እንዲለቁ እያደረጋቸው ሲሆን፥ በክልሉ በሥራ ላይ በሚገኙ ዳኞች ላይም ሥጋት አለ።[184]

ከዚህ በተጨማሪም፥ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች በዳኝነት ስርዓቱ ላይ ከፍተኛ ጫና የማሳደር አቅም ያላቸው ናቸው[185]።

## የፍርድ ቤቶች ገለልተኝነት

የአማራ ክልል ሕገ መንግሥት ፍርድ ቤቶች ከማንኛውም የመንግሥት አካል፥ ባለሥልጣን፣ ወይም ሌላ ጣልቃ ገብነት ወይም ተፅዕኖ ነፃ ናቸው በማለት መሥርቷቸዋል። ይህንን ድንጋጌ ይዘው የሚሠሩ ዳኞች ቢኖሩም፥ ሌሎች ደግሞ በተለያዩ ጊዜያት ለወከባና ለጥቃት ሲዳረጉ ተስተውሏል። ስለዚህም፥ በክልሉ ፍትሐዊና ገለልተኛ ፍርድ ሊሰጥ ቢችልም፥ የፖለቲካና ሌሎች ተፅዕኖዎች በስፋት ይስተዋላሉ።

ይሁንና፥ የክልሉ ሕዝብ በፍርድ ቤቶች ላይ እምነት ስላለው እስከ ይግባኝ ሰሚ የፍርድ ቤት መዋቅሮች ድረስ ጉዳያቸውን ይዘው ይሔዳሉ። ሆኖም፥ ምንም እንኳን ሕዝቡ በፍርድ ቤቶች እምነት ቢኖረውና ፍርድ ቤቶች የሕግ ጥበቃ ቢደረግላቸውም፣ የፖለቲካ ተፅዕኖው ስለሚያመዝን ገለልተኝነታቸው ላይ ጫና አለባቸው።

## ነፃ ሚዲያ

በክልሉ ብዝኃነት ያለው ሚዲያ አለ ለማለት አዳጋች ነው። ምንም እንኳን በመንግሥት ይዞታ የሚተዳደር ቢሆንም፥ የአማራ ብዙኃን መገናኛ ድርጅት የተለያዩ ሐሳቦችን የሚያስተናግድና የተለያዩ አስተሳሰቦች የሚንፀባረቁበት ነው። ይህ በተለይ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ በስፋት የሚስተዋል ሲሆን፥ በፖለቲካውም የጎላ ባይሆንም የተለያዩ አስተሳሰቦችን የመወከል ተሞክሮ አለ። ነገር ግን በክልሉ ያለው የመገናኛ ብዙኃን ድርጅት በዋናነት የፓርቲ አፈ ቀላጤና ከቋንቋ ውጪ የሐሳብ ብዝኃነት የማይታይበት ነው ብለው የሚከራከሩም አሉ።[186]

በግል የተመሠረቱና በዲጂታል ሚዲያ ዘርፍ የተሰማሩ መገናኛ ብዙኃን መረጃ ስለማይሰጣቸው በክልሉ ስላለው ነባራዊ ሁኔታ የማይዘግቡና በነፃነት መንቀሳቀስ የማይችሉ ሆነዋል። ከዚህ ባለፈም በክልሉ ሆነው የሚሠሩ መገናኛ በዙኃን ቁጥር አእንስተኛ በመሆኑ፣ ያሉትም የሐሳብ ብዝኃነት የሚታይባቸው ሳይሆኑ የታጣቂ ቡድኖች አቀንቃኝ ከመሆናቸው ባለፈ፥ የክልሉ መገናኛ ብዙኃን ቀድሞ የነበረውን ነፃነት እያጣና የውይይት ርዕስ ጉዳዮቹም እየጠበቡ እና ግጭት እና ፖለቲካ ትንተና ላይ ትኩረት እያደረጉ መጥተዋል። ክልሉን ትኩረት አድርገው የሚዘግቡ ጋዜጠኞችም ለእስርና ለስደት ሲዳረጉም በ2015 ታይቷል።[187]

184 https://am.addiszeybe.com/featured/bahir-dar/current-affairs-am/it-is-said-that-the-resignation-of-judges-in-the-amhara-region-is-another-challenge-to-the-justice-system (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

185 አተኳሪ የቡድን ውይይት 3

186 አተኳሪ የቡድን ውይይት 3

187 የቡድን ውይይት 3

## ተሟጋች ቡድኖች

በፌዴራል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ተመዝግበው በአማራ ክልል የሚንቀሳቀሱ ከ125 በላይ ድርጅቶች የሚገኙ ሲሆን፥ በርካቶቹ የልማትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ናቸው።[188] በዴሞክራሲ፣ አድቮኬሲና መብቶች ማቀንቀን ላይ የሚሠሩ ድርጅቶች በብዛት የሉም።

ሆኖም ግን፥ በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች አዳዲስ ድርጅቶች እየተመሠረቱ ሲሆን፥ አሁን እየተሻሻለ የመጣ የተሟጋች ቡድኖች ተሳትፎ አለ። ይሁንና፥ የፖለቲካ ምኅዳሩ እየጠበበ በመጣ ቁጥር የሲቪክ ምኅዳሩም እየጠበበ መጥቷል።[189] ስለዚህም፥ በአማራ ክልል የክልሉን አስተዳደር ውጤታማነት የሚፈትሹ እና የሚተቹ ብዝኃነት ያላቸው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና ተሟጋች ቡድኖች ኑባሬ ተግዳሮት ገጥሞታል።

> እነዚህ ማጣቀሻዎች ከግምት ገብተው ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ **(28)** ያገኘው መገለጫ ***"የሕግ አውጪው ሥልጣን"*** ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(18)** ያስመዘገበው ደግሞ ***"ነፃ ሚዲያ"*** ነው። በአጠቃላይ የአማራ ክልል መንግሥት የቁጥጥር እና ሚዛን ድምር ዴሞክራሲያዊ ባሕሪ ውጤት **119/225** ነው።

ይህ የሚያሳየውም በክልሉ ወሳኝ የቁጥጥርና ሚዛን ሥራ ሊሠራ የሚችለው የነፃ ሚዲያ ዘርፍ አደጋ ላይ እንዳለ የሚያሳይ ሲሆን፥ ክልሉ ጠቅላላው ቁጥጥርና ሚዛንም ደካማ ውጤት እንዲያስመዘግብ ያስቻለው ድክመትም ሆኗል።

# የዜግነት ነፃነቶች

## ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት

የአማራ ክልል ሕገ መንግሥት ከፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ሐሳብን የመግለጽ ነፃነትን ለዜጎች የሚያጎናፅፍ ድንጋጌ[190] የያዘ ሲሆን፥ ይህ መብት ግን በተለያዩ መንገዶችና መልክ ሲገደብ ይታያል።

በክልሉ በታወጁ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆችና በግጭቶች ሳቢያ በሚጣሉ የበይነ መረብ ገደቦችና መዘጋቶች ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት በተደጋጋሚ አደጋ ላይ ሲወድቅ ተስተውሏል። በሌላ ወገን ደግሞ፥ የመረጃ እጦት የዜጎችን ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት መብት የሚጎዳ ሲሆን፥ መረጃ የሚሰጠው አስፈፃሚው የሚፈልገውን ለይቶና በፈለገው ጊዜ ብቻ ነው።[191] ከዚህ በተጨማሪም በክልሉ ሐሳብን መግለጽ ነፃነት አለን ብለው የተናገሩ ወገኖች ለተለያዩ ፍረጃ የሚዳረጉ ሲሆን፥ ምኅዳሩ በፍርሐት የተሞላ እንዲሆን አድርጓል።

188 https://acso.gov.et/wp-content/uploads/2021/04/Local.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
189 የቡድን ውይይት 3
190 https://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/AMAHARA%5B1%5D.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
191 የቡድን ውይይት 3

በክልሉ ያለው የመገናኛ ብዙኃን ድርጅት (አማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን) ዘገባዎችን የሚሠራው አሁንም ድረስ ከፌዴራል መንግሥት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት እና ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በሚሰጣቸው አቅጣጫ ነው።[192]

## የመደራጀት ነፃነት

በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 31 ሥር በለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመራጀትን መብት ለማንኛውም የክልሉ ነዋሪዎች የሚያጎናፅፍ ቢሆንም፥ የአስቸኳ ጊዜ አዋጆችና የኮማንድ ፖስቶች በነበሩባቸው ጊዜያት እነዚህ መብቶች ላይ ገደቦች ይጣላሉ። ስለዚህም ይህ ነፃነት ሙሉ በሙሉ (ሳይሸራረፍ እና ሳይገደብ) ተፈፃሚ ሆኗል ለማለት ያስቸግራል።[193]

ከዚህ ባለፈም፥ በክልሉ የሚንቀሳቀሱና በፌዴራል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን የተመዘገቡ ድርጅቶች በብዛት መንግሥትን ለመቆጣጠርና ሚዛን ለማስጠበቅ በሚያስችሏቸው የአድቮኬሲ (ውትወታ) እና የዴሞክራሲ ማቀንቀን ዘርፎች የተሰማሩ ሳይሆኑ፥ በልማትና በጎ አድራጎት ዘርፎች የተሰማሩ ናቸው። ይህም በክልሉ የእነዚህ መሰል ድርጅቶች አላስፈላጊ ስለሆኑ ሳይሆን፥ መብቱ ሙሉ ለሙሉ የተረጋገጠ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ ትኩረት በማይስብ እና ለፖለቲካዊ ዕላማነት በማያጋልጡ ዘርፎች ለመሰማራት በማስብም ሊሆን ይችላል።

ስለዚህም፥ ተደራጅተው ሐሳባቸውን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማቅረብ አስቸጋሪ የሚሆንባቸው አካላት መደራጀታቸውን ለትጥቅና ለአመፃ ሲያደርጉትም ተስተውሏል።

## የሃይማኖት ነፃነት

የእምነት ነፃነቶች በሕገ መንግሥቱ ከተረጋገጡ መብቶች መካከል የሚጠቀሱ ቢሆንም፥ በክልሉ በሃይማኖቶችና በመንግሥት መካከል ያለው ቅርርብ ይህ መብት ምሉዕ ሆኖ እንዳይተገበር አድርጓል።[194]

በክልሉ ሃይማኖቶች ተቻችለውና ተከባብረው የሚኖሩ ቢሆንም፥ በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች የሃይማኖት ግጭቶች ተስተውለው ነበር። ከዚህ ባለፈም፥ በአንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች የእምነት ተቋማትን ለመገንባት ቦታና ፈቃድ ማግኘት አስቸጋሪ ነው።[195]

## የመንቀሳቀስ ነፃነት

የአማራ ክልል ሕገ መንግሥት የመዘዋወር መብትን በክፍል ሁለት ከዴሞክራሲያዊ መብቶች ሥር ደነገገ ሲሆን፥ በክልሉ መንቀሳቀስና በፈለጉት ስፍራ መኖር እንዲሁም ኑሮ መመሥረት የተፈቀደ ነው። ይሁንና፥ በክልሉ በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ቡድኖች፥ በተደጋጋሚ በሚፈፀሙ እገታዎችና ግጭቶች ሳቢያ ይህ ነፃነት በእጅጉ ተወስኖ ቆይቷል።

192 የቡድን ውይይት 3
193 የቡድን ውይይት 3
194 የቡድን ውይይት 3
195 የቡድን ውይይት 3

ከዚህ በተጨማሪም፥ በክልሉ በተከሰቱ ግጭቶስ በርካቶች የኑሮ ሁኔታቸው የተዛባና የተፈናቀሉ ሲሆን፥ በክልሉ ሲጣሉ የነበሩ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆችም መንቀሳቀስን በሰዓትና በቦታ እንዲሁም በትራንስፖርት መንገድ ገደብ ሲቀመጥ ነበር።[196]

ከዚህ ባለፈም፥ ክልሉን አቋርጦ ወደ አዲስ አበባ የሚመጡ ተሽከረካሪዎችና ዜጎች ወደ አዲስ አበባ እንዳይጓዙ ገደብ ተጥሎባቸው የነበረ ሲሆን፥ ከአንድ ክልል ወደ አማራ ክልል የሚደረጉ ጉዞዎችም ገደብ ይጣልባቸዋል።[197]

## የግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ

የአማራ ክልል ሕገ መንግሥት በአንቀፅ 26 ስር የግል ሕይወት መጠበቅና መከበር መብትን የሚያጎናፅፍ ሲሆን፥ የማንኛውም ግለሰብ ምሥጢሮች እንደማይደፈሩ ይደነግጋል። ይሁንና በክልሉ ከሕግ ውጪ የሚፈፀሙ ግድያዎች እጅግ አሳሳቢ መሆናቸውን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ያስታወቀ ሲሆን[198]፥ ግለሰቦች በተለያዩ ጊዜያት ሲታፈኑና ለማስለቀቅም ብዙ ገንዘብ ሲጠየቁ ነበር።

በተጨማሪም በክልሉ የተራዘመ ግጭት በመኖሩ የዜጎች ደኅንነት አደጋ ላይ ወድቆ የነበረ ሲሆን፥ በጥቃቶች አደጋ የደረሰባቸው ንፁሐን ዜጎች መኖራቸውም ተዘግቧል።[199] ከዚህ ባለፈም፥ በክልሉ የተጣሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆች የዜጎችን ምሥጢር ጥበቃ መብቶች ይገፍፋሉ።

አንዱ በዚህ ረገድ አሳሳቢ የነበረው ልምምድ የግለሰቦች የስልክና የኢሜል እንዲሁም የጽሑፍ መልዕክት ልውውጦች በተለያዩ መንገዶች ወጥተው በየማኅበራዊ ትስስር ገፆች ሲዘዋወሩ ታይተዋል። ይህ በተለይም "ሾልኮ የወጣ የስልክ ንግግር"[200] በሙል በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን በተለይ በማኅበራዊ ሚዲያዎች ሲዘዋወር የቆየ ሲሆን፥ የግለሰብና የቡድን ስብሰባዎችም ያለ ግለሰቦቹና ሰዎቹ ፈቃዶች ወደ አደባባይ ሲወጡ ታይተዋል።

> እነዚህን ጉዳዮች ከግምት በማስገባት በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(31)** ያገኘው የዜግነት ነጻነቶች መገለጫ *"የሃይማኖት ነፃነት"* ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(17)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"የግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ"* ነው። በአጠቃላይ የአማራ ክልል መንግሥት *"የዜግነት ነፃነቶች"* ድምር ውጤት **108/225** ነው።

196 https://amharic.addisstandard.com/%E1%8B%9C%E1%8A%93-%E1%89%A0%E1%8A%A0%E1%88%9B%E1%88%AB-%E1%8A%AD%E1%88%8D%E1%88%8D-%E1%8B%A8%E1%88%B0%E1%8B%93%E1%89%B5-%E1%8A%A5%E1%88%8B%E1%8D%8A-%E1%8C%88%E1%8B%B0%E1%89%A5-%E1%88%99%E1%88%89/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

197 https://www.bbc.com/amharic/articles/c3g49we102qo (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)፥ የቡድን ውይይት 3

198 https://ehrc.org/%E1%89%A0%E1%8A%A0%E1%88%9B%E1%88%AB-%E1%8A%AD%E1%88%8D%E1%88%8D-%E1%8A%A8%E1%88%85%E1%8C%8D%E1%8A%93-%E1%8D%8D%E1%88%AD%E1%8B%B5-%E1%8B%8D%E1%8C%AA-%E1%8B%A8%E1%88%9A%E1%8D%88%E1%8D%80/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

199 https://www.bbc.com/amharic/articles/c72r987lj25o (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

200 https://www.youtube.com/watch?v=1DIHl4kWt1o (ጥቅምት 2016)

## ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች

### መሠረታዊ ፍላጎቶች

የአማራ ክልል በመሠረታዊ ፍላጎቶች ረገድ እጅግ አናሳ ደረጃ ያለው ሲሆን፥ የውኃና የጤና አገልግሎት አቅርቦች እጅግ አናሳ ነው። የንፁሕ የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ባለመዳረሱ ኅብረተሰቡ ውኃ ከወራጅ ወንዝ የሚቀዳ ከመሆኑ ባሻገር፥ በቂ የጤና ማዕከላት ባለመኖራቸውና የአምቡላንስ አቅርቦትም ውሱን ስለሆነ ታማሚዎችና የሚያምጡ ሴቶች በቃሬዛ ወደ ጤና አገልግሎት ያለበት ሥፍራ መሔዳቸው የተለመደ ነው።[201]

በተጨማሪም በክልሉ በነበሩ ግጭቶች (ከህወሓት ኃይሎች ጋር የተደረገውን ውጊያ ጨምሮ) የወደሙ የመሠረታዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት መልሶ ግንባታ ስላልተከናወነ የመሠረታዊ ፍላጎቶች አቅርቦት ይበልጡኑ ተጎድቷል። ክልሉ የምግብ ሰብሎችን በስፋት የሚያመርት ክልል ቢሆንም የምግብ ዋስትናውን ያላረጋገጠ እና አንዳንዴም ለድርቅና ርሃብ ሲጋለጥ ይስተዋላል። በዚህም ሳቢያ፥ በክልሉ ከሚገኙ ሕፃናት 40 በመቶዎቹ የቀነጨሩ ናቸው።[202]

### የትምህርት መብት

በአማራ ክልል የትምህርት መሠረተ ልማት ያልዳበረ በመሆኑ ሳቢያ ሕፃናት የትምህርት ገበታቸው ላይ የሚገኙት ሰዓታትን በእግራቸው ተጉዘው ነው ። በማኅበረሰቡ ዘንድ ባለ አመለካከት ሳቢያም፥ በተለይ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ትምህርት የማግኘት መብታቸው በእጅጉ የተጨቆነ ሲሆን፥ የትምህርት ቤቶች የትምህርት ግብዓቶች አለመሟላታቸውም ይህ መብት ምሉዕ እንዳይሆን ያደርጋል።[203]

በአማራ ክልል በግጭቶች ሳቢያ ከ4000 በላይ ትምህርት ቤቶች[204] በከፊልና ሙሉ ለሙሉ የወደሙ ሲሆን፥ በ2015 ወደ ክልሉ በግጭት ምክንያት ትምህርት ያቋረጡ 347 ትምህርት ቤቶችን ብቻ ወደ ሥራ አስገብቷል።[205]

ተማሪዎችም ለጥቃትና ለእገታ ስለሚዳረጉም፥ ወላጆች ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት ያለመላክ አዝማሚያም አሳይተዋል። አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ለምዝገባ ብለው የሚጠይቁት ክፍያም ከወላጆች አቅም በላይ በመሆኑ ልጆቻቸውን ከትምህርት ገበታ ያስቀራሉ።[206]

### የስርዓተ ፆታ እኩልነት

የአማራ ክልል ሕገ መንግሥት የሴቶችን መብቶች በግልጽ ድንጋጌ ዕውቅና ሰጥቶ ያስቀመጠ ሲሆን፥ ሴቶች ከወንዶች እኩል የፖሊቲካ፣ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ተሳትፎና አስተዋፅዖ እንዲኖራቸው አድርጓል። በዚህም ሳቢያ ሴቶች

201 የቡድን ውይይት 3
202 https://ephi.gov.et/wp-content/uploads/2023/03/FNS_baseline_survey_preliminary_findings.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
203 የቡድን ውይይት 3
204 https://www.ethiopianreporter.com/77487/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
205 https://www.fanabc.com/archives/180601 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
206 የቡድን ውይይት 3

በተለያዩ የክልሉ መንግሥታዊ መዋቅሮች ተሳትፎ እያደረጉ ሲሆን፥ በተለይ በክልሉ ምክር ቤት ሰፊ ውክልና አላቸው። ሆኖም ግን ይህ ውክልና ትርጉም ያለው መሆን ይኖርበታል።[207]

ሴቶች በክልሉ ባሉ ግጭቶች አሁንም የበለጠ ተጎጂ ሲሆኑ፥ ለፆታዊና ወሲባዊ ጥቃቶች ተጋላጭም ናቸው።[208]

## የግል ንብረት ጥበቃ

በክልሉ የንብረት ጥበቃ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 40 የተረጋገጠና ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተመሳሳይ መብትን የሚያጎናፅፍ ነው። ሆኖም በክልሉ በሚነሱ አመፆችና ግጭቶች ሳቢያ ለግል ንብረቶች ጥበቃ ማድረግ አስቸጋሪ ሆኖ በርካታ ውድመት ሲደርስ ታይቷል። ይህ ሲሆንም በክልሉ ተጠያቂነትን የማስፈን ውሱንነቶች አሉ። ንብረት ሲወድም የወቅቱን የፖለቲካ ትኩሳት እያዩ መታገስም ተለምዷል።[209]

## የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ

በክልሉ መሬት ትልቁ ሀብት ሲሆን፥ ሴቶች ከወንዶች እኩል ንብረት የማፍራትና ባለቤት የመሆን መብቶቻቸው የተረጋገጡ ቢሆንም፥ አሁንም ድረስ ከወንዶች ጋር የመመጣጠን ውሱንነቶች አሉ።[210]

ከዚህ በተጨማሪም በከተማና በገጠር ነዋሪዎች መካከል ከፍተኛ የሆነ የሀብት አለመመጣጠን አለ።

> በነዚህ መንደርደሪያዎች በመነሳት ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(28)** ያገኘው መገለጫ *"የግል ንብረት ጥበቃ"* ሲሆን፥ ዝቅተኛው ነጥብ **(17)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"መሠረታዊ ፍላጎቶች"* ነው። በአጠቃላይ የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት *"ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች"* ድምር ውጤት **110/225** ነው።



# የጎዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

## የጎዳጣን ብሔረሰቦች ጥበቃ

በአማራ ክልል የሚኖሩ የጎዳጣን ብሔረሰቦች በሕገ መንግሥቱ ዕውቅና ተሰጥቷቸው የራሳቸውን አስተዳደራዊ መዋቅሮች የዘረጉ ሲሆን፥ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎች በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠላቸው ናቸው። በተጨማሪም፣ ሕገ መንግሥቱ ከፀደቀ በኋላ የመጡ የጎዳጣን ብሔረሰቦችች ጥያቄዎች (ለምሳሌ ቅማንት) ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል።

207 የቡድን ውይይት 3
208 የቡድን ውይይት 3
209 የቡድን ውይይት 3
210 የቡድን ውይይት 3

ይሁንና ጥያቄው ተመልሶ ያላለቀ በመሆኑ አሁንም ድረስ የግጭት መንስዔ ሲሆን ይስተዋላል። በክልሉ የማንነት አስመላሽ ኮሚቴዎችም ይገኛሉ። በጣና ሐይቅ አካባቢ የሚኖሩ የወይቶ ብሔረሰቦችም ተመሳሳይ ጥያቄ አላቸው። ሆኖም፥ በአማራ ክልል ለሌሎች ምላሽ ያልተሰጣቸው ተመሳሳይ ጥያቄዎች አሉ።[211]

## የኀዳጣን መብቶች

በአማራ ክልል የሚኖሩ ኀዳጣን ራሳቸውን በራሳቸው በሚያስተዳድሩባቸው አካባቢዎች በራሳቸው ቋንቋ የሚጠቀሙ ሲሆን፥ ባሕሎቻቸውንና የእምነቶቻቸውን እሴቶች በአደባባይ ይከውናሉ። ሆኖም፥ በተለይ ከሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ወዲህ በክልሉ በትግራይ ተወላጆች ላይ ጫና አለባቸው።

ከዚህ ባለፈም የእምነት ኀዳጣን ባሉባቸው አካባቢዎች የእምነት ተቋማትን የመገንባትና መሰል ገደቦች ያሉባቸው የክልሉ አካባቢዎችም ይገኛሉ።[212]

## የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

በአማራ ክልል የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ በተለይ በፆታና በአካል ጉዳተኝነት ረገድ ውሱንነቶች ያሉ ሲሆን፥ በአማራ ክልል የተከሰቱ ግጭቶች የተጋላጭ ቡድኖችን ሁኔታ እንዲባባስ ማድረጉን የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን አስታውቆ ነበር።[213]

በክልሉ የሚገኙ ዲግሪ ያላቸው የአካል ጉዳተኞች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ የክልሉ መንግሥት በወሰነው መሠረት ሥራ እያገኙ ቢሆንም፥ የአዕምሮ ሕመምተኞች እንዲህ ያሉ መብቶች ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም።[214]

## የብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር

የአማራ ክልል የሥራ ቋንቋ አማርኛ ቢሆንም ራሳቸውን በራሳቸው በሚያስተዳድሩ እንደ ኦሮሞ ብሔረሰብ ዞን ያሉ አካባቢዎች ከክልሉ የሥራ ቋንቋ በተጨማሪ የአካባቢው የሥራ ቋንቋ (አፋን ኦሮሞ) ጥቅም ላይ ይውላል። ሆኖም ግን፥ በክልሉ የሚኖሩም ሆኑ ሌሎች ብሔሮች ከአማርኛ ቋንቋ ውጪ ክልላዊ አገልግሎቶችን ማግኘት ሲፈልጉ የሚስተናገዱት በአማርኛ ብቻ ነው።

ይሁንና፥ በአማራ ክልል በሌሎች ክልሎች አንጻለው የመንግሥትና የንግድ ተቋማት ሥሞችን በተጨማሪ የአገሪቱ ቋንቋዎች የመጻፍ ውሱንነቶች አሉ።[215]

## የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት

የአማራ ክልል በሕግ ደረጃ መብቶችን የሚያከብር ቢሆንም፥ በተግባር ግን አሁንም ውሱንነቶች አሉበት። ለአብነትም እንደ ቅማንት ያሉ ጥያቄዎችን ምሉዕ በሆነ መልኩ ለመመለስ ባለመቻሉና የኅብረተሰቡን ቅሬታ ማዳመጥ ባለመቻሉ በተደጋጋሚ ግጭቶች እንዲከሰቱ ሆኗል።

211 የቡድን ውይይት 3

212 የቡድን ውይይት 3

213 https://ehrc.org/the-human-rights-impact-of-the-armed-conflict-on-civilians-in-amhara-regional-state/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

214 የቡድን ውይይት 3

215 የቡድን ውይይት 3

የክልሉ መንግሥት ሕዝብን የሚያዋየው ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ በመሆኑ ክልሉ መረጃ ለማቀበል እንጂ የሕዝቡን ጥያቄ ሰምቶ ለመፍታት እምብዛም አያሳትፍም። ለዚህ አንዱ ማሳያ በክልሉ ልዩ ኃይል መፍረስ የክልሉ ሕዝብ ሳይወያይ የተፈፀመ በመሆኑ፥ ሕዝቡ ሰልፍ ወጥቶ ሲቃወም የክልሉ መንግሥት ምላሹ ማብራራት እንጂ ሕዝባዊ ይሁንታ ያለው ምላሽ መስጠት አልነበረም።

በተጨማሪም፥ ክልሉ የሕዝብን ጥያቄዎች የሚቀበልበትና የሚያስተናግድበት ተቋማዊ አደረጃጀቶች የሉትም።

> እነዚህን ጉዳዮች ከግንዛቤ በማስገባት ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት፣ ከፍተኛውን ነጥብ (36) ያገኙት መገለጫዎች *"የኅዳጣን መብቶች"* እና *"ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር"* ሲሆኑ ዝቅተኛው ነጥብ (29) የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት"* ነው። በአጠቃላይ የአማራ ክልል *"የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* ድምር ውጤት 166/225 ነው።


ይህ ክልሉ በመለኪያው ከተቀመጡ የዴሞክራሲ ባሕሪዎች ከፍተኛውን ነጥብ ያገኘበት ሲሆን፥ በክልሉ መጠናከር ያለበት የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ ልምምድ መኖሩን ይጠቁማል። ይሁን እንጂ ይህም በመለኪያው *"ግትር"* ወይም ባለበት የሚረግጥ የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ደረጃ ውስጥ የሚወድቅ ነው።

## አጠቃላይ ውጤት

> ከአምስቱ የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች ውስጥ የአማራ ክልል ከፍተኛውን ነጥብ (166) ያገኘው *"የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ ሲሆን፤ ዝቅተኛውን (93) ያገኘው መገለጫ ደግሞ *"የመንግሥት ውጤታማነት"* ነው። ከአምስቱ ባሕሪያት ውስጥ ሁለቱ ብቻ (*"ቁጥጥር እና ሚዛን"* እና *"የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"*) ከግማሽ በላይ ነጥብ ያስመዘገቡ ሲሆን የተቀሩት ሦስቱ ባሕሪያት ከግማሽ በታች ነጥብ አስመዝግበዋል።

የሚከተለው ቻርት የአማራ ክልል ለሁሉም መገለጫዎች ያገኘውን አጠቃላይ ውጤት ያሳያል።

**የዴሞክራሲያዊነት መገለጫዎች አጠቃላይ ውጤት (የአማራ ክልል አስተዳደር)**




ቻርት 3: የአማራ ክልል መስተዳድር የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪያት አጠቃላይ ውጤት

ከዚህ በታች የተቀመጠው ሰንጠረዥ ደግሞ የአማራ ክልል መስተዳደርን የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ለመለካት የተቀመጡ ባሕሪዎች እና መገለጫዎች ያስመዘመገቡትን ውጤት እና *የተሰናኘ ድምር* በዝርዝር ያሳያል።

| የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ | የባሕሪዎቹ መገለጫዎች | | | | | ድምር | የተሰናኘ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መ1 | መ2 | መ3 | መ4 | መ5 | | |
| የመንግሥት ውጤታማነት | 18 | 16 | 18 | 19 | 22 | 93 | 2.07 |
| ቁጥጥርና ሚዛን | 18 | 27 | 28 | 22 | 24 | 119 | 2.64 |
| የዜጎች ነፃነቶች | 18 | 20 | 31 | 22 | 17 | 108 | 2.4 |
| ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያ መብቶች | 17 | 18 | 26 | 28 | 21 | 110 | 2.44 |
| የጎዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | 35 | 36 | 30 | 36 | 29 | 166 | 3.69 |
| **ድምር** | **106** | **117** | **133** | **127** | **113** | **596** | **430** |

**ሰንጠረዥ 6:** የአማራ ክልል መስተዳደር ሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪያት እና መገለጫዎች ዝርዝር ውጤት

በዚሁ መሠረት በሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪዎች የአማራ ክልላዊ ብሔራዊ መስተዳድር ያገኘው ድምር ውጤት **596** ወደ *ተሰናኘ ድምር* ሲቀየር **4.30** ይሆናል፤ በዚህም መስተዳድሩ ቢጫ ምድብ ወይም *"ግትር"* የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ላይ ያርፋል።



# የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር

## የመንግሥት ውጤታማነት

### የሕግ አውጪው ውጤታማነት

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሕግ አውጪ አካል በጀት መድቦና የራሱን አደረጃጀቶችና ኮሚቴዎች አዋቅሮ የሚንቀሳቀስ ቢሆንም፥ የከተማ አስተዳደሩ ለሚፈፅማቸው ክንውኖች ሕጋዊ ሽፋን መስጫ ሆኖ ያገለግላል እንጂ ያለ ጣልቃ ገብነት የራሱን ሥራ የሚከውንም መስተዳድር አይደለም።[216]

በሌላ መልኩ፥ በፓርቲ መሥመር አስፈፃሚው በተግባር የምክር ቤቱ አባላትና አመራሮች የበላይ ስለሚሆኑ ከፍተኛ የፓርቲ ጣልቃ ገብነት ይኖርበታል። የምክር ቤት አባላት በፓርቲ የሚገመገሙ ሲሆን፥ ግምገማውም በምክር ቤት በሚሠሩት ሥራ ሳይሆን በፓርቲው መስፈርቶች ነው። ለምሳሌ፥ ምክር ቤቱ ሳይነገረውና ሳይጠይቅ ዶ/ር ካሣ ተሻገር የተባሉ አባሉ በአማራ ክልል ከተቀሰቀሰው ግጭት ጋር በተያያዘ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በተቋቋመው ኮማንድ ፖስት ታስሮበታል።[217]

### የሥራ አስፈፃሚው ውጤታማነት

በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ካሉ የባለቤትነት እና ሌሎች የተቃረኑ ፍላጎቶችና የፖለቲካ ፉክክሮች ምክንያት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ አስፈፃሚ አካል በተለያዩ አካላት ጫና ይደርስበታል። እነዚህ ጫና አድራሾች መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ድርጅቶች ሊሆኑ ይችላሉ። አዲስ አበባ የአገሪቱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማዕከል ከመሆኗ ጋር ተያይዞ የብሔር ውክልና እና ሌሎች ፍላጎቶችን ማስተናገድ ስለሚኖርባት በመንግሥት ሠራተኞች ስብጥርም ሆነ በሌሎች ጥያቄዎች ሰበብ ጣልቃ ገብነቶች ይኖራሉ።[218]

216 የቡድን ውይይት ፣

217 https://www.dw.com/am/%E1%8B%A8%E1%8D%8C%E1%8B%B0%E1%88%AB%E1%88%8D-%E1%8A%A5%E1%8A%93-%E1%8A%AD%E1%88%8D%E1%88%8D-%E1%88%9D%E1%8A%AD%E1%88%AD-%E1%89%A4%E1%89%B5-%E1%8A%A0%E1%89%A3%E1%88%8B%E1%89%B5%E1%8A%95-%E1%8C%A8%E1%88%9D%E1%88%AE-53-%E1%8C%8D%E1%88%88%E1%88%B0%E1%89%A6%E1%89%BD-%E1%8A%A0%E1%8B%8B%E1%88%BD-%E1%8A%A0%E1%88%AD%E1%89%A3-%E1%88%98%E1%89%B3%E1%88%B0%E1%88%AB%E1%89%B8%E1%8B%8D%E1%8A%95-%E1%8A%A2%E1%88%B0%E1%88%98%E1%8A%AE-%E1%8A%A0%E1%88%A8%E1%8C%8B%E1%8C%88%E1%8C%A0/a-66717637 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

218 የቡድን ውይይት ፣

ሌላው በተከማ አስተዳደሩ ላይ የሚደርስበት ተፅዕኖ ከገዥው ፓርቲ የሚመጣ ነው። የከተማ አስተዳደሩ ተፅዕኖ ከሚያደርስበት የፓርቲ መዋቅር ጋር ተሥማምቶና ፈቅዶ የሚሠራ በመሆኑ የፓርቲ እና መንግሥት መቀላቀል ይታያል። አልፎ ተርፎም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በመሆኑና ከተማይቱ የፌዴራል መንግሥት መቀመጫ ከተማ በመሆኗም የፌዴራል መንግሥት ጣልቃ ገብነትም ቀላል አይደለም።[219]

## የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ውጤታማነት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከሌሎቹ ክልሎች የተሻለ የሰው ኃይል ያላቸው ቢሆኑም፥ የመንግሥት አገልግሎት ግን አሁንም አርኪ ሊሆን አልቻለም። ከተማ አስተዳደሩ ብቃት ያላቸው ሠራተኞች ቢኖሩትም ሁሉም የተቀጠሩት ግን በሙያቸውና በብቃታቸው ብቻ ነው ለማለት አይቻልም። ከፍተኛ ጣልቃ ገብነት ስላለባቸው ከአገልግሎቱ ጥራትና ቀልጣፋነት ይልቅ ለፖለቲካው ያደላሉ።[220]

የከተማ አስተዳደሩ ሠራተኞች የሚገመገሙባቸውና ብቃታቸው የሚለኩባቸው መሥፈርቶች ቢኖሩም፥ እነዚህ መሥፈርቶች ጥቅም ላይ የሚውሉት የሥራውን ውጤታማነት ለማሻሻል ሳይሆን ለፖለቲካዊ ውግንነት ሲሆኑ ይታያል። ስለዚህ የገዥው ፓርቲ ፍላጎቶች የሚመራቸው ተቋማት ናቸው። በርካታ የመንግሥት ሠራተኞችም የፓርቲ አባላት ስለሚሆኑ መዋቅራዊ የሆኑ ችግሮች እንዲኖሩ አድርጓል። በተጨማሪም፥ የከተማ አስተዳደሩ ብዛት ያላቸው ተቋማቱ ከፍተኛ ሙስና ተንሰራፍቶበት የሚታይበት ነው።[221]

## የፀረ ሙስና ውጤታማነት

የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በተደጋጋሚ በከተማ አስተዳደሩ እንደተገለጸው ሰፊ ሙስናና ዘረፋ የሚስተዋልበት ሲሆን፥ በተለይ የመሬት፣ የቤቶች፣ እንደ መታወቂያ ያሉ አገልግሎቶች፣ የገቢዎችና ሌሎች አስተዳደሮች ሰፊ የሙስና ችግሮች ያለባቸው ናቸው። እነዚህን መከላከል የሚያስችሉ የሕግና የተቋም አደረጃጀቶች ቢኖሩም፥ አስፈጻሚ ተቋማቱ ደካማ ናቸው።[222]

ለዚህም አንዱ ማሳያ የከተማ አስተዳደሩ በ2015 የመሬት አገልግሎትን በተደጋጋሚ ሲያግድ የነበረ ሲሆን፥[223] የንብረት ባለቤትነት ሥም ዝውውር ምዝገባም እንዲሁ በተመሣሣይ ታግዶ ነበር።[224]

በከተማ አስተዳደሩ አንዳንድ ዜጎች የዜግነት አገልግሎቶችን ለማግኘት ጉቦ የሚከፍሉ ሲሆን፥ የመታወቂያና የወሳኝ ኩነቶች ምዝገባዎች ለዚህ ችግር የተጋለጡ ናቸው።[225]

219 የቡድን ውይይት 1
220 የቡድን ውይየዕት 1
221 የቡድን ውይይት 1
222 የቡድን ውይይት 1
223 https://m.facebook.com/RealEstate40.60HousingProjectsAddisAbaba20.80/photos/a.634161463362435/5554336161344916/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
224 https://www.facebook.com/dw.amharic/photos/a.507141705985597/6197944403571937/?type=3 (ጥቀምት 2016 የተጎበኘ))
225 የቡድን ውይይት 1

## ያልተማከለ አስተዳደር

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተማና ቀበሌ የሚሉ አደረጃጀቶች በቻርተሩ ሲኖረው፥ በተግባር በተዘረጋው መዋቅር ግን ክፍለ ከተማና ወረዳ በሚል የተደራጀ ነው።[226] ክፍለ ከተሞች የማዘጋጃ ቤት ሥልጣን ሲኖራቸው፥ ቀበሌዎች ደግሞ የልማትና የሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማዕከል እንደሆኑ በቻርተሩ ተመላክቷል። ክፍለ ከተሞች ምክር ቤቶች አሏቸው።

ይሁንና የከተማ መስተዳድሩ መዋቅሮች የሚመሩት የውሳኔ ማዕከላዊነት ባለው የገዢው ፓርቲ አሠራር የሚመሩ በመሆናቸው ጣልቃ ገብነት በስፋት ይስተዋልባቸዋል።

> በእነዚህ መነሻዎች መሠረት ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ ከፍተኛ ነጥብ **(24)** ያገኘው የመንግሥት ውጤታማነት መገለጫ ነጥብ ***"ያልተማከለ አስተዳደር"*** ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(13)** ያስመዘገበው ደግሞ ***"የፀረ - ሙስና ውጤታማነት"*** ነው። በአጠቃላይ የአዲስ አበባ መስተዳደር የመንግሥት ውጤታማነት ድምር ውጤት **106/225** ነው።



## ቁጥጥር እና ሚዛን

### የሕግ አውጪው ሥልጣን

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስብሰባዎች የሚደረጉት የሥራ አስፈፃሚው በሚፈልግበት ጊዜ ነው እንጂ ቋሚ የስብሰባ ጊዜ የለውም። ይህም ምክር ቤቱ በቋሚነት የአስፈፃሚውን ሥራ የሚገመግምበትን ዕድል የሚያሳጣው ሲሆን፥ የከተማ አስተዳደሩ አስፈፃሚ የበላይ ከንቲባ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በመሆኑ የምክር ቤቱ ቁጥጥርና ሚዛን ሥልጣን ይቀንሳል ወይንም ሽሚያ አለበት።

ሆኖም፥ የከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችን መሥርቶ የከተማ አስተዳደሩን የተለያዩ ተቋማት እና ስራዎቻቸውን የሚነበኝና የማሻሻያ ምክረ ሐሳቦችን የሚሰጥ ሲሆን፥ እነዚህ ምክረ ሐሳቦች ግን ቢፈፀሙም ባይፈፀሙም እርምጃ መውሰድ የሚያስችለው ቁመና የለውም። ምክር ቤቱ የከተማ መስተዳድሩ የሚሠራቸውን አንዳንድ ሥራዎች በምን ሥልጣን እንደሚሠራ እንኳን የመጠየቅ ሥልጣን ወይም ልምድ የለውም። ለዚህም ማሳያ የሚሆኑት በ2015 የቀጠሉ በአስፈጻሚው ወይም በከንቲባዋ ተነሳሽነት የሚደረጉ በጎ ፈቃድ መሳይ እንቅስቃሴዎች (ቤት፣ የተለያዩ ሽልማቶች፣ ለክልሎች ወይም ለአንዳንድ ኢኒሼቲቮች የሚደረጉ የገንዘብ ድጋፎች) የገንዘብ ምንጫቸው፣ የአሠራረ አግባቢነታቸው እና ሕጋዊነታቸው የሚጠየቅበት መድረክም ባሕልም አልነበረም። ይህ አካሄድ በፌደርል መንግሥት እንዲሁም በሌሎች የፌዴሬሽኑ ክልሎችም ተስፋፍቶ ይገኛል።

---

226 https://www.fsc.gov.et/DesktopModules/EasyDNNNews/DocumentDownload.ashx?portalid=0&moduleid=1179&articleid=694&documentid=615 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

## የፍርድ ቤት ነፃነት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር የከተማ አስተዳደር የፍርድ ቤቶችን በከተማ አስተዳደርና በቀበሌ ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች ካዋቀረ በኋላ፥ የዳኞችን ሹመት በሚመለከት ለከተማ አስተዳደሩ በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይቀርባሉ ይላል። ይህ ከሌሎች መስተዳድሮች የተለየ አሠራር ነው። በሌሎች ክልሉች ዳኞች የሚሾሙት በአስፈፃሚው አካል አቅራቢነት፣ በምክር ቤቱ ነው ።

በከተማ አስተዳደሩ የሚሠሩ ዳኞች የውሳኔ አሰጣጥን በተመለከተ ነፃነት ያላቸው ሲሆን፥ በተቋማዊ አደረጃጀት በበጀትና በሌሎች ጉዳዮች በከተማ አስተዳደሩ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ምንም እንኳን ፍርድ ቤቶች በውሳኔ ረገድ ነፃነት አላቸው ቢባልም፥ የሚወስኗቸውን ውሳኔዎች ባለመፈፀም በዳኞች ላይ ጫና ይደረግባቸዋል።[227] ይህ በተለይ የከተማ አስተዳደር የዳኝነት አካል ሥልጣን በሆነው የፋይናንስ ጉዳዮች እና በከተማ ፕላን በሚኖሩ ክርክሮች ጎልቶ ይታያል። ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የእግድ ውሳኔም በከተማ አስተዳደሩ ነቀፋ ሲደርስባቸው ታይቷል።

## የፍርድ ቤቶች ገለልተኝነት

የከተማ አስተዳደሩ ቻርተር የዳኝነት አካል ገለልተኝነትን በተመለከተ በግልጽ የተቀመጠ ድንጋጌ የሌለ ቢሆንም፥ የዳኞችን አሿሿምና አነሳስን በተመለከተ ያስቀመጠው ድንጋጌ ለዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ትልቅ ስልጣን የሚሰጥና ዳኞች የሚሾሙበትንና የሚነሱበትን ግልጽ ምክንያት ያስቀመጠ ነው።[228]

ምንም እንኳን የከተማ አስተዳደር የዳኝነት አካላት በግል ጉዳዮች ላይ በገለልተኝነት ለመሥራት ቢሞክሩም፥ በፖለቲካ፣ በባለሀብትና በሌላ የፍላጎት ቡድኖች ጫና ይደረግባቸዋል።[229]

## ነፃ ሚዲያ

በከተማ አስተዳደሩ የሚዲያ ብዝኃነት በቁጥርም በይዘትም በርካታ ሲሆን፥ ከተማ አስተዳደሩ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሠሩ የመገናኛ ብዙኃን ግን ጥቂት ናቸው። የከተማ አስተዳደሩ የሚያስተዳድረው የአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ የከተማ አስተዳደሩን ሥራዎች የሚሸፍን ቢሆንም፥ አስተዳደሩ የፖለቲካ ጫና ስላለበት፥ እንዲሁም ብቁ የሰው ኃይል እጥረት ስላለበት የቁጥጥርና ሚዛን ሥራውን በምሉዕነት ሊወጣ አልቻለም።

ይህ የሆነበት አንደኛው ምክንያት ለእነዚህ ተቋማት ነፃነት የሚፈቅድ አሠራር ባለመዘርጋቱ ሲሆን፥ የከተማ አስተዳደሩና የፌዴራል መሥሪያ ቤቶች የኮሚዩኒኬሽን ክፍሎች አቅጣጫ እየሰጧቸውም ይዘት የሚሠሩ ናቸው።[230] በከተማዋ ያሉ ሌሎች የመንግሥት መገናኛ ብዙኃንም እንዲሁ በነፃነት ሠርተው የቁጥጥርና ሚዛን ሥራቸውን ለመከወን የሚችሉ አይደሉም።

227 የቡድን ውይይት ።
228 https://www.fsc.gov.et/DesktopModules/EasyDNNNews/DocumentDownload.ashx?portalid=0&moduleid=1179&articleid=694&documentid=615 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
229 የቡድን ውይይት ።
230 የቡድን ውይይት ።

ስለዚህም፥ ሁሉም የመገናኛ ብዙኃን ተመሳሳይ ይዘቶችን በሁሉም መንገዶች ሲያሰራጩ የሚታዩ ሲሆን፥ አንዱ ለየት ብሎ የራሱን ይዘት የሚሠራበት ዕድል የለውም።

### ተሟጋች ቡድኖች

በርካታ ተሟጋች ቡድኖች አዲስ አበባ ከተማን ማዕከል አድርገው የሚንቀሳቀሱ ቢሆንም እነዚህ ተቋማት በብዛት ትኩረታቸው የከተማ አስተዳደሩ ሳይሆን የፌዴራሉ መንግሥት ሥራዎችና እንቅስቃሴዎች ላይ ነው። ይሁንና፣ አንዳንድ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በከተማይቱ የሚከናወኑ ሥራዎችን ጭምር እየተከታተሉ ትችትና ምክረ ሐሳብ የሚያቀርቡ አሉ።[231]

ይሁንና፥ በከተማው አንዳንድ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ላይ የሚደርሱ ጫናዎች ቢኖሩም፥ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በቁጥርም በዓይነትም በብዛት የሚገኙበት መስተዳድራዊ ቀጠና ነው።

> ከላይ በተቀመጡት ጉዳዮች መነሻነት ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ **(33)** ያገኘው መገለጫ "*ተሟጋች ቡድኖች*" ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(24)** ያስመዘገበው ደግሞ "*ነፃ ሚዲያ*" ነው። በአጠቃላይ የአዲስ አበባ መስተዳድር የቁጥጥር እና ሚዛን ድምር ውጤት **142/225** ነው።

## የዜግነት ነፃነቶች

### ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚተዳደሩ መገናኛ ብዙኃንም ሆኑ ሌሎች መድረኮች የሐሳብ ብዝኃነት የማይታይባቸው ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ አንዳንድ ሐሳቦች ይታፈናሉ። መገናኛ ብዙኃኑ የሚያስተላልፏቸው መረጃዎች የተመረጡና በበላይ ኃላፊዎች ፈቃድ የሚተላለፉ ናቸው።[232]

በተጨማሪም በከተማው የበይነመረብ አገልግሎት ሲቆራረጥና በአንዳንድ አገልግሎቶችም ላይ ገደቦች ሲጣሉ የነበሩ ከመሆኑ የተነሳ ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት በአንድም በሌላም መንገድ የተገደበ እንዲሆን አድርገዋል።

### የመደራጀት ነጻነት

የከተማ አስተዳደሩ የፌዴራል መንግሥቱ መቀመጫ እንደመሆኑ መጠን በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉ የመደራጀት መብቶች በከተማ አስተዳደሩ ለሚኖሩ ዜጎች ተፈፃሚ ሲሆን፥ በከተማይቱ በርካታ ተቋማት ማዕከላቸውን አድርገው ይሠራሉ። የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና የፖለቲካ ፓርቲዎች ሥራዎቻቸውን በዋናነት በአዲስ አበባ የሚያከናውኑ ሲሆን፥ የመደራጀት፣ የመሰባሰብና የመቃወም መብት በሕግ የተረጋገጠ ነው።

231 የቡድን ውይይት ፤

232 የቡድን ውይይት ፤

ሆኖም፥ ይህ መብት ገደብ ሲጣልበት በተደጋጋሚ ታይቷል። በከተማ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብሰባዎችን እንዳያደርጉ፥ እንዲሁም የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም እንዳይሰባሰቡና መግለጫ እንዳይሰጡ ሆነዋል። በተጨማሪም በመሰባሰብ መብት ላይ ጫና የሚያሳድሩ አስተዳደራዊ አሠራሮችም ተዘርግተው የነበረ ሲሆን፥ አንደኛው በሆቴሎች አዳራሽ ተከራይቶ ስብሰባ ለማድረግ የፖሊስ ፈቃድ ማግኘት ማምጣት አለባቸው የሚለው ሕጋዊ ያልሆነ ቅድመ ሁኔታ ነው። በከተማ መስተዳደሩም ሆነ አገር አቀፍ ተደራሽነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚሠሩ ተቋማት በብዛት የሚገኙት በአዲስ አበባ ከተማ በመሆኑ እነዚህ ከሕግ አግባብ ውጪ የሚደረጉት ጫናዎች እና ገደቦች በከተማ መስተዳደሩ እና በፌዴራል መንግሥት የሚፈጸሙ ናቸው።

## የሃይማኖት ነፃነት

በአዲስ አበባ የእምነት ነጻነት በሕገ መንግሥቱ በተደነገገው መሠረት የሚገዛ ሲሆን፥ ከተማዋ የእምነት ተቋማት በብዛት የሚገኙባት፥ እንዲሁም የአደባባይ በዓላት በስፋት የሚከወኑበት ናት። ሆኖም ግን፥ በሃይማኖቶች ውስጥ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት የታየ ሲሆን፥ በ2015 የነበረው የአንዋር መስጅድ ግጭትና የኦርቶዶክስ ክርስትና አማኞች ሰልፍ የቀሰቀሰው ጣልቃ ገብነት አዲስ አበባ ከተማን ማዕከል አድርጎ ነው። የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ችግሮችን እየፈጠረ የእምነት ነፃነትን እያሳጣ ይገኛል።[233]

የከተማ አስተዳደሩ የእምነት መሪዎቻቸውን ትዕዛዝ አክብረው ጥቁር የለበሱ የከተማ መስተዳድሩ ሠራተኞች ከሥራ ገበታቸው የታገዱ ቢሆንም፥ የትኛውም የእምነት ተቋም በማምለኪያ ስፍራው እንዳያመልክ የተጣለ ክልከላ አልነበረም[234]።

## የመንቀሳቀስ መብት

በአገሪቱ የፀጥታ ችግሮች ሲስተዋሉ በአዲስ አበባ ከፍተኛ የሆነ የመንቀሳቀስ ገደብ የሚጣል ሲሆን፥ በተለይ በከተማዋ የሚደረጉ ጉዞዎች ላይ የሰዓትና መሰል ክልከላዎች ይደረጋሉ። በከተማ አስተዳደሩ የፀጥታ አካላት ከዚህ ባለፈም በከተማዋ መኖሪያ ቤት የሚቀይሩ ሰዎች መደበኛ ባልሆነ መንገድ በተደራጁ ቡድኖች ለጫኝና አውራጅ የሚጠየቁት ያልተገባ ክፍያ ነዋሪዎች እንደልባቸው ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስና መኖሪያ የመመሥረት መብትን የገደበ ነው።

በተለያዩ ጊዜያት በከተማዋ የሚሠሩ የሞተር ሳይክልና ባለ ሦስት እግር ባጃጅ ተሽከርካሪዎች ሲከለከሉ የነበረ ሲሆን፥ ይህም በአንዳንድ አካባቢዎች የመንቀሳቀስና የመሥራት ነፃነትን ሲገድብ ታይቷል።[235]

233 የቡድን ውይይት ፤
234 የቡድን ውይይት ፤
235 የቡድን ውይይት ፤

## የግል ደኅንነትና ምስጢር ጥበቃ

አዲስ አበባ ውስጥ በ2015 አስቸጋሪ የነበረው ሰዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታና ያለ ፍርድ ቤት ዕውቅናና ትዕዛዝ ትፈለጋለህ ተብለው እየተወሰዱ የሚሰወሩ የነበረ መሆኑ ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ የበርካቶች ቤቶችና ንብረቶች ያለ ፈቃዳቸው ሲበረበሩና ሲፈተሹም ነበር።[236]

> ከላይ የተቀመጠ ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(33)** ያገኘው መገለጫ ***"የሃይማኖት ነፃነት"*** ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(24)** የተመዘገበበት መገለጫ ነጥብ ደግሞ ***"የግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ"*** ነው። በአጠቃላይ የአዲስ አበባ መስተዳደር ***"የዜግነት ነፃነቶች"*** ድምር ውጤት **139/225** ነው።

ከዚህ ውጤት ማየት እንደሚቻለው የከተማ መስተዳድሩ የዜግነት ነፃነትን በተመለከተ መልካም የሚባል አፈፃፀም ቢኖረውም፥ በተለይ ከግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ ረገድ ጉድለቶች እንዳሉበት ያሳያል።



# ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች

## መሠረታዊ ፍላጎቶች

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር በተለይ የምግብ ዋስትና እንዲረጋገጥ የተለያዩ ሙከራዎች የተደረጉ ቢሆንም፥ እነዚህ እርምጃዎች ተጠቃሚ የሚያደርጓቸወው አካላት ጥቂት ስለሆኑ ስልታዊ በሆነ መንገድ ለሁሉም ነዋሪዎች የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ረገድ አሁንም ችግሮች ይታያሉ። የከተማይቱ የምግብ ግብዓቶች በብዛት ከሌሎቹ የአገሪቱ ክልሎች የሚመጡ በመሆናቸውና አብዛኛው ነዋሪ ሸማች በመሆኑ በፀጥታ ችግሮችና በሌሎች ጉዳዮች አቅርቦቱ ይስተጓጎልበታል።

በከተማ አስተዳደሩ የጤና አገልግሎት በስፋት ተደራሽ ቢሆንም አሁንም የሕክምና ቁሳቁስና መድኃኒት አቅርቦት እጥረት አለ። የከተማው ነዋሪ የጤና መድኅን እንዲኖረው የተደረገ ቢሆንም፥ መድኃኒት ማግኘት ግን አዳጋች ነው።[237]

የንፁሕ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትም እንዲሁ በእኩልነትና በቀጣይነት ያልተረጋገጠ ሲሆን፥ በከተማዋ ለሚኖሩ ዜጎች የቤት አቅርቦት ጥያቄም በአመዛኙ አልተመለሰም።

236 የቡድን ውይይት ፣
237 የቡድን ውይይት ፣

## የትምህርት መብት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሻለ ሥራ የሠራው የዜጎችን የትምህርት መብት በማረጋገጥ መስክ ሲሆን፥ ለተማሪዎች ከትምህርት ገበታ እንዳይቀሩ በማሰብ ምግብ፥ የደንብ ልብስና የትምህርት ቁሳቁሶችን ያሟላል። ከመንግሥት ትምህርት ቤቶች በተጨማሪ በከተማው በርካታ የግል ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን፥ ለተደራሽነቱ አስተዋፅዖ አድርገዋል። ይሁንና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የሚመጣው የግል ትምህርት ቤቶች ክፍያ በከተማ አስተዳደሩ ትኩረት አላገኘም።[238]

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቅበላ/ተሳትፎ፥ በፆታ መመጣጠንና በክፍልና መተማሪ ጥምርታ የተሻለ ቢሆንም፥ በአጠቃላይ ቅበላ መጣኔ እንዲሁም ተማሪዎች በትክክለኛው ዕድሜ ትምህርት መጀመርን በተመለከተ ዝቅ ያለ አፈፃፀም አለው።[239]

## የስርዓተ ፆታ እኩልነት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስርዓተ ፆታ እኩልነት በሕግ የተረጋገጠ ቢሆንም፥ ዜጎች በተለያዩ ሁኔታዎች በፆታ ላይ ለተመሠረቱ ጥቃቶች ተጋላጭ ይሆናሉ። ይሁንና በምክር ቤቶችና በመንግሥት ኃላፊነቶች ላይ የሚወከሉ የሴቶች ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ ለስርዓተ ፆታ እኩልነት መረጋገጥ ራሱን የቻለ ሚና ይጫወታል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2017 አዲስ አበባ የሴቶች፣የሕፃናት፣የአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን መብትና ደህንነት የተረጋገጠባት፤የማህበራዊ ጥበቃ አገልግሎቶች የተስፋፉባት እና የስርዓተ-ፆታ እኩልነት የጎለበተባት ከተማ ሆና የማየት ራዕይ የሰነቀና የስርዓተ ፆታ ማካተትና ስርፀት አንዱ የከተማ አስተዳደር የሴቶችና ሕፃናት ቢሮ መዋቅር ክፍል ቢሆንም[240]፥ አሁንም ድረስ የሴቶች ተሳትፎና አካታችነት እጅግ ውሱን ነው።

## የግል ንብረት ጥበቃ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንብረት የማፍራትና የመጠቀም መብት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት መነሻነት የተረጋገጠ መብት ቢሆንም፥ ይህ መብት ለተለያየ የኢኮኖሚ አቅም ያላቸውን ያገናዘበ በሚሆን መልኩ እስከ ታች ወርዶ የተተገበረ አይደለም። ከዚህ ባለፈም፥ እንደ ኮንዶሚኒየም የጋራ መኖሪያ ቤቶች የመሳሰሉ ኅብረተሰቡ በቁጠባ የገነባቸው ንብረቶች መንግሥት ለሚፈልጋቸው ሰዎች በስጦታ ሲያበረክት የታየ ሲሆን፥ ይህ የሚሆነውም ዜጎች ሳይፈቅዱ ነው።[241]

ከዚህ ባለፈም፥ በከተማይቱ እየተበራከተ የመጣው የተሽከርካሪዎች ዝርፊያ ነዋሪዎችን እያማረረ እንደሚገኝ በተደጋጋሚ የተገለፀ ሲሆን[242]፥ ለዓመታት የዘለቀው በሞተር ብስክሌቶች የታገዘ[243] ዘረፋ አሁንም የቀጠለ ሲሆን፥ የከተማ አስተዳደሩ ፖሊስ ኮሚሽን በተለያዩ ጊዜያት የተሰረቁ ንብረቶችን ገዝተው የሚሸጡ ሰዎችን በቁጥጥር ስር እንዳዋለም ሲያሳውቅ ታይቷል።[244]

238 የቡድን ውይይት 1
239 Ministry of Education, the Education Statistics Annual Abstract 2021/22
240 ኢቃቂ ቃሊቲ ሴቶች፤ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ፅ/ቤት
241 የቡድን ውይይት 1
242 https://t.me/housinginaddisababa/8249 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
243 https://www.ena.et/web/amh/w/am_166467 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
244 https://www.ena.et/web/amh/w/am_166467 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

## የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ አለመመጣጠን የሚታይ ሲሆን፥ በተለይ ከኑሮ ውድነት ጋር ተያይዞ በከተማው የሚኖሩ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ወደ ዝቅተኛው የድህነት ወለል ሲወርዱ፥ መካከለኛ ገቢ ያለው ማኅበረሰብ ደግሞ እየጠፋ ወደ ድህነት ተጠግቷል። ከዚህ በተጨማሪ ከፍተኛ የሆነ ገቢ ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች ገቢያቸው እያደገና የገቢ ምንጫቸውም እየተበራከተ በመምጣቱ በደሀውና በሀብታሙ መካከል ያለው ልዩነት እየበረታ መጥቷል። እዚህ ላይ ሴቶችና አካል ጉዳተኞች የበለጠ ተጎጂ ናቸው።[245]

> ከላይ የተነሱትን ሐሳቦች ከግንዛቤ በማስገባት ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከመገለጫ ነጥቦቹ ውስጥ ከፍተኛውን ነጥብ **(36)** ያገኘው መገለጫ ***"የትምህርት መብት"*** ሲሆን፥ ዝቅተኛው ነጥብ **(14)** የተመዘገበበት መገለጫ ነጥብ ደግሞ ***"የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ"*** ነው። በአጠቃላይ የአዲስ አበባ መስተዳደር ***"ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች"*** ድምር ውጤት **119/225** ነው።

በዚህ ረገድ የከተማ አስተዳደሩ አነስተኛ የሚባል ነጥብ ሲሆን ያስመዘገበወው፥ በተለይ በመሠረታዊ ፍላጎቶችና በኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ ብዙ መሥራት ይጠበቅበታል።



# የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

## የኅዳጣን ብሔረሰቦች ነጻነት

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ተሰባጥረው የሚገኙ እንጂ ተሰባስበው የሚኖሩና ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ያላቸው ብሔሮች ባይኖሩም፥ በከተማ አስተዳደር ውስጥ እኩል የመወከል ጥያቄዎች ግን ይነሳሉ። ሆኖም፥ በከተማ አስተዳደሩ ይህንን መብት የጠየቀና የተነፈገ ቡድን የለም።[246]

ከዚህ ባለፈ ግን፥ ይህንን በጥልቀት የተመለከቱ ጥናቶች አይገኙም።

## የኅዳጣን መብቶች

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለይ የፖለቲካ ኅዳጣን ከፍተኛ የሆነ ጫና የሚደርስባቸው ሲሆን፥ ከገዥው ፓርቲ ጋር በቅርበት የማይሠሩና ፅኑ ተቃዋሚ ቡድኖች በተለያዩ መንገዶች ጫናዎች ይደርሱባቸዋል።

## የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

በተከማ አስተዳደሩ የተጋላጭ ቡድኖች የተሻለ ጥበቃ ቢኖርም በተለይ ሴቶች፣ አረጋውያንና ሕፃናት አሁንም

245 የቡድን ውይይት ፤
246 የቡድን ውይይት ፤

ለአካላዊ ጥቃቶች፥ አስገድዶ ስወራዎች እና ወሲባዊ ጥቃቶች ተጋላጭ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም፥ የፖለቲካ ትኩሳቶችን እየተከተለ የፖለቲካና የብሔር ኀዳጣን ለጥቃት ተጋላጭ እየሆኑ ስለመጡ አጠቃላይ የመጠቃት ስጋት እያየለ መጥቷል።

በተጨማሪም፥ በኀብረተሰብ ዓይን በንቀት የሚታዩ እንደ ወሲብ ንግድ ያሉ ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ሴቶች፥ እንዲሁም የጎዳና ተዳዳሪዎች በተደጋጋሚ በሕግ አስከባሪዎችና በማኀበረሰቡ ለአድልዎ፣ ለመገለና ለጥቃት ተጋላጭ ናቸው።[247]

## የብዝኀ ቋንቋ አስተዳደር

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አገልግሎት በአንድ ቋንቋ ብቻ ነው፤ በቅርቡ በከተማ አስተዳደሩ የተጀመሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችንና የትምህርት ቤቶችን ሥሞች ከአማርኛ በተጨማሪ በኦሮምኛ መጻፍ ብዝኃ ቋንቋን በከለሉ ሊያሰፋ ይችላል። በተጨማሪም፣ በከተማው የሚገኙ መገናኛ ብዙኃን በተለያዩ የአገሪቱ ቋንቋዎች ስርጭት ያደርጋሉ።[248]

ይሁንና፥ አሁንም ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የብዝሃ ቋንቋ ስብጥር በተለይ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት መሬት ላይ ወርዶ የማይታይ ሲሆን፥ አገልግሎት ፈላጊዎች በሚፈልጉትና የተሻለ የአገልግሎት ርካታ በሚያገኙበት ቋንቋ መስተናገዳቸውን ዕውን ለማድረግ የከተማ አስተዳደሩ ብዙ ርቀት ይጠብቀዋል።

## የከተማ መስተዳድሩ አዳማጭነት

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማዋ ነዋሪ በርካታ ጥያቄዎችን የሚያነሳና በተለይ የፖለቲካ ኀዳጣን በነፃነት የመንቀሳቀስ መብት እንዲኖራቸው ተደጋጋሚ ጥያቄዎች የሚያቀርቡ ቢሆንም፥ ምላሽ በመስጠት ረገድ አሁንም ውሱንነቶች አሉ። ነገር ግን፥ ምንም እንኳን የውጤታማነት ጥያቄዎች ቢኖሩም በከተማ መስተዳድሩ ተቋማት ውስጥ ቅሬታ ማዳመጫ መንገዶች ተዘርግተዋል።[249]


> በዚህ መነሻነትም ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከላይ ከተጠቀሱት መገለጫ ነጥቦች ከፍተኛውን ነጥብ **(27)** ያገኘው ባሕሪ **“የተጋለጭ ቡድኖች ጥበቃ”** ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(22)** የተመዘገበበት ባሕሪ መገለጫ ደግሞ **“ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር”** ነው። በአጠቃላይ የአዲስ አበባ መስተዳደር **“ የኀዳጣን እና የተጋለጭ ቡድኖች ጥበቃ”** ድምር ውጤት **123/225** ነው።

## አጠቃላይ ውጤት

> ተሳታፊዎቹ ከሞሉት መጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከአምስቱ የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች ውስጥ የአዲስ አበባ መስተዳድር ከፍተኛውን ነጥብ **(142)** ያገኘው በ“ቁጥጥር እና ሚዛን” ሲሆን፥ ዝቅተኛውን **(106)** ያገኘው ደግሞ በ“መንግሥት ውጤታማነት” ነው። ከአምስቱ ባሕሪዎች ውስጥ አራቱ ከግማሽ በላይ ነጥብ ያስመዘገቡ ሲሆን አንዱ ባሕሪ (የመንግሥት ውጤታማነት) ግን ከግማሽ በታች ነጥብ አስመዝግቧል።

247 የቡድን ውይይት ፤
248 የቡድን ውይይት ፤
249 የቡድን ውይይት ፤

የሚከተለው ቻርት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ለባሕርያቱ ያገኘውን አጠቃላይ ውጤት ያሳያል።





ቻርት 4: የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የዴሞክራሲያዊነት ባሕርያት አጠቃላይ ውጤት

ከዚህ በታች የተቀመጠው ሰንጠረዥ ደግሞ የአዲስ አበባ መስተዳደርን የዴሞክራሲ ሒደት ለመለካት የተቀመጡ ባሕሪዎች እና መገለጫዎች ያስመዘመገቡትን ውጤት እና ድምር በዝርዝር ያሳያል።

| የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ | የባሕሪዎቹ መገለጫዎች | | | | | ድምር | የተሰናኘ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መ1 | መ2 | መ3 | መ4 | መ5 | | |
| የመንግሥት ውጤታማነት | 23 | 23 | 23 | 13 | 24 | 106 | 2.36 |
| ቁጥጥርና ሚዛን | 29 | 30 | 26 | 24 | 33 | 142 | 3.16 |
| የዜጎች ነፃነቶች | 27 | 30 | 33 | 25 | 24 | 139 | 3.09 |
| ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያ መብቶች | 18 | 36 | 26 | 25 | 14 | 119 | 2.64 |
| የጎዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | 25 | 23 | 27 | 22 | 26 | 123 | 2.73 |
| ድምር | 121 | 142 | 135 | 109 | 121 | 629 | 4.59 |

ሰንጠረዥ 7: የአዲስ አበባ መስተዳደር ሁሉም የዴሞክራሲ ባሕዎች እና መገለጫዎች ዝርዝር ውጤት (መ = መገለጫ)

በዚሁ መሠረት በሁሉም የዴሞክራሲ ባሕርያት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ያገኘው ድምር ውጤት *629 የተሰናኘ ድምር 4.59* ይሆናል፤ ይህም መስተዳድሩ ቢጫ ምድብ "ግትር" የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ተስተውሎበታል።



# የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር

## የመንግሥት ውጤታማነት

### የሕግ አውጪው ውጤታማነት

የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት (ጨፌ ኦሮሚያ) በክልሉ የሕግ አውጪነት ሥልጣን ያለው ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲ ጫናና መንግሥታዊ ያልሆኑ ስብስቦች ጫና አለበት። በተለይም በክልሉ በበርካታ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች በተለያዩ ባለስልጣናት እና ግለሰቦች ላይ ግድያና አፈና ስለሚፈፅሙ የምክር ቤት አባላትና የክልሉ ባለሥልጣናትም ለዚህ ድርጊት ሲጋለጡ ቆይተዋል[250]።

ከዚህ ባለፈም፥ በክልሉ ያሉ የተለያዩ ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች ብሎም ባለሀብቶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በውሳኔ አሰጣጥ ሒደቶች ላይ ጫና ያሳድራሉ። ምክር ቤቱም አንዳንዴ በጭብጨባ ድጋፉን ከማሳየት እና እጅ ከማውጣት የዘለለ ሚና አይኖረውም[251]።

### የሥራ አስፈፃሚ ውጤታማነት

የኦሮሚያ ክልል ሥራ አስፈፃሚ በሚሠራቸው ሥራዎች ከፍተኛ ጫና ያለበት ክልል ሲሆን፥ በተለይ በክልሉ የሚሠሩ ሥራዎች በፖለቲካ ፍላጎቶች በሚመሩ የትግል የመገናኛ ብዙኃንና ነቀፌታ ይቀርብባቸዋል። ይህ በተለይ በሸገር ከተማ ምሥረታ ላይ የታየ ሲሆን፥ የኦሮሚያ ክልል እነዚህን ግፊቶች ተቋቁሞ ውጤታማ መሆን ያዳግተዋል።

በሌላ መንገድ፥ የፌዴራል መንግሥት በክልሉ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድር ሲሆን፥ መፈፀም የሚፈልጋቸውን ጉዳዮች ግፊት በማድረግ በክልሉ ያስተገብራል። የዚህ አንዱ ማሳያ የበጋ ስንዴ እርሻ ሲሆን፥ ክልሉ በጠቅላይ ሚኒስትሩ በተሰጠው አቅጣጫ ሎሎች ምርቶች በሚመረቱበትን ስፍራ በሙሉ ስንዴ እንዲዘራ አድርጓል።[252] በክልሉ አስፈጻሚው አካል ማስፈን ያልቻለውን ሰላም እና መረጋገት ለመመለስ የፌደራል የጸጥታ ኃይል የበላይነት እየመራው በሽብርተኝነት ከተፈረጀው የኦሮሞ ነጻነት ሠራዊት (መንግሥት “ሸኔ” ይሏል) ጋር ውጊያ እያካሄደ ይገኛል።

250 የቡድን ውይይት 2
251 የቡድን ውይይት 2
252 የቡድን ውይይት 2

## የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ውጤታማነት

በኦሮሚያ ክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ቅጥር የሚፈፀመው በብቃት ሳይሆን በጥቅም፣ በዝምድናና በፖለቲካ ታማኝነት በመሆኑ፥ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። እየጨመረ የመጣው ለመንግሥት ባለስልጣናት እና ከፍተኛ አመራሮች ከፍተኛ ገንዘብ እየከፈሉ ዘመዶችን ማስሾም በ 2015ም እንደቀጠለ ነው።[253] ይህም በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሙስና እንዲንሰራፋ በር የከፈተ ሲሆን፥ ያለ ገንዘብ የዜግነት መብት የሆኑ አገልግሎቶችን ማግኘት አስቸጋሪ እይሆነ መጥቷል።[254] የመንግሥት የታችኛው መዋቅር ደግሞ በክልሉ በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ኃይሎች ጫና እየደረሰባቸው ነው።

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥም ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ያለ ሲሆን፥ ነፃ ሆኖ የሚሠራ የመንግሥት መሥሪያ ቤትም ሆነ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ማግኘት አዳጋች እየሆነ መጥቷል። ይህም፥ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውጤታማ እንዳይሆኑ እንቅፋት ይፈጥራል።

## የፀረ ሙስና ውጤታማነት

በኦሮሚያ ክልል የሙስና መከላከያ የሕግ ማዕቀፎችና ተቋማዊ አደረጃጀቶች ቢኖሩም፥ በክልሉ ሙስና በስፋት ተንሰራፍቶ ይገኛል። ይህ የሆነበት ምክንያትም ሙስና እንደ ጥፋት ታይቶ ሳይሆን ሰዎች ክስ የሚመሠረትባቸውና የሚታሰሩት፥ ጉዳዩ የፖለቲካ ግብ ማሳኪያ በመሆኑ ነው።[255]

በክልሉ በሚገኙ ተቋማት አገልግሎት ለማግኘት ያልተገባና የተጋነነ ገንዘብ መክፈል የተለመደ ከመሆኑም ባሻገር፥ በባለሀብቶችና በተለያዩ የፍላጎት ቡድኖች ጫና ምክንያትም በግድ ወደ ሙስና የሚገቡ አገልግሎት ሰጪዎች አሉ። ሙስና፥ በተለይም ጉቦ መስጠት የተለመደ ሆኗል።[256]

ከዚህ በተጨማሪም፥ በኦሮሚያ ክልል ከግብርና እና ግንባታ ግብዓቶች ጋር በተገናኘ ከፍተኛ ማጭበርበር የሚታይ ሲሆን፥ ለአብነትም በክልሉ ከ2300 ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ በሕገ-ወጥ መንገድ ሲዘዋወር በቁጥጥር ስር መዋሉ አንዱ ማሳያ ነው።[257] በተጨማሪም፥ በክልሉ የማጭበርበርና የኢ-ፍትሐዊነት ስጋቶች ስር የሰደዱ ናቸው።[258]

## ያልተማከለ አስተዳደር

የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት በክፍል አራት አንቀፅ 45 ሥር በክልሉ ያልተማከለ አስተዳደር እንደሚኖርና፥ እነዚህም አስተዳደራዊ መዋቅሮች ክልል፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ ተብለው መከፈላቸውን ይደነግጋል።[259]

253 የቡድን ውይይት 2
254 የቡድን ውይይት 2
255 የቡድን ውይይት 2
256 የቡድን ውይይት 2
257 https://www.fanabc.com/archives/204203https://www.fanabc.com/archives/204203 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
258 https://www.ena.et/web/amh/w/amh_3022968 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
259 https://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/Labsii_Lak_46_Bara_1994%5B1%5D_0.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

እነዚህ አደረጃጀቶች በሕገ መንግሥቱ ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጣቸው ቢሆንም፥ ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ ነፃና ገለልተኛ አይደሉም። በዞን ደረጃ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮች ካሉ ወደ ክልል ጥያቄ ቀርቦ የሚወሰን ሲሆን፥ እነዚህ አደረጃጀቶች የላይኛው መዋቅር የመቆጣጠሪያ መሣሪያዎች እንጂ ራሳቸውን ችለው የሚሠሩ አይደሉም።[260] ስለዚህ ንዑስ የመንግሥት መዋቅሮች ሥራቸው የሕዝቡን ተሳትፎ በማረጋገጥ ያልተማከለ አስተዳደርን ማስፈን ሊሆን አልቻለም። የዚህ አንዱ ማሳያ፥ በጉጂና ቦረና ዞኖች የሕዝብ ተሳትፎ ሳይደረግ የተወሰነው የአስተዳደር መዋቅር ለውጥ ወደ ብጥብጥ ማምራቱ ነው።

> ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ **(22)** ያገኘው የመንግሥት ውጤታማነት መገለጫ ***"ያልተማከለ አስተዳደር"*** ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(11)** ያስመዘገበው ደግሞ ***"የፀረ-ሙስና ውጤታማነት"*** ነው። በአጠቃላይ የኦሮሚያ ክልል ***የመንግሥት ውጤታማነት*** ድምር ውጤት **88/225** ነው።



## ቁጥጥር እና ሚዛን

### የሕግ አውጪው ሥልጣን

የኦሮሚያ ክልል የሕግ አውጪ አካል (ጨፌ ኦሮሚያ) የቁጥጥርና ሚዛን ሥራ መሥራት የሚያስችሉት ቋሚ ኮሚቴዎችን የመሠረተ ቢሆንም፥ እነዚህ ኮሚቴዎች እምብዛም ውጤታማ አይደሉም። በታዛቢዎች ዓይን፣ የምክር ቤቱ አባላት የቁጥጥርና ሚዛን ሥራዎችን ለመሥራት ፍላጎት ያላቸውም አይመስሉም።[261]

የምክር ቤቱ ሥልጣን ችግሮች ሳይከሰቱ ማቆምን ጨምሮ ችግሮቹ ሲታዩ እስከሚታረሙ ክትትል ማድረግና ተጠያቂነት ማስፈን ቢሆንም፥ ጥፋት አለ ተብሎ የተቋማት ጉብኝት ቢያደርጉም የሚያናግሩትና መረጃ የሚጠይቁት በአጥፊነት ከተፈረጁት ወገን ብቻ ነው። በጥቅሉ፥ በሥራ አስፈፃሚው የሚወርደውን አቅጣጫ ብቻ የመከተልና የቁጥጥር ሚናቸውን ያለመከተል ችግር አለባቸው።[262]

### የፍርድ ቤት ነፃነት

የክልሉ የዳኝነት መዋቅር በሕገ መንግሥቱ ነፃ ተብሎ የተቋቋመ ሲሆን፥ ፍርድ ቤቶች በውሳኔ ረገድ ችግር ባይኖርበትም፥ የሥራ አስፈፃሚው የማይፈልገው ዓይነት ውሳኔ ከሆነ ጣልቃ የመግባት አዝማሚያዎች አሉ። ለአብነትም በክልሉ በአዳማ ከተማ ሦስት ዳኞች የታሰሩ ሰዎች እንዲፈቱ በመወሰቸናው ለእስር ተዳርገው ነበር[263]። ፖሊሶችም "ከበላይ አካል በመጣ ትዕዛዝ አለ" በማለት በፍርድ ቤት ነጽ የተባሉ ተጠርጣሪዎችን አይፈቱም፣ የፍርድ ቤቶችን ትዕዛዝ አያከብሩም።[264]

260 የቡድን ውይይት 2
261 የቡድን ውይይት 2
262 የቡድን ውይይት 2
263 https://ambadigital.net/2022/14364/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
264 https://m.facebook.com/diretube/photos/a.10152259127894587/10160852084094587/?locale=id_ID (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

በተቋማዊ አደረጃጀት ላይም ፍርድ ቤቶች በበጀትና በሰው ኃይል ረገድ በክልሉ መንግሥት ይሁንታ ማግኘት የሚጠበቅባቸው መሆኑ በነጻነታቸው አይ አሉታዊ ጫና ያሳድራል።

## ነፃ ሚዲያ

የኦሮሚያ ክልልን መሠረት አድርገው ወይንም በክልሉ ላይ ትኩረት አድርገው በክልሉ የሥራ ቋንቋ የሚሠሩ መገናኛ ብዙኃን ቢኖሩም፥ ሁሉም የሚወግኑላቸው የፖለቲካ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖች ይኖራሉ። ሚዲያዎችም እንዲሠሩ የሚፈቀድላቸው ከክልሉ መንግሥት ጋር የማይቃረኑ ከሆነ ብቻ ነው።[265]

የኦሮሚያ ክልል መገናኛ ብዙኃን (ኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትዎርክ) በቋንቋ ረገድ በበርካታ ቋንቋዎች አገልግሎት የሚሰጡና የይዘት ብዝኃነት ያለባቸው ቢሆኑም፥ እንደ ሌሎቹ የአገሪቱ ክልሎች ሁሉ የብቃት ውሱንነቶች አሉባቸው። ሚዲያው ጎራ ለይቶ የተቃውሞ ወይንም የድጋፍ ተብሎ የተከፈለ ሲሆን፥ በዚህ ሁኔታ የቁጥጥርና ሚዛን ሥራቸውን ይሠራሉ ማለት አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ፥ በአገሪቱ በጠቅላላው 63 ጋዜጠኞች በ2015 ሲታሰሩ፥ ጋዜጠኞች ለእስር ከተዳረጉባቸው ክልሎች አንዱ የኦሮሚያ ክልል ነበር።[266]

## ተሟጋች ቡድኖች

በኦሮሚያ ክልል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በብዛት የሚገኙ ቢሆንም፥ አሁንም ድረስ በርካታ ተግዳሮቶች አሉባቸው። በብዛት በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የልማትና የበጎ አድራጎት ሥራዎችን የሚሠሩ ድርጅቶች ቢሆኑም፥ ጥቂት የሰላም ግንባታ፣ የአድቮኬሲና የዴሞክራሲ አቀንቃኝ ድርጅቶች እየተፈጠሩ ነው። አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሠሩና መሰል ድርጅቶችም በሚንቀሳቀሱባቸው አካባቢዎች ላሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች መብቶች ያቀነቅናሉ።

በክልሉ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ስብሰባዎችን ለማድረግ አዳራሽ ሲፈልጉ ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ሲሆን፥ አድቮኬሲ ላይ የተሠማሩ ድርጅቶች ላይ ገደቦች ይበረታሉ። ከዚህ ባለፈም፥ በፌዴራል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ፈቃዳቸውን በየዓመቱ ማደስ ይጠበቅባቸው የነበረውን ሲያስቀር የኦሮሚያ ክልልን ጨምሮ ሌሎችም ክልሎች በክልሎቹ ተንቀሳቅሶ ለመሥራት አሁንም ድረስ በየዓመቱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ፈቃድ መታደስ አስገዳጅ ነው።[267] በዚህም ምክንያት፥ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ፈቃዳችን ላይታደስልን ይችላል በማለት ጠንካራ የአድቮኬሲ ሥራዎችን ከመሥራት ይቆጠባሉ።

> ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ **(36)** ያገኘው መገለጫ ***"ተሟጋች ቡድኖች"*** ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(19)** ያስመዘገበው ደግሞ ***"የሕግ አውጪው ሥልጣን"*** ነው። በአጠቃላይ የኦሮሚያ ክልል የቁጥጥር እና ሚዛን ድምር ውጤት **137/225** ነው።

265 የቡድን ውይይት 2

266 https://www.cardeth.org/sites/default/files/2018-01/CARD-Media-Landscape-in-Ethiopia.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

267 የቡድን ውይይት 2

በዚህ ውጤት መሠረት የክልሉ የሕግ አውጪ አካል የቁጥጥርና ሚዛን ሥራውን ከተቋማዊ አደረጃጀት ባለፈ ወደ ተግባር ማውረድ ይጠበቅበታል። የተሟጋች ቡድኖች ውጤትም ቢሆን የተሻለ ነው እንጂ፥ በርካታ ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች አሉ።



## የዜግነት ነፃነቶች

### ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት

የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት ሐሳብን የመግለጽ ነፃነትን በአንቀፅ 29 ሥር የሚደነግግ ሲሆን፥ ይህም ድንጋጌ ከፌዴራሉ ሕገ መንግሥት የተቀዳ ነው። ሆኖም፥ በ2015 በኦሮሚያ ክልል በርካቶች ሐሳባቸውን በመግለጻቸውና በመቃወማቸው ለጥቃት፣ ለእስርና ለስደት ተዳርገዋል።[268]

በክልሉ መንግሥት ስር የሚተዳደሩ የመገናኛ ብዙኃንም የድጋፍ ድምፆችን ካልሆነ በስተቀር ለየት ያሉ ሐሳቦችን አያስተናግዱም፤ በተቃዋሚ ጎራ ያሉ አካላትም ሐሳባቸውን የሚያስተጋቡበት መገናኛ ብዙኃን አላቸው። ይሁንና በብዛት ተቀማጭነታቸው ከአገር ውጪ ነው። የትጥቅ ትግል የመሠረቱ ቡድኖች ደግሞ በክልሉ መስተዳድር የሐሳብ ብዝኃነት የማይስተናገድ እና ለሰላማዊ ትግል በር ስለተዘጋ ነው ብለው ይሞግታሉ። በሌላ ወገን፥ በክልሉ ለየት ያለ ሐሳብ የሚያንፀባርቁ አካላት ማኅበራዊ የትስስር ገጾችን የሚጠቀሙ ሲሆን፥ በክልሉ ባሉ ግጭቶች ሳቢያ ግን በበርካታ አካባቢዎች የኢንተርኔት አገልግሎት በ2015 ተቋርጦ ቆይቷል።[269]

### የመደራጀት ነፃነት

የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት እንዳለው የሚደነግግ ሲሆን፥ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና የመቃወም መብትም እንዲሁ በሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ተረጋግጧል። እንደ ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳዮች ቢሮ ያሉ የመንግሥት ተቋማት ሠራተኞች በማኅበር ለመደራጀት ሲፈልጉ ድጋፍ ያደርጋሉ።

በክልሉ ተመዝግበው የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችም በርካታ ሲሆኑ፥ ሁሉንም ዓይነት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እኩል ተስፋፍተዋል ማለት ግን አይቻልም። በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የአድቮኬሲ ድርጅቶች ቢደራጁም በሙሉ አቅማቸው እንዳይሠሩ የሚያደርጓቸው ተግዳሮቶች አሉ።[270]

268 የቡድን ውይይት 2
269 የቡድን ውይይት 2
270 የቡድን ውይይት 2

## የሃይማኖት ነፃነት

የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግስት በአንቀፅ 27 ስር የሃይማኖት፣ የሕሊናና የነፃነት መብትን ለነዋሪዎች የሚያጎናፅፍ ሲሆን፥ በክልሉ መንግትና ሃይማኖት የተለያዩ ስለመሆናቸው፥ አንዱ በሌላው ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባም ተደንግጓል። ሆኖም ግን ይህ ድንጋጌ በተግባር ይፈተናል፥ እምነቶችንና የእምነት ተቋማትን ለፖለቲካ ዓላማ የመጠቀም ፍላጎቶች ጉልህ ናቸው።

በሃይማኖቶችና በእምነቶች መካከል ባሉ ግንኙነቶች ማኅበራዊ ግጭቶች እየታዩ ሲሆን፥ ከይዞታና ከክብረ በዓላት ጋር በተገናኘም የሚታዩ ግጭቶች በ2015 ሊቆሙ አልቻሉም።

## የመንቀሳቀስ መብት

የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት የመዘዋወር መብትን የሚያጎናፅፍ ሲሆን፥ ማንኛውም ሰው የክልሉ ነዋሪም ሆነ በሕጋዊ መንገድ ወደ ክልሉ የገባ ሰው በክልሉ የመዘዋወር፥ በመረጠው ቦታ መኖሪያ የመመሥረት፣ የመሥራትና በፈለገው ጊዜ የመልቀቅ መብትን ደንግጓል።

ነገር ግን፣ በክልሉ የሚታዩ ከዚህ ድንጋጌ ጋር የሚቃረኑ ድርጊቶች አሉ። ለአብነትም በክልሉ ሸገር ከተማ አስተዳደር ሲመሠረት በርካቶች ቤታቸው ፈርሶ የተፈናቀሉ ሲሆን፥ በክልሉ የሚገኙ ግጭቶችም መንገዶችን ተደራሽ እንዳይሆኑ በማድረግ የመንቀሳቀስ መብት እንዲገደብ አድርገዋል። የመንግሥት ባለሥልጣናት ሳይቀሩ የሚታገቱ፣ የሚጠቁና የሚገደሉ ሲሆን፥ በክልሉ እገታ የተበራከተበት ዓመት ነበር። ሰዎችም ከእገታ ለመለቀቅ ከፍተኛ የቤዛ ገንዘብ ሲጠየቁ ነበር።

## የግል ደኅንነትና ምሥጢር ጥበቃ

ከሌሎቹ መብቶች ጋር በተመሳሳይ የክልሉ ሕገ መንግሥት የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብትን ደንግጎ የሚያጎናፅፍ ቢሆንም፥ ከፍተኛ የሆነ የደኅንነት ስጋት ያለበት ክልል ነው። በክልሉ ተቃዋሚዎችን ጨምሮ ሰዎች እየታፈኑ ይወሰዱ የነበረ ሲሆን፥ በክልሉ ከሕግ ውጪ የሆኑ ግድያዎችና ስወራዎችም አሉ። በክልሉ የሚታሰሩ ሰዎችም የት እንደሚታሰሩ የመግለጽና ደኅንነታቸውን ቤተሰቦቻቸው እንዲከታተሉ ከማድረግ አኳያም ሰፊ ክፍተት ታይቷል።

ከዚህ ባለፈም፥ ያልታወቁ ቡድኖች በሚባል የሚጠቀሱ አካላት በዜጎች ላይ ጥቃቶችን የሚሰነዝሩ ሲሆን፥ ሰዎች እየታፈኑ፥ እየተደበደቡና እየተሰወሩ ማን እያደረጋቸው እንደሆነም አይታወቅም።[271]

በተጨማሪም፥ በኦሮሚያ ክልል የሰዎች ቤቶችና ንብረቶች ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ በብዛት የሚበረበሩ ሲሆን[272]፥ "በድብቅ ተቀረፀ" እና "ሾልከው የወጡ" ተብለው ለአደባባይ የበቁ የግለሰብ ንግግሮች በማኅበራዊ ትስስር ገፆች ላይ በስፋት ሲዘዋወሩ ታይተዋል።

271 የቡድን ውይይት 2

272 https://tbinternet.ohchr.org/_layouts/15/TreatyBodyExternal/DownloadDraft.aspx?key=/FD43aUhbzqqLOGcCynonODEA0th1PQG642FYd1zC6ki6uTid3B3/q9P+uoRCkXsojOaawEYUl+FJTpmnr7iKQ== (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)

ከላይ የተነሡ ነጥቦች ከግንዛቤ ገብተው በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ (37) ያገኘው መገለጫ *"የሃይማኖት ነፃነት"* ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ (14) የተመዘገበበት መገለጫ ነጥብ ደግሞ *"የግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ"* ነው። በአጠቃላይ የኦሮሚያ ክልል *"የዜግነት ነፃነቶች"* ድምር ውጤት 125/225 ነው።



## ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች

### መሠረታዊ ፍላጎቶች

በክልሉ የመሠረታዊ ፍላጎት ተደራሽነትን ለማሻሻል የተሠሩ ተግባራት ያሉ ሲሆን፥ በተለይም በክልሉ የሚገኘው ማኅበረሰብ አሁንም የመጠጥ ውኃና የጤና ተደራሽነት ችግሮች ያሉበት ነው። በክልሉ የሚታዩ ግጭቶችም የመሠረተ ልማቶችን የሚያወድሙ ሲሆን፥ በጤና፣ በትምህርት እና ሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎት ሲጪ ተቋማት ላይ ጥቃቶች ይደርሳሉ።

በተጨማሪም፥ በ2015 በክልሉ አስከፊ ድርቅ የነበረ ሲሆን፥ በተለይ እንደ ቦረና፣ ምሥራቃዊ ባሌ ያሉ አርብቶ አደር አካባቢዎች ኑሯቸውን የሚመሩባቸውን የቀንድ ከብቶች በብዛት አጥተዋል። ይህም የአካባቢዎቹን በምግብ ራስን የመቻል አቅም ጎድቶታል።[273]

### የትምህርት መብት

በኦሮሚያ ክልል የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ የሚሰጥ ሲሆን፥ የተሻለ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎችም የተለየ ትምህርት ቤት ተከፍቶ ተማሪዎችን ይቀበላል። ከዚህ በተጨማሪም፥ በክልሉ አዳዲስ ትምህርት ቤቶች የተገነቡ ሲሆን፥ የትምህርት ዕድል ተፈልጎላቸው እንዲማሩ የሚደረጉ የክልሉ ተማሪዎችም በርካቶች ናቸው።

ሆኖም ግን፥ አሁንም ቢሆን የትምህርት ተደራሽነት ችግር ያለ ሲሆን፥ በተለይ የግጭት ቀጠና የሆኑ የክልሉ አካባቢዎች ትምህርት ቤቶች ከመውደማቸውም ባለፈ በርካታ የትምህርት ተቋማት ተዘግተዋል፥ ተማሪዎችም ለጥቃት ስለሚዳረጉ ወደ ትምህርት ገበታ መሄድ አልቻሉም።

### የስርዓተ ፆታ እኩልነት

የኦሮሚያ ክልል በሕገ መንግሥቱ የሴቶችን መብቶች ለብቻው የሚደነግግ ሲሆን፥ የስርዓተ ፆታ እኩልነት ለማረጋገጥ የሕግ ማዕቀፍ ችግሮች የሉም። በክልሉ ይህንን እንዲሠሩ የተዋቀሩ የሴቶች ጉዳይ ቢሮና ሌሎች ተቋማት አሉ። ሆኖም ግን፥ ሴቶች ላልተመጣጠነ ጥቃት የሚጋለጡባቸው የግጭትና የጥቃት ሁኔታዎች አሉ።

273 የቡድን ውይይት 2

በክልሉ ሴቶች ላልተገባ ጥቃት የሚጋለጡም ሲሆን፥ አስገድዶ መስወርና የግድያዎች ሰለባም ይሆናሉ።[274]

### የግል ንብረት ጥበቃ

የክልሉ ማኅበረሰብ የንብረት ጥበቃ በሕግ የተረጋገጠለት ቢሆንም፥ ይህ መብቱ ግን በተግባር ችግር ውስጥ ሲወድቅ ይታያል። ሆኖም፥ በተለያዩ ሁኔታዎች በርካታ የክልሉ ነዋሪዎች ያለካሳ ንብረቶቻቸውን የሚያጡ ሲሆን፥ በተለይ በግጭት አካባቢ ያሉ ዜጎች፥ የአርሶና አርብቶ አደር ንብረቶች ጥበቃ አይደረግም።[275]

### የኢኮኖሚ የመመጣጠን ደረጃ

በኦሮሚያ ክልል የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ በገጠሩና በከተማ ነዋሪው፥ በሴቶችና በወንዶች እንዲሁም የፖለቲካ ትስስር ባላቸውና በሌላቸው አካላት መካከል ሰፊ ሲሆን፥ በተለይ የገጠሩ አምራች አርሶ አደር የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቱ አናሳ ነው[276]።

> ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(30)** ያገኘው የዜግነት መብቶች ባሕሪ መገለጫ *"የትምህርት መብት"* ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(25)** ያስመዘገቡት መገለጫዎች ደግሞ *"መሠረታዊ ፍላጎቶች"* እና *"የግል ንብረት ጥበቃ"* ናቸው። በአጠቃላይ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች *"ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች"* ድምር ውጤት **133/225** ነው።



## የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

### የኅዳጣን ብሔረሰቦች ነፃነት

በኦሮሚያ ክልል ተሰባስበው የሚኖሩ ኅዳጣን ቢኖሩም፥ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ጥያቄ አቅርበው የተከለከሉ የሉም። ለአብነትም በባቱ ሐይቅ ደሴቶች የሚኖሩ የዛይ ብሔረሰብ አባላት ቢኖሩም፥ ራሳቸውን በራሳቸው ያለ ጣልቃ ገብነት እያስተዳደሩ አይደለም። ራሱን የቻለ አስተዳደርም የለውም።

### የኅዳጣን መብቶች

በክልሉ የሚኖሩ የተለያዩ ኅዳጣን ባሕሎቻቸውንና እምነቶቻቸው በክልሉ ለመተግበር ክልከላ የሌለባቸው ቢሆንም፥ በክልሉ እንዲሁም በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች በተለያዩ አካባቢዎች የነበሩ ግጭቶች ብሔር ተኮር መልክ ነበራቸውና እነዚህ ግጭቶች አሁንም ድረስ በአንዳንድ ኅዳጣን ዘንድ ያጠሉት ስጋት አለ።[277]

274 የቡድን ውይይት 2
275 የቡድን ውይይት 2
276 የቡድን ውይይት 2
277 የቡድን ውይይት 2

## የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

በክልሉ በ2015 ከቀጠለው ግጭት ጋር ተያይዞ ሴቶች፥ ሕፃናትና አረጋውያን ለተለያዩ ጥቃቶች የተጋለጡ ሲሆን፥ በአንዳንድ አካባቢዎች በግጭቶች ሳቢያ ቤት ንበረታቸውን አጥተዋል። በክልሉ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ አካል ጉዳተኞችም እንዲሁ በችግር ምክንያት ትምህርታቸውን መከታተል ሳይችሉ ቀርተዋል።

## የብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር

የኦሮሚያ ክልል የሥራ ቋንቋ ኦሮሚኛ ቋንቋ ቢሆንም በተለይ አማርኛ በስፋት በክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሥሞችን ለመጻፍ ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን፥ በክልሉ የሚወጡ ሕጎች በአፋን ኦሮሞ፣ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተሙ ናቸው። በትምህርት ቤቶችም አማርኛ ትምህርት ይሰጣል።

ከዚህ በተጨማሪ በክልሉ የሚገኙ መገናኛ ብዙኃን አማርኛ፥ ሲዳምኛ፥ ትግርኛ፥ አኙዋ፥ ኑዌርና ሌሎች የአገሪቱን ቋንቋዎች የሚጠቀሙ ሲሆን፣ ይህ በተለይ በብሮድካስት መገናኛ ብዙኃን ዘርፍ ጎልቶ ይታያል። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎቶች በስፋት የሚሰጡት በአንድ ቋንቋ ቢሆንም[278] በክልሉና በአጎራባች አበባቢዎች ያለውን ብዝነሃት የሚያማክሉ የትምህርትና የመገናኛ ብዙሃን አገልግተቶች እየተስፋፉ ነው።

## የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት

የኦሮሚያ ክልል በተደጋጋሚ ጥቃት የሚደርስባቸውንና ተጋላጭ የሆኑ ኅዳጣን ጥበቃ እንዲያደርግላቸው በተደጋጋሚ ጥሪ ቢያቀርቡም ክልሉ ለተጠቂዎች ጥበቃ የሚያደርግበት አቅም ያልነበረውና፥ የክልሉን ሰላምና ደኅንነት ለማስጠበቅ በፌዴራል መንግሥት ኃይሎች ላይ ጥገኛ የነበረበት ዓመት ነው።[279]

> ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(33)** ያስመዘገበው መገለጫ *"ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር"* ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(26)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* ነው። በአጠቃላይ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል መንግሥት *"የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* ድምር ውጤት **146/225** ነው።

ይህ ባሕሪ ክልሉ የተሻለ ነጥብ ያገኘበት ሲሆን፥ በኅዳጣን ቡድኖች ጥበቃ ረገድ ሰፊ ክፍተት እንዳለበት የሚያመለክትም ነው።


# አጠቃላይ ውጤት

እያንዳንዱ መገለጫ ሊያገኝ የሚችለው ከፍተኛ ነጥብ 225 (=45*5) ከፍተኛ፣ እንዲሁም ዝቅተኛ ነጥብ 45 (=9*5) ነው። ተሳታፊዎቹ ከሞሉት መጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከአምስቱ የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች ውስጥ ከፍተኛውን ነጥብ (146) ያገኘው *"የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* ሲሆን፤ ዝቅተኛውን (88) ያገኘው መገለጫ ደግሞ *"የመንግሥት ውጤታማነት"* ነው። ከአምስቱ ባሕሪዎች ውስጥ አራቱ ከግማሽ በላይ ነጥብ ያስመዘገቡ ሲሆን አንዱ ባሕሪ (*"የመንግሥት ውጤታማነት"*) ከግማሽ በታች ነጥብ አስመዝግቧል።

278 የቡድን ውይይት 2
279 ቡድን ውይይት 2

የሚከተለው ቻርት የኦሮሚያ ክልል መስተዳድር በሁሉም ባሕሪዎች ያገኘውን አጠቃላይ ውጤት ያሳያል።

## የዴሞክራሲያዊነት መገለጫዎች አጠቃላይ ውጤት (የኦሮሚያ ክልል መስተዳድር)





ቻርት 5: የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች አጠቃላይ የምዘና ውጤት

ከዚህ በታች የተቀመጠው ሰንጠረዥ ደግሞ የኦሮሚያ ክልል መስተዳደርን የዴሞክራሲ ሒደት ለመለካት የተቀመጡ ባሕሪዎች እና መገለጫዎች ያስመዘመገቡትን ውጤት እና ድምር በዝርዝር ያሳያል።

| የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ | የባሕሪዎቹ መገለጫዎች | | | | | ድምር | የተሰናኘ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መ1 | መ2 | መ3 | መ4 | መ5 | | |
| የመንግሥት ውጤታማነት | 15 | 19 | 21 | 11 | 22 | 88 | 1.96 |
| ቁጥጥርና ሚዛን | 19 | 25 | 31 | 26 | 36 | 137 | 3.04 |
| የዜጎች ነፃነቶች | 22 | 27 | 37 | 25 | 14 | 125 | 2.78 |
| ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያ መብቶች | 25 | 30 | 26 | 25 | 27 | 133 | 2.96 |
| የኅዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | 30 | 29 | 26 | 33 | 28 | 146 | 3.24 |
| ድምር | 111 | 130 | 141 | 120 | 127 | 629 | 459 |

ሰንጠረዥ 8: የኦሮሚያ ክልል መስተዳደር ሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪዎች እና መገለጫዎች ዝርዝር ውጤት

በዚሁ መሠረት በሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪዎች የኦሮሚያ ክልላዊ ብሔራዊ መስተዳድር ያገኘው ድምር ውጤት 629 *የተሰናኘ ድምር* ሲቀየር 4.59 ይሆናል፤ በዚህም መስተዳድሩ ቢጫ ምድብ (“ግትር”) የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ላይ ይገኛል።



# የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መስተዳደር

## የመንግሥት ውጤታማነት

### የሕግ አውጪው ውጤታማነት

የጋምቤላ ክልል ምክር ቤት በክልሉ መዋቅራዊ ውክልና የዘለለ ሚና የሌለውና በክልሉ ጉዳዮች ላይ በቀጥታ ተሳትፎ አድርጎ ጣልቃ ሲገባ አይታይም። ለምሳሌ በክልሉ አብዛኛው ሹመት የሚሰጠው ከላይ ወደ ታች ነው፤ ከላይ መመሪያ እስከሚወርድ ሁሉም ይጠብቃል። የውጭ አገር ታጣቂዎች (ከደቡብ ሱዳን የሚነሱ የሙርሌ ጉሳ ታጣቂዎች) ወደ ክልሉ ገብተው ከክልሉ ነዋሪዎች ጋር ተጋጭተው ሰው ሲገድሉ የክልሉ ምክር ቤት ምንም ሲያደርግ አልታየም።[280]

በተጨማሪም በገዢው ፓርቲና በመንግሥት መካከል የተሰመረ ግልጽ መሥመር ስለሌለ የፓርቲ ተፅዕኖ በምክር ቤቱ ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ነው። በዚህም ምክንያት የፓርቲ አመራር እጆች የክልሉን ምክር ቤት ይዘውራሉ። በክልሉ ያለው ባለሀብት፥ በተለይም በግብርና ሥራ የተሠማሩ ኢንቨስተሮች ቀላል የማይባል ጫና ያሳድራሉ።

በ2015 ምክር ቤቱ ያላያቸውና ያላፀደቃቸው ሹመቶች የነበሩ ሲሆን፥ ምክር ቤቱ አስፈፃሚው የሚያስበውን ማስፈፀሚያ መሣሪያ ነው።

### የሥራ አስፈፃሚው ውጤታማነት

የጋምቤላ ክልል እጅግ ከፍተና የፀጥታ ፈተናዎች የበዙበት ከመሆኑ የተነሳና በርካታ የፌዴራል የፀጥታ አካላት በክልሉ ከመኖራቸው የተነሳ በክልሉ ከፀጥታና ሌሎች ጉዳዮች ጋር በተገናኘ አስፈፃሚው አካል የሚኖረው የመወሰን ነፃነት በእጅጉ የተገደበ ነው። ከዚህ በተጨማሪም፥ በማዕከላዊነት ውሳኔ በሚሰጥበት የፓርቲ ስርዓት ውስጥ ስለሚገኝም የፓርቲው ተፅዕኖ የክልሉ መንግሥት በክልሉ ነባራዊ ሁኔታ ላይ ተመሥርቶ የፖሊሲ ውሳኔዎችን እንዳይሰጥ ያደርገዋል።

በክልሉ ያለው ከፍተኛ የግብርና ኢንቨስትመንትና ተያያዥ ፍላጎቶች፥ እንዲሁም የአቅም ማነስ የክልሉን ሥራ አስፈፃሚ በከፍተኛ ተፅዕኖ ሥር ያሳድረዋል። በተጨማሪም፥ በክልሉ ያሉ የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖች ከደቡብ

280 የቡድን ውይይት 6

ሱዳን ታጣቂዎች ጋር በተለያዩ መንገዶች ስለሚገናኙና በክልሉ ግጭቶችን በትብብር የሚፈጥሩ ታጣቂዎች በመኖራቸውም በሥራ አስፈፃሚው ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡[281]

## የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አገልግሎት ውጤታማነት

በክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሠራተኞች የሚቀጠሩባቸው መስፈርቶች የተቀመጡና ደረጃ የወጣለት፣ በቅጥር ማስታወቂያ የሚነገር ቢሆንም፥ የሠራተኞች ቅጥር አሁንም በዘመድና ትስስር ይፈፀማል። በዚህም ምክንያት ተቋማት ለሚሰጧቸው አገልግሎቶች የማይመጥኑ ሰዎች በክልሉ መሥሪያ ቤቶች ተቀጥረው ይሠራሉ።

በተጨማሪም በክልሉ ያለው የጎሳ መሳሳብና ፖለቲካ ቅጥሮች ላይ ጫና ስለሚያሳድርም፥ ብቃት ያላቸው ሰዎች አይቀጠሩም፤ ተቀጣሪዎቹ ብቃት ስለማይኖራቸውም ለፖለቲካና ለሌሎች ጣልቃ ገብነቶች ተጋላጭ ይሆናሉ።

## የፀረ ሙስና ውጤታማነት

በጋምቤላ ክልል በተለያዩ ከኢንቨስትመንት፣ ከሠራተኛ ቅጥርና ካልተገባ ጥቅም ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ሙስና የሚፈፀም ሲሆን፥ በክልሉ በርካታ የሕዝብ ሀብት ጉዳት ቢደርስበትም ተጠያቂነት ግን አልሰፈነም። ይሁን እንጂ ይህንን ማድረግ የሚያስችል የሕግና ተቋማዊ አደረጃጀት ቢኖርም ከውጤታማነት አኳያ ክፍተቶች አሉበት፡፡[282]

## ያልተማከለ አስተዳደር

የጋምቤላ ክልል መንግሥት በክልል፣ ብሔረሰብ ዞኖች፣ አስተዳደራዊ ወረዳዎችና ቀበሌዎች የተዋቀረ ቢሆንም፣ ንዑሳን መዋቅሮቹ ከላይኛው የመንግሥት አስተዳደር ተቆርሶ የሚሰጣቸው ሥልጣን እንጂ በመዋቅራቸው በሕገ መንግሥቱ የተሰጣቸው ሥልጣኖች መተግበሪያ አይደሉም። ከዞንና ከዛ በታች ያሉ መዋቅሮች ያልተማከለ የፋይናንስ አስተዳደር የላቸውም፤ ራሳቸውም የገንዘብ ምንጭ አፈላልገው የሚፈፅሟቸው የአካባቢውን ማኅበረሰብ ፍላጎት ያገናዘቡ ፕሮጀክቶችም የሏቸውም፤ ቢኖሩም ኢ-ምንት ናቸው፡፡[283]

> እነዚህ ጉዳዮች ተገናዝበው ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ **(22)** ያገኘው መገለጫ *"ያልተማከለ አስተዳደር"* ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(11)** ያስመዘገበው ደግሞ *"የፀረ - ሙስና ውጤታማነት"* ነው። በአጠቃላይ የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል መስተዳድር ***የመንግሥት ውጤታማነት*** ድምር ውጤት **90/225** ነው፡፡

ይህ ክልሉ በሁሉም ባሕሪዎች ያገኘው ዝቅተኛው ውጤት ሲሆን፥ የክልሉ መንግሥት ከአማካይ ነጥብ በታች ነው ያገኘው። ይህም የሚያሳየው ውጤታማ መንግሥት በክልሉ ለማምጣት በርካታ ክፍተቶች እንዳሉ ነው።

281 የቡድን ውይይት 6

282 የቡድን ውይይት 6

283 የቡድን ውይይት 6

## ቁጥጥር እና ሚዛን

### የሕግ አውጪው ሥልጣን

የጋምቤላ ክልል ምክር ቤት በክልሉ አስፈፃሚ አካል ላይ ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችሉት ቋሚ ኮሚቴዎችና ንዑሳን ኮሚቴዎች ያሉት ቢሆንም፥ እነዚህ ኮሚቴዎች ሥራ አስፈፃሚው ሪፖርት ሲያቀርብላቸው ከማዳመጥና ከመጠየቅ በዘለለ እስከ ታች ሔደው ሥራዎችን ሲከታተሉና ሲገመግሙ አይታዩም።

የክልሉ ምክር ቤት ሥራ አስፈፃሚው የሚወስናቸውን ውሳኔዎች ሲያስቀይሩ ወይንም እንዲሻሻሉ ሲያደርጉም አልታዩም። ለአብነትም በክልሉ የተለያዩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የማስዋብ ሥራዎች ሲሠሩ በምክር ቤቱ አባላት ስለ ገንዘብ ምንጩም ሆነ ስለ ሥራውና ስለ ወጪው መመጣጠን እምብዛም ጥያቄ ሲያቀርቡ አልታዩም።[284]

### የፍርድ ቤት ነፃነት

በጋምቤላ ክልል ሕገ መንግሥት ነፃ የዳኝነት አካል እንደሚኖር የሚደነግግ ሲሆን፥ የትኛውም ፍርድ ቤት ከመንግሥት፣ ግለሰቦች ወይንም ሌላ ተፅዕኖዎች ነፃ እንደሆኑም ያስቀምጣል።[285]

ነገር ግን የክልሉ ፍርድ ቤቶች በሥራ አስፈፃሚው አካል፥ በክልሉ በሚገኙ ባለሀብቶች እንዲሁም በዝምድና ተፅዕኖ የሚደረግባቸው ሲሆን፥ የፍርድ ቤቶች ውሳኔም በተሟላ ሁኔታ አይከበርም።[286]

### የፍርድ ቤት ገለልተኝነት

ፍርድ ቤቶች በተለያዩ ፍላጎቶች ጫና ሥር ስለሚወድቁ ከፍተኛ የሆነ የገለልተኝነት ጥያቄ አለባቸው። በተለይ ፍርድ ቤቶች የፖለቲካና የሌሎች ፍላጎቶች ገለልተኝነታቸው የሚፈተን ሲሆን፥ በክልሉ ያለው የጎሳ ፖለቲካ፣ የአስፈፃሚውና ሌሎች ጣልቃ ገብነትና በመሳሰሉ ጉዳዮች የፍርድ ቤቶች ገለልተኝነት ውጤታማ ነው ለማለት ያዳግታል።[287]

### ነፃ ሚዲያ

በጋምቤላ ክልል በዋናነት የክልሉ መገናኛ ብዙኃን ድርጅት ሲሆን፥ ይህ ድርጅት ልክ በሌሎች ክልሎች በስፋት እንደሚታየው ለክልሉ መንግሥት የሚወግንና ሌሎች ድምፆችን የማያስተናግድ ነው። በሌላ ወገን፥ በክልሉ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚዎች እንደ ጠላት ስለሚታዩም በመገናኛ ብዙኃን ዕድል አያገኙም።

---

284 የቡድን ውይይት 6
285 https://www.ethcriminalawnetwork.com/system/files/GAMBELA%5B1%5D.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
286 የቡድን ውይይት 6
287 የቡድን ውይይት 6

ሐሳባቸውን ሳይደብቁ የሚገልጹ ግለሰቦች ስለሚፈረጁ ሥማቸውን እየሸሸጉ በማኅበራዊ ትስስር ገፆች ሐሳባቸውን የሚያስተጋቡ ቢሆንም፥ በእነዚህ ሐሳቦች እየተጠረጠሩ ጥቃት የሚደርስባቸውም አሉ።[288]

## ተሟጋች ቡድኖች

በጋምቤላ ክልል ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትና ነፃ ሚዲያ የሚፈተኑ ስለሆነ በክልሉ የሚገኙ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በብዛት ትኩረት የሚያደርጉት በልማትና በበጎ አድራጎት ሥራዎች ላይ ነው። የአድቮኬሲ እንዲሁም የዴሞክራና ሰብዓዊ መብቶች ማቀንቀን ላይ የሚሠሩ ድርጅቶች ፈቃድ ለማግኘትም ሆነ እንደ ልባቸው ለመንቀሳቀስ ያስቸግራቸዋል።[289]

በክልሉ የሚንቀሳቀሱና የክልሉን መንግሥት በመቆጣጠር ሥራዎች የተሰማሩ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ለጥቃት ሲጋለጡ የነበረ ሲሆን፥ እስከ እስርና መንገላታት፣ ጽሕፈት ቤታቸውን እስከማጣትና እስከመዘረፍ ሲደርሱም ነበር።

> በእነዚህ መሠረትም ከተሳታፊዎቹ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛ ነጥብ **(23)** ያገኘው መገለጫ ***"የፍርድ ቤት ገለልተኝነት"*** ሲሆን ዝቅተኛ ነጥብ **(17)** ያስመዘገቡት የቁጥጥርና ሚዛን መገለጫዎች ደግሞ "***የሕግ አውጪው ሥልጣን***" እና "***ነፃ ሚዲያ***" ናቸው። በአጠቃላይ የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል መስተዳድር የቁጥጥር እና ሚዛን ድምር ውጤት **97/225** ነው።

ይህ ውጤት እንደሚያሳየውም፥ ክልሉ ከፍተኛ የሆነ የቁጥጥር እና ሚዛን ዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ ጉድለት ያለበት ሲሆን፥ በተለይ የሕግ አውጪው ገለልተኛ ሆኖ በመሥራት ላይ በርካታ መሻሻሎች መኖር እንደሚኖርበት ማሳያ ነው።



# የዜግነት ነፃነቶች

## ሐሳብን የመግለፅ ነፃነት

በጋምቤላ ክልል ሰዎች በሐሳባቸው ምክንያት ለተለያዩ ፍረጃዎችና ማስፈራሪያዎች ስለሚዳረጉ ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት በክልሉ በእጅጉ የተገደበ ነው። ይሁን እንጂ፥ በክልሉ ሕገ መንግሥት ማንኛውም ሰው የፈለገውን ሐሳብ የመያዝና የመግለጽ መብት ተሰጥቶታል። በክልሉ የሚገኙ መገናኛ ብዙኃንም በክልሉ የሚገኙ የተለያዩ አካላትን ሐሳቦችን የማያስተላልፉ ሲሆን፥ በመንግሥትና በገዥው ፓርቲ እሳቤዎች ብቻ የተሞሉ ናቸው።

በጋምቤላ የተለዩ ሐሳቦችን ማንፀባረቅ ለጥቃትና ለአደጋ ስለሚጋልጥም፥ ሰዎች የሐሰት ሥሞችን እየተጠቀሙ በማኅበራዊ ትስስር ገፆች መልዕክቶቻቸውን ያስተጋባሉ። እንዲህም ሆኖ የሚፅፉ ሰዎች ከማስፈራሪያ አልዳኑም።[290]

288 የቡድን ውይይት 6
289 የቡድን ውይይት 6
290 የቡድን ውይይት 6

## የመደራጀት ነፃነት

በጋምቤላ ክልል የመደራጀት መብት በሕግ የተረጋገጠ ሲሆን፥ የክልሉ ሕገ መንግሥት ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር መደራጀት እንደሚችል ደንግጓል። በክልሉ ለንግድ ሥራዎች መደራጀት የማይከለከል ሲሆን፥ በተለይ ግን ለፖለቲካ ዓላማና ለዜግነት ተሳትፎ መደራጀት ከፍተኛ ጫና ይገጥመዋል።

በክልሉ ጎልተው የወጡ የሲቪክ ማኅበረሰብ ድርጅቶች የማይታዩ ሲሆን፥ በመንግሥት ድጋፍ የሚደረግላቸውና የሚበረታቱት ለንግድ ሥራ አልያም ለልማትና በጎ አድርጎት የሚደራጁ ስብስቦች አሉ።[291]

በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች በክልሉ ሁኔታዎች ላይ መግለጫዎችን ሲያወጡም ማስፈራሪያዎችና ወከባ ይደርሱባቸዋል።

በጋምቤላ ክልል የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለይ ከ2011 ወዲህ ከትጥቅ ትግል የተመለሱ ናቸው። እነዚህ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወደ ሰላማዊ የፖለቲካ ሲመጡ የጠበቁት የፖለቲካ ምህዳር በክልሉ የሌለ ሲሆን፥ በክልሉ አዲስ የተመሰረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎችም አይታዩም። እንደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መረጃ በክልሉ የሚገኙ ተፎካካሪ/ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች አራት ብቻ ሲሆኑ፥ ቢያንስ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከክልሉ ገዥ ፓርቲ ብልፅግና ጋር ተዋህዷል። እነዚህ አራት ፓርቲዎች ከገዥው ፓርቲና ከአገራዊው የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) ፓርቲ ጋር በመሆን ክልላዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት መስርተዋል።[292]

በክልሉ የተመሰረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጎሳ ፉክክሮች የሚስተዋሉባቸው[293] ሲሆኑ፥ አዳዲስ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሲመሰረቱም እምብዛም አይታይም።

## የሃይማኖት ነፃነት

በጋምቤላ ክልል በ2015 ሃይማኖታዊ ክልከላዎችም ሆኑ የእምነት ነፃነትን የሚገዳደሩ ክልከላዎች ሲደረጉ አልታየም። የክልሉ ሕገ መንግሥትም የእምነት ነፃነትን የሚያጎናፅፍ ሲሆን፥ መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውንም ይደነግጋል።

ይሁንና፥ በጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኝ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከግቢው እንዲለቅና ሌላ ቦታ እንዲመሠረት ሲጠየቅ ውዝግቦች ተነስተው ነበር፤ በዚህም የታሰሩ የሃይማኖት አባቶች ነበሩ።[294]

## የመንቀሳቀስ ነፃነት

በጋምቤላ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች በታጣቂዎች ጥቃት ይደርስባቸው ስለነበር በክልሉ የመንቀሳቀስና ሰዎች በሚፈልጉበት አካባቢ ሥራ የመሥራት መብታቸው በእጅጉ ተጨቁኖ ነበር። የክልሉ መንግሥትም በሕገ መንግሥቱ የመንቀሳቀስ መብትን፣ በየትኛውም የክልሉ አካባቢ መኖሪያ መመሥረትን እንዲሁም ሠርቶ መኖርን የደነገገ ቢሆንም፥ በዚህ ረገድ በስፋት ለተስተዋሉ ችግሮች የሰጠው መፍትሔም እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም።

291 የቡድን ውይይት 6
292 https://www.ena.et/web/amh/w/am_125377 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
293 https://www.ethiopianreporter.com/119892/ (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
294 የቡድን ውይይት 6

ክልሉ በጎሳን መሠረት ባደረጉ የፖለቲካ ትኩሳትቶች የሚታመስ ከመሆኑም አኳያ፥ አንድ ሰው የርሱ/የርሷ ጎሳ ከማይኖርበት አካባቢ ወደ ሌላው መሔድ አይችልም - ለጥቃትም ይጋለጣል።

በተጨማሪም፥ የሙርሌ ጎሳ ታጣቂዎች ከደቡብ ሱዳን ድንበር እያቋረጡ ወደ ክልሉ በመግባት ጥቃቶችን የሚያደርሱ ሲሆን፥ ሰዎች በአካባቢያቸው ለመቆየትና በፈቃዳቸው ብቻ መልቀቅ ሲፈልጉ እንዲለቅቁ የሚያደርጋቸው ሁኔታ የለም። በእነዚህና መሰል ጥቃቶች ሰዎች የመሠረቷቸውን የኑሮ ሁኔታዎችም ሲያዛቡ ነበር።[295]

## የግል ደኅንነትና የምሥጢር ጥበቃ

በክልሉ የግል ሕይወት መጠበቅና መከበር በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 27 የተደነገገ ቢሆንም፥ በ2015 በተደጋጋሚ በነበሩ ጥቃቶች የዜጎች ሕይወት ሲነጠቅ፣ ሕፃናት ሲታፈኑ የነበሩበት ዓመት ነበር። በክልሉ ታጣቂዎች የሚንቀሳቀሱ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ሰዎች ከቦታ ቦታ ለመንቀሳቀስ ደኅንነት አይሰማቸውም።[296]

> ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(42)** ያገኘው መገለጫ ***"የሃይማኖት ነፃነት"*** ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(17)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ ***"ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት"*** ነው። በአጠቃላይ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ***"የዜግነት ነፃነቶች"*** ድምር ውጤት **123/225** ነው።

ክልሉ በዚህ ባሕሪ የተሻለ የሚባል አፈፃፀም ቢኖረውም፥ በተለይ ሐሳብን በመግለጽ ነፃነት ላይ ሰፊ ክፍተት የታየበት ነው።



# ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች

## መሠረታዊ ፍላጎቶች

የጋምቤላ ክልል ከመሠረታዊ ፍላጎቶች አቅርቦት አንፃር ትልቅ ችግር ያለ ሲሆን፥ በክልሉ በቂ የውኃ አቅርቦት፥ እንዲሁም የትምህርት ተደራሽነት የሌለ ሲሆን፥ በክልሉ በተደጋጋሚ በሚከሰት ጎርፍና ግጭቶች እነዚህ ችግሮች ይባባሳሉ። በክልሉ የሚኖሩ ዜጎች የመሠረታዊ ፍላጎቶች እንዲሁም የመልማት መብቶች በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉ ቢሆነም፥ በተግባር ግን ክልሉ በእነዚህ መሥፈርቶች ወደ ኋላ የቀረ ነው።

295 የቡድን ውይይት 6
296 የቡድን ውይይት 6

ከዚህ ባለፈም፥ በክልሉ በተፈጠረው የአቅርቦት እጥረትና በኑሮ ውድነት በመሠረታዊ ፍላጎቶች ላይ ቀላል የማይባል ተፅዕኖ ነበረው።[297] በክልሉ ለውጭ ዜጎች የተዘጋጁ የመጠለያ ካምፖችን በማየትም የክልሉ ሕዝብ በክልሉ ካለው የመሠረታዊ ፍላጎት አቅርቦት የተሻለ በመጠለያ አለ በማለት ቅሬታ ያቀርባል።

## የትምህርት መብት

በጋምቤላ ክልል የትምህርት ቤቶች ተደራሽነት አነስተኛ ነው። በተለይ በግጭቶች አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ትምህርት ያቋረጡ ሲሆን፥ አንዳንዶችም ለአጭር ጊዜ ብቻ ያስተማሩም ነበሩ። በከተማ አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች የተሻለ ተደራሽነት ያላቸው ሲሆን፥ በገጠራማ አካባቢዎች በተለይ በክረምት ወራት ትምህርት ቤት መሄድ ያስቸግራል።

በትምህርት ቁልፍ ማሳያዎች ከሆኑት የትምህርት ቤት ተደራሽነትና መጠነ ተሳትፎ አናሳ ሲሆኑ፥ መጠነ ማቋረጥም በስፋት ይታያል። ትምህርት ቤቶችም ምክንያታዊ በሆነ ርቀት ላይ አይገኙም።[298]

## የስርዓተ ፆታ እኩልነት

ጋምቤላ ክልል የሴቶች መብቶች በሕገ እየተረጋገጡና ተቋማዊ መዋቅሮችም የሴቶችን መብቶች ለማስከበር የሚሠሩ ቢሆንም፥ በክልሉ ግን ከፍተኛ የሆነ የስርዓተ ፆታ ኢ-እኩልነት ተንሰራፍቶ ይገኛል።[299] ለአብነት እድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች ሆኖ የሚዳሩ ሴቶች 22 በመቶ[300] ሲሆኑ፥ ከ18 ዓመት በታች የሚዳሩ ደግሞ 44 በመቶ[301] አካባቢ ናቸው።

ሴቶች ከወንዶች ጋር ያላቸው የትምህርት ተሳትፎ እየተቀራረበ ቢሆንም፥ በክልሉ የተንሰራፋው ያለ ዕድሜ ጋብቻና ፆታ ተኮር ጥቃት አሳሳቢ ነው።

ሴቶች በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በክልል ምክር ቤቶች ውክልናቸው እያደገ የመጣ ሲሆን፥ አሁንም ብዙ የሚቀረው ነው። ሴቶች በቤት ውሥጥም የሚጨቆኑ ሲሆን፥ የወንዶች በጋብቻ ላይ ጋብቻ መመሥረት ባሕላዊ ተቀባይነት አለው።[302]

## የግል ንብረት ጥበቃ

የጋምቤላ ክልል ሕገ መንግሥት የንብረት መብትን የሚያጎናፅፍ ቢሆንም፥ በተለይ የሴቶች የንብረት መብቶች ምሉዕ ሆነው አልተከበሩም። ለምሳሌ በፍቺ ጊዜ ሴቶች በጋራ ያፈሩት ንብረት የመካፈል ዕድል የላቸውም።

ከዚህ ባለፈም፥ በግጭቶች ሳቢያ በሚኖሩ ጥቃቶች የዜጎች ንብረቶች የሚጠቁና ጉዳት የሚደርስባቸው፣ ብሎም የሚወድሙ ቢሆንም፥ ለዚህ ጥበቃና ከለላም አይደረግም።[303]

297 የቡድን ውይይት 6
298 የቡድን ውይይት 6
299 የቡድን ውይይት 6
300 https://reproductive-health-journal.biomedcentral.com/articles/10.1186/s12978-021-01234-4 (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
301 https://www.unicef.org/ethiopia/media/1506/file/Surprising%20trends%20in%20child%20marriage%20in%20Ethiopia.pdf (ጥቅምት 2016 የተጎበኘ)
302 የቡድን ውይይት 6
303 የቡድን ውይይት 6

## የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ

በጋምቤላ ክልል በገጠሩና በከተማ ነዋሪው መካከል የኢኮኖሚ አለመመጣጠን በስፋት የሚስተዋል ሲሆን፥ በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው አለመመጣጠን ደግሞ ይበልጡኑ የሰፋ ነው። ሴቶች የግል ገቢያቸውም ቢሆን በወንዶች ቁጥጥር ስር ያለ ሲሆን፥ ከወንዶች ጋር ንብረት የመካፈል መብታቸውም አልተረጋገጠም።[304]

> እነዚህን በማገናዘብ ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(27)** ያገኘው መገለጫ *"የግል ንብረት ጥበቃ"* ሲሆን፥ ዝቅተኛው ነጥብ **(13)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"መሠረታዊ ፍላጎቶች"* ነው። በአጠቃላይ የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል መስተዳድር *"ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች"* ድምር ውጤት **102/225** ነው።



# የኀዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

## የኀዳጣን ብሔረሰቦች ነፃነት

በጋምቤላ ክልል በሕገ መንግሥቱ ዕውቅና የተሰጣቸው አምስት ብሔሮች አሉ። ይሁንና በክልሉ ተሰባስበው የሚገኙ ሌሎች ብሔሮች ያሉ ሲሆን፥ አንዳንዱም የእውቅና ጥያቄ ኖሯቸውም ምላሽ አላገኙም። ከእነዚህ መካከል ሳቦ ይጠቀሳል። ከዚህ ውጪም፥ የክልሉ ዞኖች የብሔረሰብ ዞኖች ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ የራሳቸውን ዞኖችና የወረዳ አስተዳደሮች እየጠየቁ ያሉ አካባቢዎች አሉ።

እነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ እያገኙ ባለመሆኑም በክልሉ መንግሥት ላይ ተስፋ መቁረጥ ይታያል።[305]

## የኀዳጣን መብቶች

በክልሉ የሚገኙ የፖለቲካና የብሔር ሕዳጣን መብቶቻቸውን ለማስከበር የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ምላሽ አያገኙም። በክልሉ የሚገኙ ብሔሮች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ትምህርት መማር እንደሚችሉ ሕገ መንግሥቱ ቢደነግግም ይህ በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ አልሆነም።[306]

## የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ

በክልሉ ያሉ ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ ብዙ ክፍተቶች ያሉበት ነው። ለምሳሌ በጋምቤላ ክልል ያላቻ ጋብቻ እጅግ የተንሰራፋ ሲሆን፥ ይህም የሕፃናት ጥበቃ ጉድለትን ያመላክታል። የሴቶችና የአካል ጉዳተኞችም ጥበቃ እንዲሁ የተጓደለ ነው።

304 የቡድን ውይይት 6
305 የቡድን ውይይት 6
306 የቡድን ውይይት 6

በክልሉ በስፋት በሚከሰቱ ግጭቶች ሳቢያም በርካታ ተጋላጭ ቡድኖች ለጥቃት ይጋለጣሉ። በክልሉ ተፈጥሯዊ አቀማመጥና የጎርፍ አደጋን ለመከላከል ከተሠሩ ሥራዎች አነስተኛነት የተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭነትም በክልሉ ሁሌም የሚታይ ክስተት ነው[307]።

## የብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር

የጋምቤላ ክልል ሕገ መንግሥት የክልሉ የሥራ ቋንቋ አማርኛ እንደሆነ ቢደነግግም፥ ሁሉም ቋንቋዎች እኩል ዕውቅና እንዲኖራቸውና ሁሉም በፈለጉት ቋንቋ መማር እንዲችሉ ይደነግጋል። በተጨማሪም፥ በክልሉ የሚገኙ ሌሎች ብሔሮች በመረጡት ቋንቋ እንዲማሩ ይፈቅዳል። የክልሉ መገናኛ ብዙኃንም በተለያዩ ቋንቋዎች ስርጭት ያደርጋል።[308]

ከመገናኛ ብዙሃን በተጨማሪ በክልሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚሰጧቸው አገልግሎቶች በብዛት በአማርኛ የተገደቡም ናቸው። ሆኖም የብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር ከማስፋት አኳያ በርካታ ውሱንነቶች ያሉ ሲሆን፥ በክልሉ የሚከፈቱ ብዝኃ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች (ለምሳሌ ኢፈ ቦሮ የአዳሪ ትምህርት ቤት) በዚህ ረገድ ሚና ይጫወታል።

## የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት

የክልሉ መንግሥት በተለያዩ ጊዜ እየተነሱና ሲንከባበሉ የመጡ የወረዳ አስተዳደሮች የማዋቀር ጥያቄቶች እስካሁን ምላሽ አልሰጠም። በጋምቤላ ከተማም በቀበሌዎች የሚኖሩ ነዋሪዎች ቁጥር ስለማይመጣጠን የስድስተኛ ቀበሌ ምሥረታ ጥያቄዎች አሉ። በተጨማሪም፥ ዞኖችና ወረዳዎች የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ያነሳሉ።

> እነዚህን ነጥቦች ታሳቢ አድርጎ ከተሳታፊዎች በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከፍተኛውን ነጥብ **(34)** ያስመዘገበው መገለጫ *"ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር"* ሲሆን ዝቅተኛው ነጥብ **(17)** የተመዘገበበት መገለጫ ደግሞ *"የክልሉ መንግሥት አዳማጭነት"* ነው። በአጠቃላይ የጋምቤላ ክልል *" የጎዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* ድምር ውጤት **133/225** ነው።


## አጠቃላይ ውጤት

ተሳታፊዎቹ ከሞሉት መጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ መሠረት ከአምስቱ የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪዎች ውስጥ ከፍተኛውን ነጥብ (133) ያገኘው *"የጎዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"* ሲሆን፤ ዝቅተኛውን (90) ያገኘው መገለጫ ደግሞ *"የመንግሥት ውጤታማነት"* ነው። ከአምስቱ ባሕሪዎች ውስጥ ሁለቱ ("የጎዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ" እና "የዜጎች ነፃነቶች") ከግማሽ በላይ ነጥብ ያስመዘገቡ ሲሆን የተቀሩት 3ቱ ባሕሪያት ከግማሽ በታች ነጥብ ያስመዘገቡ ናቸው።

የሚከተለው ቻርት የጋምቤላ ክልል መስተዳድር ለአምስቱ የዴሞክራሲ ባሕሪዎች ያገኘውን አጠቃላይ ውጤት ያሳያል።

307 የቡድን ውይይት 6
308 የቡድን ውይይት 6

### የዴሞክራሲያዊነት መገለጫዎች አጠቃላይ ውጤት (የጋምቤላ ክልል መስተዳድር)




ቻርት 6: የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል መስተዳድር የዴሞክራሲያዊነት መለኪያዎች አጠቃላይ የምዘና ውጤት

ከዚህ በታች የተቀመጠው ሰንጠረዥ ደግሞ የጋምቤላ ክልል መስተዳደርን የዴሞክራሲ ሒደት ለመለካት የተቀመጡ ባሕሪያት እና መገለጫዎች ያስመዘመገቡትን ውጤት እና ድምር በዝርዝር ያሳያል።

| የዴሞክራሲያዊነት ባሕሪ | የባሕሪዎቹ መገለጫዎች | | | | | ድምር | የተሰናኘ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | መ1 | መ2 | መ3 | መ4 | መ5 | | |
| የመንግሥት ውጤታማነት | 19 | 18 | 20 | 11 | 22 | 90 | 2.0 |
| ቁጥጥርና ሚዛን | 17 | 20 | 23 | 17 | 20 | 97 | 2.16 |
| የዜጎች ነፃነቶች | 17 | 19 | 42 | 22 | 23 | 123 | 2.73 |
| ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያ መብቶች | 13 | 22 | 24 | 27 | 16 | 102 | 2.27 |
| የኀዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | 31 | 31 | 20 | 34 | 17 | 133 | 2.96 |
| ድምር | 97 | 110 | 129 | 111 | 98 | 545 | 3.84 |

ሰንጠረዥ 9: የጋምቤላ ክልል መስተዳደር ሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪያት እና መገለጫዎች ዝርዝር ውጤት

በዚሁ መሠረት በሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪዎች የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል መስተዳድር ያገኘው ድምር ውጤት *545 ወደ ተሰናኘ ድምር* ሲቀየር *3.84* ይሆናል፤ በዚህም መስተዳድሩ ቢጫ ምድብ (“ግትር”) የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ላይ ያርፋል።


5

# መደምደሚያ

በአምስቱ ባሕሪዎች ከተቀመጡት አምስት፣ አምስት መገለጫዎች ስር ካሉት ነጥቦች በአጠቃላይ ከአንድ ክልል ሊገኝ የሚችለው ትልቁ ውጤት 1125 (45*5*5) ሲሆን ዝቅተኛው ደግሞ 255 (=9*5*5) ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ መገለጫ ደግሞ ሊያገኝ የሚችለው ከፍተኛ ነጥብ 225 (=45*5) ከፍተኛ፤ እንዲሁም ዝቅተኛ ነጥብ 45 (=9*5) ሲሆን የሁሉም ክልል ተደምሮ ከአንድ መገለጫ ሊገኝ የሚችለው ከፍተኛ ነጥብ 1350 (225*6) እንዲሁም ዝቅተኛው 270 (=45*6) ነው፡፡

የስድስቱንም ክልሎች አጠቃላይ ውጤት ስንመለከት የሲዳማ ክልል መስተዳድር 669 ነጥብ በማግኘት ቀዳሚውን ደረጃ የያዘ ሲሆን፤ ከሁሉም ያነሰ ነጥብ ያስመዘገበው ደግሞ የጋምቤላ ክልል መስተዳድር ሲሆን ያስመዘገበው ነጥብም 545 ነው። የሲዳማ፣ ኦሮሚያ እና አዲስ አበባ መስተዳድሮች፤ ከአምስቱ የዲሞክራሲ ባሕሪዎች በአራቱ ከግማሽ ነጥብ (112.5) በላይ ያስመዘገቡ ሲሆን ሦስቱም መስተዳድሮች ከግማሽ ነጥብ በታች ያስመዘገቡበት ባሕሪ "የመንግሥት ውጤታማነት" ነው። የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አማራ እና ጋምቤላ ክልል መስተዳድሮች ደግሞ ከአምስቱ የዲሞክራሲ ባሕሪያት በሁለቱ ባሕሪያት ብቻ ከግማሽ ነጥብ(112.5) በላይ አስመዝግበው ተገኝተዋል። የአማራ ክልል መስተዳድር ከግማሽ ነጥብ በላይ ያስመዘገበባቸው ሁለቱ ባሕሪዎች "የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ" እና "ቁጥጥር እና ሚዛን" ሲሆኑ፥ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መስተዳደር በ"የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ" እና "ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያ መብቶች" እንዲሁም የጋምቤላ ክልል መስተዳድር ደግሞ በ"የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ" እና በ"ዜግነት ነፃነቶች" ከግማሽ ነጥብ በላይ አስመዝግበዋል። በአጠቃላይ ስናየው "የመንግሥት ውጤታማነት" በስድስቱም ክልሎች ከግማሽ ነጥብ በታች የተመዘገበበት የዴሞክራሲ ባሕሪ ነው። ከዚህ በታች ያለው ቻርት የክልል አስተዳደሮች በአጠቃላይ ለእያንዳንዱ የዴሞክራሲ ባሕሪዎች ያገኙትን ውጤት ያሳያል።

**አጠቃላይ የክልሎች ድምር ውጤት**




ቻርት 7: አጠቃላይ የክልሎች ድምር ውጤት

አጠቃላይ ውጤቱን ዴሞክራሲያዊነትን ለመለካት ከተቀመጡት ባሕሪዎች አንፃር ስንመለከተው ደግሞ ***"የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ"*** ምዘናው በተካሄደባቸው ስድስቱ ክልሎች ውስጥ በአምስቱ ክልሎች ከፍተኛ ነጥብ በማስመዝገብ 1ኛ ደረጃን የያዘ ሲሆን፤ ***"የመንግሥት ውጤታማነት"*** በአምስት ክልሎች ዝቅተኛ ነጥብ በማስመዝገብ 5ኛ ደረጃን ይዟል። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ ዝርዝር መረጃዎችን ያሳያል።

| ክልል | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ | 5ኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| ሲዳማ | የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | የዜግነት ነፃነቶች | ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | ቁጥጥር እና ሚዛን | የመንግሥት ውጤታማነት |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | የዜግነት ነፃነቶች | የመንግሥት ውጤታማነት | ቁጥጥር እና ሚዛን |
| አማራ | የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | ቁጥጥር እና ሚዛን | ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | የዜግነት ነፃነቶች | የመንግሥት ውጤታማነት |
| አዲስ አበባ | ቁጥጥር እና ሚዛን | የዜግነት ነፃነቶች | የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | የመንግሥት ውጤታማነት |
| ኦሮሚያ | የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | ቁጥጥር እና ሚዛን | ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | የዜግነት ነፃነቶች | የመንግሥት ውጤታማነት |
| ጋምቤላ | የኅዳጣን እና የተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | የዜግነት ነፃነቶች | ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | ቁጥጥር እና ሚዛን | የመንግሥት ውጤታማነት |

**ሰንጠረዥ 10:** የክልል መስተዳደሮች ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ነጥብ ያስመዘገቡባቸው የዴሞክራሲ ባሕሪዎች

አምስቱ የዴሞክራሲ ባሕሪዎች እያንዳንዳቸው አምስት አምስት መገለጫዎች ያሏቸው ሲሆን አጠቃላይ 25 መገለጫዎች አሉ ማለት ነው። ከነዚህ መገለጫዎች ውስጥ ከሁሉም ክልል መስተዳድር ድምር አነስተኛውን ነጥብ (88) ያገኘው መገለጫ "የፀረ-ሙስና ውጤታማነት" ሲሆን፤ ከፍተኛውን ያገኘው ደግሞ የሃይማኖት ነፃነት (222) ነው። አብዛኛዎቹ መስተዳደሮች ላይ ከፍተኛ ነጥብ ያመጡት መገለጫዎች "የሃይማኖት ነፃነት" እና "ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር" ሲሆኑ፤ ዝቅተኛውን ደረጃ የያዙት ደግሞ "የፀረ-ሙስና ውጤታማነት" እና "መሠረታዊ ፍላጎቶች" ናቸው። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ በየክልል መስተዳደሩ ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገቡ ሦስት መገለጫዎች እና ዝቅተኛ ነጥብ ያስመዘገቡ ሦስት መገለጫዎች ይቀርባሉ።

| መስተዳድር | ከፍተኛ ደረጃ ያገኙ መገለጫዎች | | | ዝቅተኛ ደረጃ ያገኙ መገለጫዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 23ኛ | 24ኛ | 25ኛ |
| ቤኒሻንጉል | የሃይማኖት ነፃነት | ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር | የኀዳጣን መብቶች | የፀረ-ሙስና ውጤታማነት | ሐሳብን የመግለጽ ነፃነት | ነፃ ሚዲያ |
| ሲዳማ | የሃይማኖት ነፃነት | የኀዳጣን ብሔረሰቦች ነጻነት | ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር | የሕግ አውጪው ውጤታማነት | የፀረ-ሙስና ውጤታማነት | ነፃ ሚዲያ |
| አማራ | የኀዳጣን መብቶች | ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር | የኀዳጣን ብሔረሰቦች ነጻነት | የግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ | መሠረታዊ ፍላጎቶች | የሥራ አስፈፃሚው ውጤታማነት |
| አዲስ አበባ | የትምህርት መብት | የሃይማኖት ነፃነት | ተሟጋች ቡድኖች | መሠረታዊ ፍላጎቶች | የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ | የፀረ-ሙስና ውጤታማነት |
| ኦሮሚያ | የሃይማኖት ነፃነት | ተሟጋች ቡድኖች | ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር | የሕግ አውጪው ውጤታማነት | የግል ደኅንነት እና ምሥጢር ጥበቃ | የፀረ-ሙስና ውጤታማነት |
| ጋምቤላ | የሃይማኖት ነፃነት | ብዝኃ ቋንቋ አስተዳደር | የኀዳጣን መብቶች | የኢኮኖሚ መመጣጠን ደረጃ | መሠረታዊ ፍላጎቶች | የፀረ-ሙስና ውጤታማነት |

**ሰንጠረዥ 11:** የክልል መስተዳደሮች ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ነጥብ ያስመዘገቡባቸው የዴሞክራሲ ባሕሪዎች መገለጫዎች

ክልል መስተዳድሮች በሁሉም የዴሞክራሲ ባሕሪዎች ያስመዘገቡትን ውጤት ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡

| ደረጃ | መስተዳድር | የመንግሥት ውጤታማነት | ቁጥጥር እና ሚዛን | ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች | የዜግነት ነጻነቶች | የጎዳጣን እና ተጋላጭ ቡድኖች ጥበቃ | የተሰናኘ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሲዳማ | 2.49 | 2.58 | 2.78 | 3.33 | 3.69 | 4.95 |
| 2 | ኦሮሚያ | 1.96 | 3.04 | 2.96 | 2.78 | 3.24 | 4.59 |
| 3 | አዲስ አበባ | 2.36 | 3.16 | 2.64 | 3.09 | 2.73 | 4.59 |
| 4 | አማራ | 2.07 | 2.64 | 2.44 | 2.4 | 3.69 | 4.30 |
| 5 | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 2.24 | 2.07 | 2.71 | 2.49 | 3.07 | 4.03 |
| 6 | ጋምቤላ | 2 | 2.16 | 2.27 | 2.73 | 2.96 | 3.84 |
| አማካይ ድምር | | 2.19 | 2.61 | 2.63 | 2.8 | 3.23 | |

**ሰንጠረዥ 12:** የክልል/ከተማ መስተዳደሮች ለዴሞክራሲ መገለጫዎች ያስመዘገቧቸው የተሰናኘ ውጤት

ክልሎች ያመጡት አጠቃላይ ውጤት የዲሞክራሲያዊነት ባሕሪ ደረጃ ለመስጠት ከ1-9 ባለ የተሰናኘ ልኬት ያመጡት ድምር ነጥብ ተቀይሮ በሦስት ምድብ ይቀመጣል፡፡ ምድብ አንድ ከ1.0-3.0 ነጥብ ያመጡትን የሚያካትተው ቀይ ምድብ ሲሆን "አሉታዊ" እና እያሽቆለቆለ ያለ አስተዳደርን ያሳያል፡፡ ሁለተኛ፣ ከ3.01 እስከ 6.00 ነጥብ ያገኙትን የሚያካትተው ቢጫ ("ግትር") ምድብ ነው፤ ይህ ምድብ መሻሻልም፣ ማሽቆልቆልም ያላሳየን መስተዳድር ይወክላል፡፡ ከ6.01 እስከ 9.00 ነጥብ የሚያገኙት ደግሞ በአረንጓዴ ("ተራማጅ") ምድብ ይቀመጣሉ፤ እዚህ ምድብ ውስጥ ያሉ መስተዳድሮች መሻሻል ያስመዘገቡ ናቸው፡፡ በ2015 አፈፃፀማቸው የተመዘኑት ሁሉም ክልሎች በቢጫ ምድብ ውስጥ "ግትር" ሆነው ተገኝተዋል፡፡

| መስተዳድር | የተቀናጀ ውጤት | ምድብ |
|---|---|---|
| የለም | [6.01-9.00] | ተራማጅ |
| ሲዳማ | 4.95 | ግትር |
| ኦሮሚያ | 4.59 | ግትር |
| አዲስ አበባ | 4.59 | ግትር |
| አማራ | 4.30 | ግትር |
| ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 4.03 | ግትር |
| ጋምቤላ | 3.80 | ግትር |
| የለም | [1.00-3.00] | አሉታዊ |

**ሰንጠረዥ 13:** የመስተደድሮች የዴሞክራሲያዊነት ሒደት ምድብ

በዚህ መሠረትም፥ በክልሎች መካከል መበላለጥ ቢኖርም፥ ውጤቱ የሚያሳየው ግን የዴሞክራሲያዊነት ሒደቱ በዚህ ልኬት በተካተቱ ክልሎች ሁሉ እዛው እርገጥ የሆነና መበላለጡም አንዱን ክልል ከሌላው በተሻለ አፈፃፀም በማስመዝገብ ተራማጅ አልሆነም። ዝቅ ያለ ውጤት ያስመዘገቡ እንደ ጋምቤላ ያሉ ክልሎችም አሉታዊ ወደሚለው ዝቅተኛ ደረጃ አልወረዱም። ለዚህ ዋናው ምክንያት በሁሉም ክልሎች መሰረታዊ የዴሞክራሲ መለኪያዊች ጥቅም ላይ የዋሉ የሕግ ማዕቀፍና ፖሊሲዎች መኖራቸው ሲሆን፥ እነዚህ ሕጎችና ፖሊሲዎች መሬት ላይ መውረዳቸውና መተግበራቸው ሌላኛው ልዩነት የፈጠረ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን።

**For More Info**

info@cardeth.org www.cardeth.org @CardEthiopia +251 116-671 657

Addis Ababa, Ethiopia

Visit Our Website

▼

CARD

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል

CENTER FOR THE ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY

MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF THE GAME!